# የፌደራል የፍትህ አካላት ባለሙያዎች ስልጠና ማዕከል

**ለረጅም ጊዜ የስራ ላይ ሰልጣኞች የተዘጋጀ**

**የስልጠና ሞጁል**

## የውሳኔ አጻጻፍ በተመለከተ ስለሚገባው መሰረታዊ መርሆችና ይዘቶች

በፌደራል የፍትህ አካላት በለሙያወች ማሰልጠኛ ማእከል የተዘጋጀ

# 1. መግቢያ

በሃገራችን ለበርካታ ዘመናት የተለያዩ ህጎችን በማውጣት ዜጎች በህግ አግባብ ተከራክረው ተገቢውን ውሳኔ እንዲያገኙ ጥረት ሲደረግ ቆይቷል፡፡ በተለይም በሃገራችን የወጡት ህግጋተ-መንግስት፣ የወንጀልና የፍታብሄር ህጎች ተግባራዊ መሆናቸው ዜጎች ህግ አክባሪዎች እንዲሆኑ ከማስቻሉም ባሻገር የመብት ጥሰትና የንብረት ዘረፋ ሲያጋጥማቸው በህግ አግባብ ተከራክረው መብታቸውን አንዲያስከብሩና ንብረታቸውን እንዲያስመልሱ ከመርዳቱም በላይ በሃገራችን የህግ የበላይነት እንዲሰፍንና ቅሬታዎች በህግ አግባብ ብቻ እልባት እንዲያገኙ ረድቷል፡፡በመሆኑም ህጎች ፀድቀው ስራ ላይ የዋሉ ቢሆንም ከህግ አውጭው መንፈስ ውጭ በመተርጎም፣ የዳኞችም ይሁን የዐቃቤያነ ህግ ሙያዊ ብቃት እንዲሁም ወጥ የሆነ የክስ አመሰራረትና የውሳኔ አፃፃፍ ስርዓት ባለመኖሩ የክትትልና የቁጥጥር ስርዓቱም እጅጉን የላላ ሆኖ በመቆየቱ የሃገራችን ህዝቦች በሚፈለገው ደረጃ በህግ አግባብ መብታችውን ማስከበር ችለዋል ለማለት አያስደፍርም፡፡

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን መንግስት የፍትህ ስርዓቱን አሰራር ለማሻሻል ግልፅና ተጠያቂነት ያለው አሰራር ለመዘርጋት ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡ በተለይም በሙያው የተሰማሩ ዐቃቤ ህጎችና ዳኞች በአጭርና በረዥም ጊዜ የቅድመ ስራ እና የስራ ላይ ስልጠና በመስጠት ሙያዊ ክህሎታቸውን የበለጠ እንዲያሻሽሉ እየተደረገ ይገኛል፡፡በዚህ ፅሁፍ ውስጥ በመሠረታዊነት ለማተኮር የተፈለገው በፍትህ አካሉ የተሰማራ ባለሙያ በያዘው ጉዳይ ላይ የሚሠጠውን ውሳኔ እንዴት በፅሁፍ ሊያሰፍር እንደሚገባ ነው፡፡ ለአፃፃፍ ያመች ዘንድ ሁሉንም ክህሎቶች በውሳኔ አፃፃፍ ስርዓት መግለፅ ያስፈልጋል፡፡ በየትኛውም ደረጃ የሚገኝ የፍትህ አካል የሚፅፋቸው ውሳኔዎች ትዕዛዞች ከሌሎች የፍትህ አካል፣ ከህብረተሰቡ ወይም ከባለጉዳዩ ጋር የሚገናኝበት /የሚግባባበት/ ነው፡፡

በፅሁፍ የሚሠፍረው ውሳኔ ተቀባይነት እንዲኖረው ለስራው በተፈለገው መጠን የተመጠነ ብቻ ሳይሆን የሚነበብና የማሳመን ሃይል ያለው የራሱ የሆነውን የአፃፃፍ ቴክኒክ የተከተለ መሆን ይኖርበታል፡፡ ለውሳኔ አፃፃፍ በጥቅሉ የምንጠቀምበትና የምንስማማበት ቴክኒክ እንዳለ ሁሉ የፀሃፊው የግል ክህሎትም አስፈላጊ ነው፡፡ የተሻሉ ባለሙያዎችን የክስ አዘገጃጀት እና የውሳኔ

አሰጣጥ አፃፃፍ ስርዓት መመልከት እንዲሁም በአንዳንድ ዩኒቨርስቲዎች የሚሠጡ Judgment Writing ፅሁፎችን በማንበብ የአፃፃፍ ክህሎትን ለማዳበርና የራስ ለማድረግ ወሳኝ ናቸው፡፡ በተቻለ መጠን ባለሙያዎች የሚሰጡት የውሳኔ ፅሁፎች ተነባቢ እና አሳማኝ ሊሆኑ ይገባል ይህ ካልሆነ ግን ለወቀሳ የተጋለጡ ናቸው፡፡ የዚህ ምክንያትም የውሳኔው ይዘት አለዚያ ስነ-ምግባር የጐደለው የአፃፃፍ ክህሎት ከመከተል የመነጨ ሊሆን ይችላል በአጠቃላይ የዚህ ፅሁፍ ዋና ዓላማ በውሳኔ አፃፃፍ ላይ የሚታዩ ችግሮችን በማስወገድ የተሻለ የውሳኔ አፃፃፍ ስርዓት ይኖር ዘንደ እንደመነሻ ማገልገል ነው፡፡

## 2. <u>የቅድመ ክስ ዝግጅት ታሣቢ ነጥቦች</u>፣

የፖሊስ የምርመራ መዝገብ የደረሰው ማንኛውም ዐ/ሕግ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 38 መሠረት ተገቢውን ከመወሰኑ በፊት የቅድመ ውሳኔ ዝግጅቱን የተሟላ ለማድረግ የም/መዝገቡን በጥንቃቄ መመርመርና ማጥናት ይኖርበታል፡፡ በዚህ መሠረት በተለይ በሚከተለው ነጥቦች ላይ ትኩረት ሊደረግ ይገባል፡፡

### 2.1 <u>የአሠራር ቅደም ተከተል ማውጣት</u>፡፡

ዐቃብያነ ሕግ በእጃቸው የሚገኙ የም/መዛግብትን ሲያጠኑና ሲመረምሩ እስረኛ ላለበት እንዲሁም በሕዝብ ጥቅም ላይ ከፍተኛ ጉዳት ያደረሱ መሆናቸው የሚታመንባቸው ከባድ ወንጀሎች የተፈጸሙበትን ጉዳይ ቅድሚያ በመስጠት አስፈላጊውን ተጨማሪ መመሪያ ወይም ውሳኔ መስጠት ይኖርባቸዋል፡፡

ሀ. በፖሊስ ምርመራ የተጣራበት ጉዳይ የወንጀል ተግባር መሆን አለመሆኑ ማለትም በወ/መ/ሕ/ቁ.23 ድንጋጌ መሠረት ወንጀልን የሚያቋቁሙ ማለትም የህግ (legal element) የድርጊት (material element) እና የሃሳብ (moral element) ባህሪያት ስለማሟላቱ ማረጋገጥ፡፡

ለ. በወ/መ/ሕ/ቁ.24 መሠረት በምክንያትና በውጤት (Cause and Effect) መካከል ግንኙነት መኖሩን በቅድሚያ ማረጋገጥ፡፡

ሐ. የኤግዚቪት መግለጫ የተያያዙ መሆኑን ማረጋገጥ ቅድሚያ የሚሰጠው ተግባር መሆኑ፣ ዐቃብያነ ሕግ የም/መዝገቡን ሲመረምሩ የወንጀሉ ድርጊት በኤግዚቪት ማስረጃ የተደገፈ ስለመሆኑ የሚጠቁም ፍሬ ነገር ካለበት ስለዚሁ ጉዳይ የኤግዚቪት መግለጫው በአግባቡ የተያያዘ መሆኑን ማጣራት ያስፈልጋል፡፡

### 2.2 <u>የቀድሞ የጥፋተኛነት ሪኮርድ መግለጫ መያያዝ</u>

የቀድሞ የጥፋተኝነት ሪኮርድ ለቅጣት ውሣኔ አሰጣጥ አስፈላጊ ማስረጃ ሆኖ የሚቀረብ ስለሚሆን፣ ዐቃቤ ሕግ ከያዘው የም/መዝገብ አንፃር ተፈፅሟል የተባለው ወንጀል

የሚያስከስስ መሆኑን የሚያስረዳ ማስረጃ ካለ ከመዝገቡ ጋር የቀድሞ  የጥፋተኝነት ሪኮርድ መግለጫ መኖር አለመኖሩ መጣራት ይገባዋል፡፡

2.3 <u>የማስረጃዎችን ይዘት መመርመር</u>፡፡

ዐቃብያነ ሕግ ከተገቢው ውሣኔ በፊት የምርመራ መዝገቡን ሲመረምሩ በማስረጃነት የተቆጠሩት ምስክሮች የሚሰጡት የምስክርነት ቃል ተመሣሣይ እና እርስ በርስ የሚደጋገፍ ይሁን ወይም ደግሞ አንዱ ሌላውን የሚያፈርስ መሆን አለመሆኑን እንዲሁም ተፈፅሟል የተባለው ወንጀል በሰነድ ማስረጃም ጭምር የተደገፈ ከሆነ የምስክሮች ቃል እና የሠነድ ማስረጃው ይዘት የሚጣጣም መሆኑን ወይም ደግሞ  በርካታ የሠነድ ማስረጃዎች ያሉበት ከሆነ በአከራካሪው ጭብጥ ላይ እነዚህ የሠነድ ማስረጃዎች ያላቸው የአስረጂነት ብቃት በጥልቀት መፈተሽ ይገባዋል፡፡በመሆኑም ዐቃብያነ ሕግ ከማናቸውም የወንጀል ምርመራ ክፍል የተላለፈላቸውን የም/መዝገብ  በማጥናት ከዚህ በላይ የተገለፁትንና ሌሎችንም አግባብነት ያላቸውን የቅድመ ውሣኔ መሰናዶዎች ካጠናቀቁ በኂላ ተከሣሹን በተከሰሰበት ወንጀል ጥፋተኛ ለማሰኘት የሚያስችል በቂ ማስረጃ መኖሩ ከታመነበትና ተጨማሪ ምርመራ እንዲደረግ መመሪያ መስጠት አስፈላጊ ሆኖ ካልተገኘ የዐቃብያነ ሕግ ቀጣይ ተግባር  የወንጀል ክስ ማመልከቻ ማዘጋጀት ይሆናል፡፡

በፍርድ ቤት ቀርቦ የሚታይ የማናቸውም የወንጀል ጉዳይ መሠረት የክስ ማመልከቻ ነው፡፡ ጉዳዩ ሊሰማ ቀጠሮ ከተያዘበት ቀን ጀምሮ ክርክሩ በመጨረሻ ፍርድ እስኪቋጭ ድረስ በከሣሽና በተከሣሽ መካከል በደረጃው መራራ የሙግት ፍልሚያ የሚካሄድበት፣ የምስክሮችን ትኩረት አሰባስቦ በእውነታም ሆነ በአሉታ በሚሰጡት ቃላቸው የሚፋጠጡበት ማዕከል የዐ/ሕግ የክስ ማመልከቻ ነው፡፡ በመሆኑም ፍርድ ቤት በሚቀርብ ጉዳይ ላይ ብርቱ ጥንቃቄን የሚጠይቀው ዋና ሥራ መከናወን ያለበት የወንጀል ክስ ከመዘጋጀቱ በፊትና በሚዘጋጅበት ወቅት ነው፡፡

ዐቃብያነ ሕግ የክስ ማመልከቻውን ረቂቅ አዘጋጅተው እንዳጠናቀቁ በክሱ ላይ የሚጨመር ወይም የሚቀነስ ነገር መኖሩን ለማረጋገጥ የክስ ማመልከቻውን ደጋግመው  ሊያነቡት ይገባል፡፡ የክስ ማመልከቻው ረቂቅ ዝግጅት እንደተጠናቀቀም ክሱ ሊያስነሳ የሚችለው ታሳቢ የመቃወሚያ ነጥቦች ያሉ መሆን አለመሆኑን ከወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ-ሥርዓት ቁጥር 130 አኳያ በማንሳት ክሱ ተቃውሞውን ማለፍ መቻሉን ዐቃብያነ ሕግ እርግጠኛ መሆን አለባቸው፡፡የክስ ማመልከቻው የሥነ-ሥርዓት ሕግ በሚጠይቀው ፎርማት መሠረት መዘጋጀቱንና ማናቸውንም  አስፈላጊ መረጃዎች አሟልቶ መያዙን ዐቃብያነ ሕግ በማያጠራጥር አኳኋን

ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል፡፡ ዐቃቤሕጉ ያዘጋጀው የክስ ማመልከቻ የመጀመሪያ ደረጃ ተቃውሞዎችን ማለፍ የማይችል የይዘትና የቅርፅ ድክመት ያለበት መሆኑ እየታወቀ ለፍርድ ቤት ማስተላለፍ ተገቢ አይሆንም፡፡ለወንጀል ድርጊቱ ከሚስማማ ተገቢ የሕግ ድንጋጌ ጋር ያልተዛመደ እና የወንጀሉን ዝርዝር ፍሬ ነገር በትክክል የማያመለክት የክስ ማመልከቻ ወደ ችሎት ይዞ በመቅረብ ተከሣሽን ለመርታት ክርክር መግጠም ከፍትሕ መስመር የወጣ እና ከዐቃብያነ ሕግ የሚጠበቀውን በገለልተኝነት ሙያዊ ኃላፊነትን የመወጣት መንፈስ የሚያደፈርስ የተከሣሹን የመከላከል መብት የሚያጣብብ፣ የሀብት ብክነት የሚያስከትል እና በአጠቃላይ የማይመለስ ዘርፈ ብዙ ጉዳት የሚያስከትል ስለሚሆን የወንጀል ክስ ሲዘጋጅ ከፍተኛ ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል፡፡

ከማናቸውም የወንጀል ምርመራ ክፍል ለዐ/ሕግ መሥሪያ ቤት የተላከው የም/መዝገብ በወንጀል የሚያስከስስ ሆኖ ሲገኝ፣ ዐቃብያነ ሕግ የክስ ማመልከቻውን አዘጋጅተው ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ማቅረብ የሚገባው የም/መዝገቡ በደረሰ በአስራ አምስት ቀን ጊዜ ውስጥ እንደሆነ የወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ.109 ይደነግጋል፡፡የደንብ መተላለፍን የሚመለከት ካልሆነ በስተቀር ማናቸውም የወንጀል ጉዳይ በሥነ-ሥርዓት ሕጉ መሠረት የተዘጋጀ የፅሑፍ የክስ ማመልከቻ ሳይቀርብ በፍርድ ቤት ሊሰማ አይችልም፡፡በፍርድ ቤት ሳይፈቀድ አካለ መጠን ባላደረሱት ላይ የወንጀል ክስ አይቀርብም ነገር ግን ፍርድ ቤቱ የፈቀደ እንደሆነ አካለመጠን ባላደረሱት አጥፊዎች ላይ የሚቀርበው የክስ ማመልከቻ አካለመጠን ባደረሱ ተከሣሾች ላይ እንደሚቀርበው ዓይነት ይሆናል፡ የወ/መ/ስ/ስ/ቁጥር 172 መሠረት ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## 3. <u>በክስ ዝግጅት ሂደት ዐቃቤያነ ሕግ አስቀድመው ሊያውቋቸው እና ሊያረጋግጡ የሚገቧቸው የመቃወሚያ ነጥቦች</u>

ከወንጀል ክስ አዘገጃጀት በፊትም ሆነ የክስ ማመልከቻው በሚዘጋጅበት ወቅት ከዚህ በላይ ከተገለፁት በተጨማሪ ትኩረት የሚሹ ሌሎችም ነጥቦች መኖራቸውን መገንዘብ የግድ ይላል፡፡ ከነዚህም ውስጥ ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡

### 3.1 <u>ፍርድ ቤቱ ክሱን ሰምቶ ለመወሰን ተገቢው የሥረ ነገር እና የአካባቢ ሥልጣን ያለው መሆኑን ማረጋገጥ፡፡</u>

ዐቃብያነ ሕግ የወንጀል ክስ ማመልከቻ አዘጋጅተው የሚያቀርቡት ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት በአድራሻ ሲሆን፣ ዐቃቤሕግ የወንጀሉን ክስ የሚያቀርብለት ፍርድ ቤት የሥረ ነገር እና የአካባቢ ጣምራ ሥልጣን እንዳለው ሳይረጋገጥ ክስ ተዘጋጅቶ የቀረበለት ከሆነ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 110 መሠረት ፍርድ ቤቱ የክስ ማመልከቻውን ባለመቀበል ስለሚመልሰው በዚህ ሂደት በሚከተለው የጊዜ ብክነት የመብት ጥሰት እና ሌሎችም አላስፈላጊ ችግሮች እንዳይከሰቱ ጥንቃቄ ማድረግ ያሻል፡፡

## 3.2 ሌላ ተመሣሣይ ክስ በሌላ ፍርድ ቤት አለመኖሩን ማረጋገጥ፡፡

በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 130/2/ሀ ላይ እንደተመለከተው በወንጀሉ ዓይነት በሌላ ፍርድ ቤት ተመሣሣይ ክስ ቀርቦ በመታየት ላይ ባለበት ጉዳይ የሚቀርብ ማንኛውም ክስ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያን ስለሚያስከትል ዐ/ሕግ በጉዳዩ ላይ ለባለመብቱ ፍርድ ቤት ክስ ከማቅረቡ በፊት አስፈላጊውን ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

## 3.3 ጉዳዩ ቀደም ሲል በፍርድ ቤት ውሣኔ ያልተሰጠው መሆኑን ማረጋገጥ፡፡

በአንድ ወንጀል ድጋሚ ቅጣት ስለመከልከሉ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ-መንግስት አንቀፅ 23 በግልጽ ሲደነግግ  ማንኛውም ሰው በወንጀል ሕግና ሥነ-ሥርዓት መሠረት ተከሶ የመጨረሻ በሆነ ውሳኔ ጥፋተኛነቱ በተረጋገጠበት ወይም በነፃ በተለቀቀበት ወንደል እንደገና አይከሰስም ወይም አይቀጣም ይላል፡፡የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግም እንዲሁ ስለሕጋዊነት መርህ ባሰፈረበት አንቀፅ 2/5 ላይ በግልፅ እንደሚያረጋግጠው ማንም ሰው በሕግ መሠረት የመጨረሻ በሆነ ውሣኔ ጥፋተኛነቱ ተረጋግጦ ከዚህ ቀደም በተቀጣበት ወይም ሌላ ሕጋዊ እርምጃ በተወሰደበት ወይም በነፃ በተለቀቀበት ወንጀል እንደገና እንደማይከሰስ ወይም እንደማይቀጣ በማያሻማ አኳኋን ደንግጓል፡፡

በዚህም መሠረት በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 130/2/ለ መሠረት በዚያው ወንጀል ቀደም ሲል ተከሶ ነፃ የወጣ ወይም የጥፋተኛነት ውሣኔ የተሰጠው ግለሰብ ላይ የሚቀርብ የክስ ማመልከቻ ተቃውሞ ሊቀርብበት ስለሚችል ዐ/ሕግ የምርመራ መዝገቡን ጥናት አጠናቆ ወደ ክስ ከማምራቱ በፊት ተከሣሽ በጉዳዩ ቀደም ሲል ተከሶ የተቀጣ ወይም በነፃ የተለቀቀ መሆን አለመሆኑን ማረጋገጥ ይጠበቅበታል፡፡

## 3.4 ክሱ በይርጋ ሕግ ያልታገደ መሆኑን ማረጋገጥ

በመሠረቱ አንድ ጉዳይ በይርጋ ሕግ የታገደ ነው ወይስ አልታገደም የሚለውን ለመወሰን የይርጋውን ዘመን በትክክል ማሰላት ይገባል፡፡ዐ/ሕግ ክሱን ካቀረበ በኋላ አልፎ አልፎ በተከሣሽ በኩል በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ-ሥርዓት 130/2/ሐ መሠረት የሚቀርብ ተቃውሞ የይርጋውን

ዘመን ጊዜ በትክክል ካለማስላት የተነሳ ስለሚሆን የይርጋን ዘመን ጊዜ በጥንቃቄ ማስላት ያስፈልጋል፡፡

በመሠረቱ ስለይርጋ ዘመን አቆጣጠር፣ ስለይርጋ መታገድ ወይም መቋረጥ በወንጀል ሕጉ ከአንቀጽ 216 እስከ 222 ድረስ ባሉት ድንጋጌዎች ላይ የተመለከተውን መርህ ዐቃብያነ ሕግ በጥንቃቄ ማንበብ እና መገንዘብ ይኖርባቸዋል፡፡በዚህም መሠረት በሕግ በሌላ አኳኋን ካልተደነገገ በስተቀር ከዚህ በላይ የተመለከተው የይርጋ ዘመን ካለፈ በኋላ በማናቸውም ወንጀል የግል አቤቱታን ወይም የወንጀል ክስን መቀበልና ጉዳዩን በዳኝነት ማየት አይቻልም፡፡

## 3.5 <u>የክስ ተነጥሎ አለመቅረብ በተከሣሽ ላይ ጉዳት የማያስከትል መሆኑን ማረጋገጥ፡፡</u>

በመሠረቱ ዐቃቤሕግ የሚያዘጋጀው የክስ ማመልከቻ አንድ ተከሣሽ ብቻውን በፈፀመው አንድ ወንጀል ወይም፣ አያሌ ተከሣሾች በዋናው ወንጀል አድራጊነት፣ በግብረአብርነት፣ በአባሪነት ወይም በአነሳሽነት ደረጃ በጋራ በፈፀሙበት አንድ ወንጀል ምክንያት አንድ ክስ የያዘ ሊሆን ይችላል፡፡ ከዚህም በቀር የክስ ማመልከቻው ከአንድ የወንጀል ድርጊት ጋር በተያያዙ ወይም ባልተያያዙ ሌሎች ከአንድ የበለጡ ተከሣሾችን የሚመለከቱ ብዙ ክሶች ሊይዝ ይችላል፡፡ጉዳዩ በአንድ የምርመር መዝገብ የተጣራ እስከሆነ ድረስ  አንድ ወንጀል ወይም ብዙ የተለያዩ ወንጀሎች የፈፀሙ ተከሣሾችን በአንድ የክስ ማመልከቻ ውስጥ በማጠቃለል አንድ ክስ ወይም ከአንድ የበለጡ ክሶችን አቅርቦ ማስረጃ ማሰማት ለዐቃቤሕጉ ይቀለዋል፡፡ይህም ሲሆን ምስክሮቹ በሆነ ባልሆነው እንዳይመላለሱና ከዕለት ስራቸው እንደይፈናቀሉ ያደርጋቸዋል፡፡

በሌላ በኩል ግን በተለይ ብዙ ተከሣሾች በተለያዩ ወንጀሎችና ክሶች በአንድ የክስ ማመልከቻ አማካኝነት ክስ ሲቀርብባቸው ከመካከላቸው በአንዳንዶቹ ላይ ጉዳት ሊደርስ ይችላል፡፡ ጉዳቱም አንዳንድ ተከሣሾች በአጭር ጊዜ የሚያቀርቡት መከላከያ ጥንካሬ ወዲያውኑ በነፃ የሚያስለቅቅ ጉዳይ ሲኖራቸው፣አንዳንዶቹ ደግሞ በማወቅም ሆነ ባለማወቅ የራሳቸውን ጉዳይ ቶሎ ውሣኔ እንዳያገኝ የሚያጓትቱበት ሁኔታ ይፈጥራሉ፡፡ ፍርድ ቤት በሁሉም ጉዳዮች ላይ ውሣኔ የሚሰጠው አንድ ጊዜ ስለሚሆን ጉዳያቸው ውሣኔ እንዳያገኝ የሚያጓትቱ ተከሣሾች የሚጎዱት ከሁሉም በላይ አስቸኳይ ውሣኔ የሚያስገኝ ጉዳይ ያላቸውን ሌሎች ተከሣሾች ይሆናል፡፡ዐቃቤሕግ እንዲህ ዓይነት ሁኔታን ሊፈጥሩ የሚችሉ ጉዳዮችና ተከሣሾች የሚኖሩ መሆናቸውን የምርመራ መዝገቡን በሚያጠናበት ጊዜ የሚረዳ ከሆነ ችግሩን የሚያስወግድበትን ወይም የሚያቃልልበትን ሁኔታ መፍጠር ይኖርበታል፡፡ በመሠረቱ በአንድ የክስ ማመልከቻ የግድ መከሰስ የሚኖርባቸው ካልሆነ

በቀር ዐቃቤሕግ በመነጣጠል ክሶችን ቢያቀርብም ችግሩ ሊወገድ ይችላል፡፡ ዐቃቤሕግ በራሱ አነሳሽነት ይህን ማድረግ ባይፈልግ፣ ማንኛውም ተከሣሽ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 130/2/መ/ መሠረት ከሌሎች ተከሣሾች ጋር መከሰሱ የሚጎዳው በመሆኑ ክሱ ከሌሎች ተከሣሾች ተነጥሎ ለብቻው እንዲቀርብበት እንዲደረግለት ተቃውሞ ማቅረብ ይቻላል፡፡ ፍርድ ቤቱም የዐቃቤ ሕጉን መልስ ከሰማ በኋላ እንደነገሩ ሁኔታ ተቃውሞውን በመቀበል ወይም ውድቅ በማድረግ አስፈላጊውን ብይን ይሰጣል፡፡

### 3.6 ክስ ለማቅረብ ፈቃድ የተሰጠ መሆኑን ማረጋገጥ፡፡

አንዳንድ ከፍተኛ የመንግስት ባለሥልጣናት ወይም የሕዝብ ተመራጮች የተመረጡበትን ተግባር ወይም የተጣለባቸውን የሥራ ኃላፊነትና ሥልጣን በአግባቡ እንዲወጡ ለማስቻል ሲባል የተሻለ የሕግ ጥበቃ ሊደርግላቸው እንደሚገባ በሕገ-መንግሥቱም ሆነ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የወንጀል ሕግ ላይ በግልፅ ተመልክቷል፡፡ በዚህም መሠረት እነዚህ አካላት ከባድ ወንጀል ሲፈፅሙ እጅ ከፍንጅ ካልተገኙ በስተቀር የመያዝም ሆነ ክስ የማቅረብ ሥነ-ሥርዓት ሊፈፀም እንደማይገባ  በሕጉ ተገልጿል፡፡ ዐ/ሕግ የደረሰውን የፖሊስ ምርመራ መዝገብ አጥንቶ ወደ ክስ ዝግጅት ከማምራቱ በፊት ከተከሣሹ ሥራ አንፃር ከሚመለከተው የመንግስት አካል በተለይ ፈቃድ የተሰጠ መሆኑን ማረጋገጥ ይጠበቅበታል፣ ይህ ካለሆነ ግን በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት 130/2/ሠ መሠረት በሕጉ መሠረት ፈቃድ ያልተገኘበት ክስ በተከሣሽ በኩል የመጀመሪያ ደረጃ ተቃውሞ የሚቀርብበት ነው፡፡

## 4. የወንጀል ክስ ማመልከቻ አጠቃላይ ይዘት፣

ዐቃቤሕግ የምርመራ መዝገብ ወይም የቀዳሚ ምርመራ አድራጊ ፍ/ቤት መዝገብ ከደረሰው በኋላ ጉዳዩን መርምሮ የሚያስከስስ ሆኖ ከተገኘ በ15 ቀን ውስጥ ተገቢውን ክስ አዘጋጅቶ ለሚመለከተው ፍ/ቤት ማቅረብ እንዳለበት የወ.መ.ሕ.ሥ.ሥ.ቁ.109/1/ ይደነግጋል፡፡ የሥራ ብዛትና የባለሙያ ዕጥረት የወንጀሉ ውስብስብነት የተከሣሾችና የምስክሮች ቁጥር በርካታ መሆን ጉዳዩን ለመመርመር ረዥም ጊዜ የሚጠይቅ ሊያደርገው ይችላል፡፡ ይልቁንም የክስ ማመልከቻው ብዙ ወንጀሎችን የሚመለከትና በርካታ ክሶችን የሚያጣምር ሲሆን ሰፊ ጊዜ መጠየቁ የማይቀር ነው፡፡ በመሆኑም በሕጉ ላይ የተወሰነው የ15 ቀን ጊዜ ገደብ አልፎ አልፎ በቂ እንደማይሆን መገንዘብ አያዳግትም፡፡ይሁን እንጂ አሰራራችንን ቀልጣፋ በማድረግ የተፋጠነ ውሣኔ መስጠት የደንበኞችን ፍላጐት ከማርካት አንፃር ትኩረት የሚሰጠው ጉዳይ ነው፡፡የሚያዘጋጀው የክስ ማመልከቻ በወ.መ.ሕ.ሥ.ሥ.ቁ.111 እና ቁጥር 112 የተገለፁትን ሁኔታዎች የሚያሟላና

ከወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ጋር በተያያዘው 2ኛ ሠንጠረዥ በምሳሌነት ከሰፈረው የክስ አዘገጃጀት ጋር የተቀራረበ መሆን ይገባዋል፡፡ ከፍ ሲል በተገለፀው መሠረት የክሱ ማመልከቻ፡-

1/ ክሱ የሚቀርብለትን ፍ/ቤት ሥምና አድራሻ፣

2/ ክስ የተዘጋጀበትን ቀን እና ቁጥር

3/ የዐቃቤ ሕጉን እና የፖሊሱን መዝገብ ቁጥር፤

4/ ከሳሽ -ዐቃቤ ህግ

5/ የተከሳሽ ስም፣ዕድሜ፣አድራሻና ዜግነት

6/ የምስክሮች ስም ዝርዝርና አድራሻ

7/ የዐቃቤ ህጉ ፊርማ ይኖራል

8/ የተጣሰውን የሕግ አንቀጽ፤

9/ የወንጀሉን ዝርዝር፣ማለትም ወንጀሉ የተፈፀመበት ጊዜና ቦታ፣ ተበዳዩንና ወንጀል የተፈፀመበትን ንብረት ወይም መብት፣ የወንጀሉን አፈፃፀም ሁኔታ ከሕጉ ጋር በማገናዘብ መግለጽ ይኖርበታል፡፡ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ ወንጀሎች የተፈፀሙ ሲሆን፣1ኛ፣2ኛ፣3ኛ  ክስ እየተባለ በርዕሰ ተለይቶ እያንዳንዱ ክስ ከላይ በተገለፀው መሠረት መዘጋጀት ይገባዋል፡፡በቀረበው የምርመራ ውጤት መሠረት ወንጀል መፈፀሙ በዐቃቤሕጉ ታምኖበት ነገር ግን የተጣሰው የሕግ አንቀጽ የትኛው እንደሆነ ለመወሰን ሁኔታው አሻሚ የሚሆንበት ጊዜ ሊያጋጥም ይችላል፡፡ በዚህን ጊዜ ዐቃቤሕጉ በወ.መ.ሕሥ.ሥ.ቁ 113/1/ መሠረት በይበልጥ ተጥሷል ብሎ የሚያምንበትን ድንጋጌ በመጥቀስ ክስ ካዘጋጀ በኋላ በተጨማሪም ሌላውን አማራጭ የሕግ አንቀጽ በመጥቀስ ተተኪ ክስ ማቅረብ ይችላል፡፡ በሌላ በኩል ተከሣሹ ደጋጋሚ ወንጀለኛ በመሆኑ ምክንያት በመጨረሻ የፈፀመው ወንጀል በሚከብድበት ጊዜ፣ወንጀሉ ባይከብድ ኖሮ መጥቀስ ያለበት የሕግ ድንጋጌ ጠቅሶ ክስ ማቅረብ አለበት፡፡

ፍ/ቤት በቀረበው መሠረት በተከሳሹ ላይ የጥፋተኛነት ውሣኔ የሰጠ ከሆነ ዐ/ሕጉ የጥፋተኛነት ውሣኔው ወደ ከባዱ የሕግ አንቀጽ እንዲለወጥለት ያመለክታል፡፡ ፍ/ቤቱም በዚሁ መሠረት በከባዱ የሕግ አንቀጽ የጥፋተኛነት ውሣኔ አሳልፎ ተገቢውን ቅጣት ይፈርዳል፡፡ክስ በሚዘጋጅበት ጊዜ ስህተት ሊከሰት ይችላል፡፡ ስህተቱ ቀላልና ጉዳት የማያስከትል ወይም መሠረታዊና ተከሣሹን የሚጎዳ ሊሆን ይችላል፡፡ ስህተቱ  ቀላል ከሆነ፣ የክስ ማመልከቻው ለውጥ የሚያስፈልገው አይሆንም፡፡ነገር ግን ስህተቱ ከባድና ተከሣሹን የሚጎዳ ከሆነ በወ.መ.ሕ.ሥ.ቁ. 119 መሠረት ፍ/ቤቱ በራሱ አነሳሽነት ወይም ጥያቄ ሲቀርብለት ክሱ እንዲሻሻል ትዕዛዝ ለመስጠት

ይችላል፡፡በመሆኑም በወ.መ.ሕ.ሥ.ሥ.ቁ.121 መሠረት ምስክሮቹ ቃላቸውን እንዲሰጡ ያደርጋል፡፡ ዐቃቤሕግ ክስ ካቀረበ በኋላ ክሱን ለመተው ወይም ለማንሳት የሚፈለግበት ሁኔታ ሊኖር ይችላል፡፡ ለምሳሌ ጉዳዩን በተመለከተ አስፈላጊ የሆነው ዋና ማስረጃ ሲጠፋ ክሱን መቀጠል የማይችልበት ሁኔታ ሊኖር ይችላል፡፡ተጨማሪ ምርመራ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ወይም ክሱ እንዲሻሻል ተገቢ ሆኖ ሲገኝ ክሱን ማንሳት ግድ ይሆንበታል፡፡ በወ.መ.ሕ.ሥ.ሥ. 122 ክስ የሚነሳበት ሁኔታ በዝርዝር ተመልክቶ የነበረ ቢሆንም የዚህ ድንጋጌ ንዑስ ቁጥር 1፣2፣እና 4 በአዋጅ ቁጥር 11/80 አንቀጽ 26 እንዲሁም በአዋጅ ቁጥር 39/85 መሠረት የተሻሩ ስለሆነ በአሁኑ ጊዜ ተፈፃሚነት የላቸውም፡፡ በአንፃሩ አዋጅ ቁጥር 11/80 ተክቶ የነበረው አዋጅ ቁጥር 39/85 በአዋጅ ቁጥር 73/86 ቀጥሎም በ74/86 የተሻረ በመሆኑና ከዚያ ወዲህ ክስ ለማንሳት የሚያስችሉትን ዝርዝር ሁኔታዎች የሚወስን ሕግ ባለመውጣቱ በዚህ ረገድ ክፍተት ያለ ይመስላል፡፡

የፌዴራል መንግሥት አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣው አዋጅ ቁጥር 471/98 አንቀጽ 23/3 የፌዴራሉ መንግስት ፍትሕ ሚ/ር የወንጀል ክስን በሕግ መሠረት ለማንሣት እንደሚችል ደንግጓል፡፡ ይሁን እንጅ ዝርዝር ሁኔታውን በሌላ ሕግ እንደሚወሰን ስለሚጠቁም በራሱ በቂ ሆኖ አይታይም፡፡ ነገር ግን የወንጀሉ ክስ ባለቤት የሆነው መንግሥታዊ አካል ክሱን መተው ወይም ማንሳት አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው ይህን እርምጃ ከመውሰድ የሚታገድበት በቂ ምክንያት አይኖርም፤የአማራ ክልል አስፈፃሚ አካላትን እንደገና ለማደራጀት የወጣው አዋጅን ያሻሻለው አዋጅ 120/1998 አንቀጽ 21(6) መሠረት የወንጀል ክስ የማንሳት ስልጣን ለፍትህ ቢሮ ተሰጥቶ ይገኛል፡፡

5. <u>በወንጀል ክስ ሂደት ያጋጠሙ ችግሮች</u>፡፡

በዐ/ሕግ የክስ አዘገጃጀት ረገድ በርካታ ችግሮች የሚያጋጥሙ እንደሆነ ይታወቃል፡፡ በየደረጃው የሚሰሩ ዐቃብያነ ሕግ የወንጀል ሥነ-ሥረዓት ሕጉን ያልተከተለ ልዩ ልዩ ግድፈቶች የሚታዩበትን ክስ በማዘጋጀት ወደ ፍርድ ቤት የሚያቀርቡበት አሠራር የዐቃቤሕግን የማስቀጣት አቅም በእጅጉ እያሳነሰው ሕብረተሰቡ በፍትሕ ሥርዓቱ እና በፍትሕ አስተዳደር አካላቱ ላይ ያለው አመኔታ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያሽቆለቆለ መምጣቱ ይስተዋላል፡፡በወንጀል ክስ ዝግጅት ሂደት የሚከሰቱ ችግሮችን ሙሉ በሙሉ መዘርዘር አዳጋች ቢሆንም የሚከተሉትን እንደአብነት መጥቀስ ይቻላል፡፡

5.1 ለክሱ አግባብነት ያለው የሕግ አንቀፅ ለይቶ አለመጥቀስ ግልፅና የተሟላ የክስ ማመልከቻ አለማዘጋጀት ይህም ማለት፡-

ሀ. በቂ ማስረጃ በሌለው ጉዳይ ክስ ማዘጋጀት፤

ለ. መከሰስ የማይገባቸውን ሰዎች በክሱ ውሰጥ ማካተት እንዲሁም በተቃራኒው መከሰስ የሚገባቸውን ሰዎች በክሱ አለማካተት፤

ሐ. በተከሣሹ ላይ ከአንድ በላይ ክስ ማቅረብ ሲገባ አንድ ክስ ብቻ ማቅረብና ከአንድ በላይ ክስ በቀረበ ጊዜም የትኛው ማስረጃ የትኛውን ክስ እንደሚያስረዳ ለይቶ በግልፅ አለማመልከት፤

መ. የተከሣሽንም ሆነ የምስክሮችን አድራሻ በትክክል አለመመዝገብ፣ የታይፕ ግድፈቶችን ሳያርሙ ወደ ፍርድ ቤት መላክ፣ አልፎ አልፎም ቢሆን በክስ ቻርጅ ላይ ዐ/ህግ ሳይፈርም ወይም ማህተም ሳይደረግበት ወደ ፍርድ ቤት መላክ፣

ሠ. ወንጀሉ የተፈፀመበትን ጊዜና ቦታ በክስ ማመልከቻው ላይ አለመግለፅ፤

ረ. በይርጋ የታገዱ ጉዳዮች ላይ ክስ መመስረት፣

ሰ. የግል ተበዳይና ተከሣሹ በሰጡት ቃል ላይ ብቻ ተመስርቶ ክስ ማዘጋጀት፤

ሸ. አግባብነት ያለውን አዋጅ፣ደንብ ወይም መመሪያ በትክክል ለይቶ አለማወቅ፤

ቀ. ኢግዚቢት ባላቸው ጉዳዮች ላይ ኢግዚቢት መኖሩን በክሱ ቻርጅ ላይ አለማመልከት

በ. የምስክሮችን ቃል መሠረት አድርጎ ክስ ከማዘጋጀት ይልቅ ፖሊስ በምርመራ መዝገቡ መቅድም ላይ የጠቀሰውን የወንጀል ዓይነት ጠቅሶ ከማስረጃው ጋር የማይጣጣም ክስ ማዘጋጀት በዋነኛነት የሚጠቀሱ ችግሮች ናቸው፡፡

በክስ አዘገጃጀት ረገድ የሚታዩ ችግሮችን አስመልክቶ ከዚህ በላይ የተዘረዘሩት ችግሮች አዘውትረው የሚከሰቱ መሆናቸው ስለተረጋገጠ እነዚህ ችግሮች ያሉበት ክስ ተዘጋጅቶ ፍ/ቤት ሲቀርብ ውጤት አልባ ከመሆኑም በላይ በተከሣሽ እና በምስክሮች ላይም አላስፈላጊ የሆነ መጉላላትን በማስከተል ሊካስ የማይችል ጉዳት ያደርስባቸዋል፡፡ እንዲሁም በዐቃቤ ሕግና በፍ/ቤት ላይ ያለአግባብ የሥራ ጫናና የማቴሪያል ብክነት ያስከትላል፡፡ ይህም በመሆኑ በወንጀል ፍትሕ አስተዳደሩ ላይ ከፍተኛ የሆነ አሉታዊ ተጽእኖ ይኖረዋል፡፡ በመሆኑም አሁን የተጀመረውን BPR (ስራን መልሶ የማደራጀት) ጥናት መሠረት የተቀየሱ የለውጥ አቅጣጫዎችን መሠረት በማድረግና አብረው የወረዱ የክስ አዘገጃጀት ፎርሞችን በመነሻነት በመጠቀም ለጥሩ ውጤት መስራት ካልተቻለ በኅብረተሰቡ ውስጥ ፍትሕን ማስፈን ቀርቶ አላማውን የሣተ ተግባር በማከናወን በውጤቱ ኀብረተሰቡ በአጠቃላይ በፍትህ አካላት ላይ አመኔታ እንዲያጣ ሊያደርግ ይችላል፡፡

**ለምሳሌ <u>የሚከተለውን ጉዳይ እንመልከት</u>፡፡**

**ጉዳይ** (Case) 1

ከሣሽ ዐቃቤ ሕግ፣ ተከሣሽ ወርቂ በላይ ፣ የመዝገብ ቁጥር___ዐቃቤ ሕግ ለክሱ የጠቀሰው የወ.ሕ.ቁ. 670 ሲሆን ተከሣሹ ፈጸመ የተባለው እና ምርመራ የተጣራበት የወንጀል ተግባር የግል ተበዳይ አልማዝ በኃይሉን መንገድ ላይ እየሄደች ሣለ አድርጋው የነበረውን 4 ግራም የአንገት ሐብል ወርቅ ከአንገቷ ላይ በጥሶ በመሮጥ ለማምለጥ ሲሞክር እጅ ከፍንጅ ተይዟል በሚል ነው፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ የተዘጋጀው ክስ ፍ/ቤት ከቀረበ በኂላ ተከሣሹ የእምነት ክህደት ቃሉን ተጠይቆ ባለሙያ አማክሬ እቀርባለሁ በማለቱ ፍ/ቤት ለሌላ ጊዜ ቀጥሮ ችሎቱ ከአበቃ በኂላ የችሎቱ ዐቃቤ ሕግ በጻፈው አስተያየት ተከሣሽ ወንጀሉን በፈጸመበት ወቅት ኃይል መጠቀሙን የሚያስረዳ ነገር ስለሌለ ክሱ መቅረብ የሚገባው በወ.መ.ሕ.ቁ.670 መሠረት በውንብድና ሣይሆን በወ.መ.ሕ.ቁ.665 መሠረት በስርቆት ወንጀል መሆን ይገባዋል የሚል እምነት አለኝ በማለት ለችሎት ኃላፊው ማስታወሻ አቀረበ፡፡

### የውይይት ነጥቦች

1. በተጠቀሰው ጉዳይ (Case) ላይ ዐቃቤ ሕግ በውንብድና የመሠረተው ክስ አግባብነት አለው የሚል አመለካከት አለዎት?
2. ዐቃቤ ሕግ በአንድም ይሁን በሌላ ምክንያት በወረዳ ፍ/ቤት ሥልጣን ሥር በሚወድቅ ጉዳይ ክሱን ለከፍተኛ ፍ/ቤት አዘጋጅቶ ሲያቀርብ ፍ/ቤቱ ክሱን ተቀብሎ ማከራከሩና በመጨረሻም ጉዳዩ በወረዳ ፍ/ቤት መታየት የሚገባው ስለሆነ በዚያው በኩል ዐቃቤ ሕግ ክሱን ማቅረብ ይችላል ብሎ መዝገቡን መዝጋቱ እንዴት ይታያል? እዚህ ላይ የክሱን የይርጋ ጊዜ፣ የከሣሽና ምስክሮችን በሁለት ፍ/ቤቶች መጉላላት ከግምት ውስጥ በማስገባት ተወያዩበት፡፡
3. ተከሳሽ ከላይ የተጠቀሰው አንቀጽ ተጠቅሶ ለወረዳ ፍርድ ቤት ዐቃቤ ህግ በተከሳሽ ላይ በስርቆት ወንጀል ክስ ቢመሠረት ተከሳሹ በከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩ ቀርቦ የነበረ መሆኑን ጠቅሶ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ቢያቀርብ ተቀባይነት ይኖረዋል?

### ጉዳይ (Case) 2

ከሣሽ ዐቃቤ ሕግ ተከሣሽ ተፈሪ ባንቲ የመዝገብ ቁጥር 1409/93 በተከሣሽ ላይ የቀረበው ክስ የወ.መ.ሕ.ቁ. 27/1 እና 523 ተጠቅሶ ሲሆን የግል ተበዳይ ቶፊቅ ረሺድን በግራ በኩል አንገቱ ላይ እና ግራ ክንዱ ላይ በእህል መቀሸሪያ ወግቶ በማቁሰል የመግደል ሙከራ ወንጀል ፈጽሟል ተብሎ ነው፡፡ በጉዳዩ ፍ/ቤት ለ5/7/94 ቀጠሮ ይዞ ተከሣሽ ባለመቅረቡ ፖሊስ ተከሣሽን ከወህኒ ቤት እንዲያርበው ታዞ ለ15/9/94 ዓ.ም ተቀጠረ፡፡ በ22/9/94 ተከሣሽ ቀርቦ ወንጀሉን አልፈጸምኩም በማለት ካደ፡፡ የዋስትና መብቱ እንዲጠበቅለት ሲጠይቅ ዐቃቤ ሕግ ተከሣሽ

የፈጸመው ወንጀል ከባድ በመሆኑና በግል ተበዳይ ላይ አስከፊ ውጤት ሊያስከትል ስለሚችል የዋስትና ጥያቄውን እቃወማለሁ አለ፡፡ ፍ/ቤቱ የዐቃቤ ሕግን ተቃውሞ ባለመቀበል ተከሣሽ በብር 4000(አራት ሺህ) ዋስ እንዲጠራና ምስክሮች እንዲቀርቡ አዞ ለ23/5/95 ተቀጠረ፡፡ በ23/5/95 ተከሣሽ አልቀረበም፡፡ ፖሊስ ተከሣሽን እንዲያቀርብ ታዞ ለ12/11/95 ተቀጠረ፡፡በ12/11/95 ምስክሮች ቀርበው 1ኛው የዐቃቤ ሕግ ምስክር የግል ተበዳይ ሲመሰክር፣ ተከሣሽን አላውቀውም፤ ቀኑንም አላስታውስም በ1990 ዓ.ም አንገቴና ክንዴ ላይ ከኂላ በስለት ወጋኝ በማለት አስረዳ፡፡ ፍ/ቤቱ በማጣሪያ ጥያቄ ስትወጋ ያዩ ሰዎች አሉ ወይ? ሲለው የሉም፣ ተፈሪ ባንቲ ነው የወጋው ሲሉ ሰምቻለሁ አለ፡፡ 2ኛዋ የዐቃቤ ሕግ ምስክር ተከሣሽን አላምውቀውም፤ በአጋጣሚ ዕቃ ልገዛ ስወጣ የግል ተበዳይ ደም በደም ሆኖ አየሁት በማለት አስረዳች፡፡ መዝገቡ በአዳሪ ለ14/11/95 ተቀጠረ፡፡ በ14/11/95 ዓ.ም ዐቃቤ ሕግ የጽሁፍ ማስረጃ አቅርቦ ለብይን ለ15/11/95 ዓ.ም ተቀጠረ፡፡ በ15/11/95 ተከሣሽ በቀረበበት የመግደል ሙከራ ወንጀል አልተመሰከረበትም በማለት ከክሱ በነጻ እንዲሰናበት ፍ/ቤቱ ውሣኔ ሰጠ፡፡ ዐቃቤ ሕግ በውሣኔው ላይ ቅሬታ የለኝም አለ፡፡

***<u>የመወያያ ነጥብ፣</u>***

- በዚህ ጉዳይ የግል ተበዳይ ራሱ ጉዳት ያደረሰበትን ሰው ለይቶ ባላወቀበትና በምስክርነት የተቆጠረችው አንድ ምስክርም የግል ተበዳይ ደም በደም ሆኖ ማየቷን እንጅ ተከሣሽ ወንጀሉን ሲፈጽም አላየሁም ባለችበት ሁኔታ ዐቃቤ ሕግ ክስ አቅርቦ ከዓመት በላይ ከተከራከረ በኂላ ተከሣሽ በነጻ እንዲሰናበት ፍ/ቤት ውሣኔ ሲሰጥ በውሣኔው ላይ ቅሬታ የለኝም ማለቱ እንዴት ይታያል? የስሚ ስሚ (hear say) ማስረጃ ከኢትዮጵያ የወንጀል አስተዳደር እና ከማስረጃ ህግ አንፃር ተቀባይነት አለው ብላችሁ ታምናላችሁ? ያላችሁን ሃሣብ ከጉዳዩ ጋር በማያያዝ ተወያዩበት፡፡

**ጉዳይ (case) 3**

ከሣሽ ዐቃቤ ሕግ፣ ተከሣሾችን እነ  ጣሴ በቀለ 6 ሰዎች፣ የመዝገብ ቁጥር ------ የክሱ ምክንያት ከተራ ቁጥር 1-5 የተጠቀሱት ተከሣሾች የግል ተበዳይ አናጋው አበበን አንገቱን አንቀው ሽጉጥና አንድ ራዶ ሰዓት ቀምተዋል በሚል ሲሆን የተጠቀሰባቸው የሕግ አንቀጽም የወ.መ.ሕ.ቁ.670 ነው፡፡እንዲሁም 6ኛዋ ተከሣሽ በወንጀል ሥራ የተገኘውን ሰዓት ተቀብላ አስቀምጣለች ተብሎ የወ.መ.ሕ.ቁ.682/1 ተጠቅሶ ክስ ቀርቦባታል፡፡ተከሣሾች ክሱን አልፈጸምንም በማለት ክደው ቃላቸውን ለፍርድ ቤት በመስጠታቸው ዐቃቤ ሕግ የሰውና የሠነድ ማስረጃ አቅርቧል፡፡ ዐቃቤ ሕግ ያቀረበው የጽሁፍ ማስረጃ ተከሣሾች ለፖሊስ የሰጡት ቃል ሲሆን ፍርድ ቤቱ ዐቃቤ ሕግ ተከሣሾች ለፖሊስ የሰጡት ቃል ነው በማለት ያቀረበው የጽሁፍ ማስረጃ ተከሣሾች ወንጀሉን

ላለመፈጸማቸው የሚያስረዳ በመሆኑ ተከሣሾች በነጻ ይሰናበታሉ በማለት ወሰነ፡፡ በማስረጃ አመራረጥና አቀራረብ ላይ ምን ችግር እንዳስተዋላችሁ ዐቃቤ ህግ ምን ማድረግ እንደነበረበት በማንሳት ተወያዩበት፡፡ በወ.መ.ህ.ስ.ስ.ቁጥር 27(2) መሰረት ለፖሊስ የሚሠጥ የተከሳሽነት ቃል ለማስረጃነት ማቅረብ ምን ያህል ተቀባይነት ይኖረዋል?

**ጉዳይ** (Case) 4

ዐቃቤ ሕግ ይግባኝ ባይ ጀሊ ነጐ የኦነግ ሠራዊት አባል በመሆን በጦርነት ተሣትፎ የወ.መ.ሕ.ቁ. 252/1/ሀ፣ተላልፎአል በማለት በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ክስ አቀረበ፡፡ ይግባኝ ባይም ወንጀሉን አልፈጸምኩም በማለቱ ዐቃቤ ሕግ ማስረጃ አቅርቧል፡፡ ዐቃቤ ሕግ ክሱን ያስረዳኛል በማለት ያቀረበው የጽሁፍ ማስረጃ ይግባኝ ባይ በወ.መ.ሕ.ሥ.ሥ.ቁ.35 መሠረት የሰጠውን ቃል ነው፡፡ ይግባኝ ባይም ወንጀሉን የፈጸምኩት ተገድጀ እና በኦነግ ሶስት ዓመት ታስሬ ነው በማለት ነው ቃሉን የሰጠው፡፡ ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ ይግባኝ ባይን ጥፋተኛ በማድረግ በ16 ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጣ ቢፈርድበትም ጠቅላይ ፍርድ ቤት በወንጀል መዝገብ ቁጥር --------ዐቃቤ ሕግ የራሱን ማስረጃ ስላፈረሰ ይግባኝ ባዩ በነጻ ይሰናበታል በማለት ወሰነ፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይስ ምን አስተያየት አላችሁ?

**ጉዳይ** (Case) 5

ተከሣሽ አቶ በልሁ  የግል ተበዳይ አቶ አናጋውን በቦክስ አፉ ላይ በመምታት ሶስት ጥርሶቱን አነቃንቆ ከኪሱ 150 ብር በመውሰዱ በ---ከተማ ፖሊስ መምሪያ በፖሊስ የምርመራ መዝገብ ቁጥር ----ምርመራ ተጣርቶበት መዝገቡ ለወረዳ ለዐቃቤ ሕግ ተልኮ መዝገቡ የተመራለት ዐቃቤ ሕግ በተከሣሹ ላይ በ1ኛ ክስ የወ/ሕ/556/1 በመጥቀስ በሰው አካል ላይ ቀላል ጉዳት በማድረስ ወንጀል እንዲሁም፣ በ2ኛ ክስ የወ/ሕ/አንቀጽ 665/1 በመጥቀስ በሥርቆት ወንጀል ክስ አዘጋጅቶበት ፍ/ቤት ከቀረበ በኂላ ፍ/ቤቱ  ጉዳዩን ተመልክቶ የተፈጸመው ወንጀል የውንብድና ወንጀል በመሆኑ ጉዳዩን የማየት ሥልጣን -------- ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው በማለት ክሱን በ21/4/2000 ስላቋረጠው መዝገቡ ለዞን ዐቃቤ ሕግ ተልኳል፡፡ከዚህ ጉዳይ የምንረዳው ክሱን ያዘጋጀው  ዐቃቤ ሕግ በቂ የሆነ ስልጠና ወይም ልምድ ማያገኝ በቀጥታ በምርመራ መዛግብት ላይ ውሣኔ እንዲሰጥ መደረጉን እና ውሣኔውም በቅርብ አለቃው ወይም ልምድ ባለው ዐቃቤ ሕግ ሣይታይ ወደ ፍርድ ቤት የተላከ መሆኑ ነው፡፡ በዚህ ዓይነቱ የአሰራር ግድፈት በርካታ ችግሮች እንደሚያጋጥሙ ማሣያ ነው፡፡ ተመሳሳይ በተግባር ያጋጠሙ ችግሮችን በማንሳት ተወያዩበት?

**ጉዳይ (Case) 6**

ለባህርዳር ዙሪያ ወረዳ ፍ/ቤት

ባ/ዳር፣

ከሣሽ ፡- ዐቃቤ ሕግ

ተከሣሽ 1ኛ. ሞላ በለው

2ኛ. ቢራገጥ በለው

<u>**ወንጀሉ**</u>

- በ1996 ዓ.ም የወጣውን የወ/ህ/ቁጥር 649(1) (ሀ) የተመለከተውን በመተላለፍ

<u>**የወንጀሉ ዝርዝር**</u>

ተከሣሾች በግፍ ሰው ለመግደል አስቀድመው በማሰብ በ25/5/2002 ዓ.ም ሟች አቶ ቦጋለ መርጊያ የተባለውን ከዚህ በፊት የ1ኛ ተከሣሽ ሚስት የነበረችውና በህጋዊ መንገድ የፈታችን ወ/ሮ ባፋና ከሟች ጋር በህጋዊ መንገድ ጋብቻ በመመስረት አብረው በመኖራቸው 1ኛ ተከሣሽ እኔ የፈታኋትን ሚስት አገባ በሚል ቂም በመያዝ 2ኛ. ተከሣሽ የወንድሜን ሚስት አገባ በሚል አስቀድመው ቂም በመያዝ ሟችን በ2 ጥይት በመምታት በግፍ ሰው መግደል ወንጀል ተከሰዋል፡፡

**ምስክሮች**

1. ወ/ሮ ጥሩወርቅ ይግዜ
2. አቶ አልታሰብ ገብሩ

**የመወያያ ነጥቦች፡-**

1. ከዚህ በላይ በተጠቀሰው የክስ ቻርጅ ሙሉ ነው ብለህ ታስባለህ? አይደለም ከሆነ ምላሽህ የተጓደሉ ነጥቦች የምትላቸውን በማውጣት በመዘርዝር ተወያዩበት?
2. ዐቃቤ ሕግ የክስ ቻርጁን አዘጋጅቶ ለባህዳርዳር ዙሪያ ወረዳ ፍርድ ቤት ያቀረበ በመሆኑ የወረዳው ፍርድ ቤት ስልጣኔ አይደለም ብሎ መዝገቡን መዝጋቱ ተገቢ ነው ብለህ ታስባለህ? ምክንያቱን በመጥቀስ ተወያዩበት?
3. ዐቃቤ ህግ ክሱን በማሻሻል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቀረበ ተከሣሾች በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ወረዳ ላይ ክሱ ቀርቦ የተዘጋ በመሆኑ ሁለተኛ ልንጠየቅ አይገባም ብለው ቢከራከሩ ያዋጣቸዋል ብላችሁ ታስባላችሁ ምክንያታችሁን በመጥቀስ ተወያዩበት?
4. ከፍተኛ ፍርድ ቤት ማስረጃውን ከሠማ በኋላ በተከሣሾች ላይ የ13 ዓመት ቅጣት ቢወስንና ዐቃቤ ሕግ በኤግዚቢትነት በተያዘው ሁለት ክላሽ ኮፕ መሣሪያ ላይ ውሣኔ ይሰጥልኝ ብሎ ቢያሳስብ ፍርድ ቤቱ በክስ ቻርጁ ላይ የኢግዚቪት ዝርዝር ስላልተጠቀሰ በሚል ቢያልፈው ተገቢ ነው ብላችሁ ታስባለች ምክንየቱን በመጥቀስ ተወያዩበት?
5. ከላይ የተጠቀሰውን ክስ አስተካክላችሁ አዲስ የክስ ቻርጅ በማዘጋጀት ተወያዩበት?

6. ተከሣሾች ወንጀሉን መፈጸማቸውን አምነው ድርጊቱን የፈጸምነው በደም ፍላት ራሣችንን መቆጣጠር ስላልቻልን ነው ብለው ቢከራከሩ የፍርድ ቤቱን ውሣኔ ያስቀይራል ብላችሁ ታምናላችሁ እንዴት?

## 5.2 በምርመራ መዛግብት ላይ በሚሰጡ መመሪያዎች ዙሪያ የሚታዩ ችግሮች

በፖሊስ የምርመራ መዛግብት ላይ ያልተሟሉ ነጥቦች እንዲሟሉ ተጨማሪ ምርመራ እንዲደረግ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/ 38/ሐ/ መሠረት የሚሰጠው መመሪያ በጉዳዩ ላይ ትክክለኛ ውሣኔ ለመስጠት ማለትም ክስ ለመመስረት ወይም መዝገቡን ለመዝጋት የሚያስችል ከፍተኛ ጠቀሜታ ያለው ሕጋዊ አሰራር ቢሆንም በቀላሉ ከመርማሪዎች ጋር በስልክ በመነጋገር ሊስተካከሉ በሚችሉ ጥቃቅን ጉዳዮች ወይም ጭራሽ መመሪያ መስጠት ሣያስፈልግ በመዛግብቱ ላይ ውሣኔ ለመስጠት በሚቻልበት ሁኔታ ሁሉ አላስፈላጊ የሆነ መመሪያ በመስጠት መዛግብቱ በመመሪያ በዐቃቤ ሕግ እና በፖሊስ መካከል እየተንከባለሉ በተገቢው ጊዜ ውስጥ ውሣኔ ባለማግኘታቸው ባለጉዳዮች ያለ አግባብ ይጉላላሉ፡፡

እንዲሁም በአንድ መዝገብ ላይ በሚሰጠው የተጨማሪ ምርመራ ትዕዛዝ መካተት የሚገባቸውን ነጥቦች በሙሉ ባለማካተት የተጠቀሰው ነጥብ ተሟልቶ መዝገቡ ለዐቃቤ ሕግ ከተመለሰ በኋላ በድጋሚ በመጀመሪያው መመሪያ ያልተጠቀሰው ነጥብ እንዲሟላ የሚታዘዝበት ተገቢ ያልሆነ አሰራር ይታያል፡፡ ለዚህ ዓይነት የአሰራር ችግር መኖር ምክንያቱ ዐቃብያነ ሕጉ የሚያከናውኗቸው ተግባራት የቅርብ ክትትልና ቁጥጥር እንዲሁም ድጋፍ አለመኖር በተለይም በመዛግብቱ ላይ ለመወሰን በራስ ያለመተማመን ችግር እንደሆነ ብዙዎቹ ዐቃቢያነ ሕግ ይስማሙበታል፡፡ሌላው በመመሪያ ዙሪያ የሚታየው ከፍተኛ ችግር መመሪያ ከተሰጠ በኋላ ፖሊስ መመሪያውን አሟልቶ በተገቢው ጊዜ ውስጥ መዝገቡን ለዐቃቤ ሕግ መልሶ መላኩን የመከታተያ ሥርዓት ባለመኖሩ መዝገቡ ለረጅም ጊዜ በመቆየቱ የክሱ የማቅረቢያ ጊዜ (ይርጋ) ያልፋል፡፡ ወይም ደግሞ ባለጉዳይ ካልተከታተለው በስተቀር የመዝገቡ ደብዛ የሚጠፋበት ሁኔታ ያጋጥማል፡፡ በዚህም ምክንያት ከፍተኛ የሕዝብና የግለሰብ ጥቅም ያለባቸው ጉዳዮች ፍተሃዊ ውሣኔ ሣያገኙ ይቀራሉ፡፡

በሌላ በኩል ተጨማሪ ምርመራ እንዲደረግ የሚሠጠው ትዕዛዝ አልፎ አልፎ የሚታየው የመርማሪ ፖሊስን ስብዕና የሚጋፋ፣በስድብ የታጀበ፣ ያልተገቡ ቃላቶች ያሉበትና ከጉዳዩ የራቀ የግል ስሜት የሚሰፍርበት ሁኔታ የሚስተዋል ሲሆን ይህ አይነት ትዕዛዝ ለትችት የተጋለጠ በመሆኑ ጥንቃቄ ሊደረግበት ይገባል፡፡አሁን ስራን መልሶ በማደራጀት (BPR) ጥናት ችግሩን በስፋት በማጥናት የመፍትሄ እርምጃ ስለተወሰደ መዝገብ ከሚመላለስ ፖሊስና ዐቃቤ ህግ

ተናበውና በመተጋገዝ ላይ ተመስርተው መስራት እንዲችሉ አቅጣጫ ስለተቀመጠ በተጨማሪ ምርመራ ምክንያት የመዝገብ መመላለስ ለማስቀረት ጥረት በመደረግ ላይ ይገኛል፡፡

## የመወያያ ነጥቦች

1. በአንድ የምርመራ መዝገብ ውስጥ የተከሣሽ ስም ወይም አድራሻ ተሟልቶ ያልተጻፈ ወይም የማይነበብ በሆነ ጊዜ ዐቃቤ ሕጉ በጽሁፍ መመሪያ መስጠት አለበት ወይስ መርማሪውን ፖሊስ በመጥራት ወይም በስልክ በማነጋገር ማስተካከል ይገባዋል ይላሉ?
2. ዐቃቤ ሕግ የጽሁፍ መመሪያ ከመስጠት ይልቅ መርማሪውን በስልክ በማነጋገር ያገኘውን መረጃ በፖሊስ የምርመራ መዝገብ ላይ በመመዝገብ ከሕግ አኳያ የሚኖረው ውጤት ምን ይመስልዎታል?
3. ብዙ ጊዜ እንደሚታየው መርማሪ ፖሊስ በጽሁፍ ካልታዘዘ በቀር በስልክም ይሁን በቃል ለሚሰጥ ትዕዛዝ ትኩረት ያለመስጠት ችግር ያጋጥማል በሌላ በኩል በጽሁፍ የሚሰጥ የተጨማሪ ምርመራ ትዕዛዝ የመዝገብ መዘግየት ወይም በዚያው መቆየት ያገጥማል ይህን ችግር በምን መልኩ መፍታት ይቻላል ተወያዩበት?
4. **3 አጠራጣሪ በሆኑ ጉዳዮች መሪ ትዕዛዝ በሚጠየቅበት አሰራር ዙሪያ የሚታዩ ችግሮች**

ዐቃቤ ሕጉ ለውሣኔ አጠራጣሪ የሆነ ጉዳይ ባጋጠመው ጊዜ መሪ ትዕዛዝ እንዲሰጠው ነገሩን ለበላይ ዐቃቤ ሕግ ማስተላለፍ እንደሚገባው በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ.41 ሥር ተደንግጓል፡፡

**በመሪ ትዕዛዝ አጠያየቅ ዙሪያ የሚታዩ ችግሮች**

1ኛ. በጉዳዩ ላይ ውሣኔ ለመስጠት ያልደፈረ ወይም በአንድም ሆነ በሌላ ምክንያት ውሣኔ ለመስጠት ያልቻለ ዐቃቤ ሕግ በመዝገቡ ውስጥ ለውሣኔ የሚያስፈልጉት ሁኔታዎች ተሟልተው እያሉ መሪ ትዕዛዝ እንዲሰጠው የሚጠይቅበት አጋጣሚ ይስተዋላል፡፡

2ኛ. በመሪ ትዕዛዝ ላይ ምላሽ የሚሰጡ የበላይ ዐቃቤ ህጐች አልፎ አልፎ የአቅም ችግር የተጠየቀውን ጥያቄ በውል አለማገናዘብ ጋር ተያይዞ ለተጠየቀው የመሪ ትዕዛዝ ጥያቄ ተገቢውን ህግ ጠቅሰው ያለመመለስ በዚህም የበታች ዐቃቤ ህግ በተሰጠው ምላሽ ያለመርካትና የመፃፃፍ ሁኔታ የሚፈጠርበት ሁኔታ መኖሩ፣

- ❖ በአጠቃላይ የበታች ዐቃቤህግ መሪ ትዕዛዝ የሚያስጠይቅ ወይም የማያስጠይቅ መሆኑን መጀመሪያ በአግባቡ መለየት ያለባቸው ሲሆን የላይ ዐቃቤ ህግም ጥያቄውን አገናዝበው ተገቢውን ምላሽ መስጠት አለባቸው፡፡መሪ ትዕዛዝ ሲጠየቅ በሠነዱ ውስጥ መካተት ያለበት

- ❖ ቀንና ኘሮቶኮል ቁጥር፣
- ❖ መሪ ትዕዛዝ የጠየቀው ፍትህ ጽ/ቤት መዝገብ ቁጥር፣
- ❖ መሪ ትዕዛዝ ምላሽ እንዲሰጥ  የተጠየቀው ፍትህ መምሪያ፣
- ❖ የተከሳሽ ስም፣
- ❖ የጉዳዩ ፍሬ ነገር ባጭሩ፣
- ❖ መሪ ትዕዛዝ የተጠየቀበት ምክንያት፣
- ❖ የዐቃቤ ህጉ ፊርማ ይኖረዋል፡፡

<u>መወያያ ጥያቄ</u>

1. አቶ በልሁ የ "ጣና" የህብረት ስራ ማህበር የሽያጭና ግዥ ኃላፊ ሆኖ ሲሰራ ብር 100000 ብር አጉድሏል ተብሎ ተከሷል፡፡ጉዳዩን የያዘው ዐቃቤ ህግ አቶ በልሁ መከሰስ ያለበት በወ/ህ/ቁጥር 675(1) ወይም 676 (2) ስር ለመሆኑ መወሰን አቅቶታል፡፡ጉዳዩን የያዝከው /የያዝሽው/ ዐቃቤ ህግ አንተ /ች/ ብትሆን/ኚ/ የምርመራ መዝገቡን 20 ገጽ ለበላይ ከመላክ ጋር መሪ ትዕዛዝ በስነ ስርዓት ህጉ መሠረት አዘጋጅ፡፡
2. ወ/ሮ እርብቃ መስከረም 2/2002 ዓ.ም 10 ኩንታል ምርጥ ዘር ከአዲስ አበባ ወደ ባህርዳር ስታጓጉዝ ዱሩቤቴ ከተማ ላይ ትያዛለች፡፡ ምርጥ ዘሩ የያዘው ማዳበሪያ BF 320 የሚል መለያ ቁጥር ተጽፎበታል፡፡ ይህን ድርጊት መፈጸሟ በወ/ሮ እርብቃ የታመነ ሲሆን በምስክርም ተረጋግጧል፡፡ ይሁን እንጅ በወ/ሮ እርብቃ  ላይ ክስ ለመመስረት፣ምርጥ ዘሩ በዚህ መልኩ መያዙ ወንጀል መፈጸምን ያረጋግጣል?  በየትኛው የህግ አንቀጽስ ይሸፈናል? የትኛው ፍ/ቤት ይቀርባል በማለት ጥያቄዎችን መመለስ የቸገረህ በመሆኑ ለበላይ ዐቃቤ ህግ የመሪ ትዕዛዝ ጥያቄ አቅርብበት?

## 5. 4 የአያስከስስም ውሣኔ በሚሰጥባቸው ጉዳዮች ዙሪያ የሚታዩ ችግሮች

የአያስከስስም ውሣኔ የሚሰጥባቸው ሁኔታዎች በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/39 እና 42 ሥር በዝርዝር የተደነገገ ሲሆን በተለይ በቁጥር 42/1/ሀ እና ለ ሥር የተቀመጡት የአያስከስስም ውሣኔ መስጫ ምክንያቶች ግልጽነት የሌላቸው በመሆናቸው ዐቃቤያነ ሕግ በተመሣሣይ ጉዳዮች ላይ የሚሰጧቸው ውሣኔዎች ወጥነት የሌላቸው እና የሚቃረኑ እንዲሆኑ ስለማድረጉ በተግባር ከሚታየው የዕለት ተዕለት አፈጻጸም ለመረዳት ይቻላል፡፡ በቁጥር 42/2/ሀ መሠረት በቂ ማስረጃ የለም የሚለው የማስረጃ ምዘና ግላዊ ወይም ሣብጀክቲቭ መሆኑ እያንዳንዱ ዐቃቤ ሕግ የራሱን የምዘና አቅም በመጠቀም የሚሰጠው ውሣኔ የተለያየ ነው፡፡ ከዚህም የተነሣ አንዱ ዐቃቤ ሕግ ክስ የሚመሰርበትን ጉዳይ ሌላው ዐቃቤ ሕግ በቁጥር 42/1/ሀ/ መሠረት ሲዘጋው ማየት የተለመደ

ተግባር ነው፡፡እንዲሁም በቁጥር 42/1/ለ/ መሠት ተከሣሹ ካልተገኘ ወይም የማይገኝ ከሆነ መዝገቡን ለመዝጋት የተቀመጠው መመዘኛም አሻሚ የሚሆንበት አጋጣሚ እንዳለ ከተሞክሮ ለማወቅ ተችሏል፡፡ ተከሣሹን ለማግኘት የማይቻል እንደሆነ ክሱ አይቀርብም ሲባል እስከ አሁን ባለው አሰራር ዐቃብያነ ሕግ ከፖሊስ የተላከላቸውን የምርመራ መዝገብ በማየት የተከሣሽ ስምና አድራሻ ስለመኖሩ እንዲሁም የዋስትና ፎርም ሞልቶ በዋስ መለቀቁን ከማየት ውጭ ክሱ ከተመሠረተ በኂላ ተከሣሽ በአድራሻው ስለመገኘቱ ምንም ዓይነት ማረጋገጫ መንገድ የላቸውም፡፡ በዚህ ሁኔታ ማስረጃው የተሟላ ነው የሚል እምነት ያለው ዐቃቤ ሕግ ክስ ይመሰረታል፡፡ ተከሣሽ የማይገኝ መሆኑ የሚታወቀውም በፍ/ቤት መጥሪያ ተልኮለት ሣይቀርብ በቀረ ጊዜ ነው፡፡

ከዚህ ፅሁፍ ጋር የተያያዘውን የ42 (1)(ሀ) ውሳኔ ይዘት ለመረዳት እንደሚቻለው በአድራሻ ለፖሊስ የሚፃፍ ሲሆን

- ቀንና ቁጥር ይኖረዋል፣
- የፍትህ ጽ/ቤት መዝገብ ቁጥር፣
- የፓሊስ የምርመራ መዝገብ ቁጥር፣
- ለ---------------ፓሊስ ኮሚሽን /ጽ/ቤት፣
- የክስ ፍሬ ነገር፣
- የተከሳሾች ቃል፣
- የምስክሮች ቃል ባጭሩ፣
- ህጋዊ አስተያየትና ውሳኔ፣የሚሉ ሀሳቦችን የያዘ ሲሆን በመጨረሻም የዐቃቤ ህጉ ፊርማ ይኖርበታል፡፡

<u>ጉዳይ (Case)</u>

1. እነ አቶ ቦጋለ / 4 ሰዎች ) የቀበሌ ተመራጮች በመሆን ሲሠሩ የወ/ሮ ዘርፌ የይዞታ የገጠር መሬት በቆሎ ከተዘራበት በኂላ መንገድ እንዲወጣበት አድርገዋል፡፡የሚል የምርመራ መዝገብ ደርሶሃል፡፡ በጉዳይ ላይ 6 የሰው እና የጽሁፍ ማስረጃ ቀርቧል፡፡ 1ኛ፣2ኛ፣3ኛ ምስክሮት አዲስ መንግድ አልተከፈተም በማለት መስክረዋል፡፡ 4ኛ ምስክር መንገድ በተከሳሾች ሲከፈት አላየሁም ብሏል፡፡ 5ኛ እና 6ኛ ምስክሮቹ በበኩላቸው በወ/ሮ "ዘርፌ" መሬት ላይ ተከሳሾች በክሱ መሠረት መንገድ ሲከፍቱ ተመልክቻለሁ በማለት አስረድቷል፡፡ በሌላ በኩል የቀረበው የሰነድ ማስረጃ ከዚህ ቀበሌ የተገኘ የሰነድ ማስረጃ ሲሆን የተባለው መንገድ በአሁን ተከሳሾች የተከፈተ ሳይሆን / ክስ ከመመስረቱ በፊት በ1960 አንስቶ የነበረ መንገድ ነው በማለት

ያስረዳል፡፡ ከላይ የቀረቡትን ሁኔታዎች ግምት ውስጥ በማስገባት በጉዳዩ ላይ የመሠለህን የውሳኔ ሀሳብ በፅሁፋ አስፍር፡፡

2. አቶ በድሉ የወረዳ ፍርድ ቤት ዳኛ ለሆነው አቶ "ዚኮ" ጉቦ ለመስጠት በማሰብ አቶ "በድሉ " በጉን መግዛቱን በራሱ ግቢ ውስጥ አስሮ ማስቀመጡን አምኗል፡፡ ድርጊቱ በ1/11/2001 ዓ.ም በ--------- በወረዳ ---------- ቀበሌ አስተዳደር ውስጥ የተፈፀመ ነው፡፡በጉዳዩ ላይ ተጣርቶ ለደረሰው የምርመራ መዝገብ የአያስጠይቅም ውሳኔ ስጥ/ጭ/፡፡ድርጊቱ የሚያስጠይቅ ከመሠለህ ክስ መስርት/ች/፡፡

3. ተከሣሾች 1ኛ. አቶ ሙራድ

   2ኛ. አቶ ቢምረው

ተከሣሾች የተከሰሱበት ሰኔ 1 ቀን 2001 ዓ.ም በግምት 11፡00 ሠዓት ሲሆን ወልባ ወረዳ ኩሙ ቀበሌ ባህር ጐጥ ተብሎ ከሚጠራው ስፍራ ከዱር ውስጥ አድፍጠው በመጠበቅ ሟች አቶ ኖህ የተባለው ከወ/ሮ ሚዛን ለቅሶ ቤት ውሎ ወደ መኖሪያ ቤቱ ሲመለስ ተከሣሾች በያዙት ዱላ የሟችን አናት ደጋግመው በመምታት ገድለውታል የሚል ሲሆን ሁለት የሰው ምስክር ቀርበው በተመሣሣይ ቃል 1ኛ ተከሣሽ ከላይ በተጠቀሰው ቀንና ስፍራ ሟችን በያዘው ዱላ ደጋግሞ አናቱን የመታው ሲሆን 2ኛ ተከሣሽ ለመገላገል ሲሞክር ያዩት መሆኑን እንጅ ሟችን ሲደበድበው ያላዩ መሆኑን መስክረዋል፡፡ የቀረበው የሀኪም ማስረጃ ሟች ጭንቅላት ላይ በመፈንከቱ 2 c/m ጥልቀት የሚታይና በዚሁ ምክንያት መሞቱን ያሣያል፡፡ በቀረበው ማስረጃ ላይ ተመርኩዘህ ተገቢ ነው የምትሉትን ውሣኔ በፅሁፍ አስፍር፡፡

## 6. የፍርድ አሰጣጥንና አፃፃፍን ከሌሎች ሰነዶች አፃፃፍ ልዩ የሚዳርጉት ባህርያት

- ሥራው ፍሬነገርንና ማስረጃን ከሕግ ጋር አስማምቶ በሚያሳምን መልኩ መጻፍን የሚጠይቅ መሆኑ፣
- የፍሬ ነገር ማስረጃና ሕግ የውስብስብነት ባህርይ ያላቸው መሆናቸውንና ክርክሮች የሚቀርቡበት በተቃራኒና በተደበላለቀ መልኩ በመሆኑና ከውሳኔ በፊት ስንዴውን ከገለባው የመለየትን እውቀትና ክህሎት ስለሚጠይቅ፣
- አለመግባባቶችን /Disputes) መፍትሔ መስጫ የመጨረሻ መንገድ መሆኑና አሸናፊና ተሸናፊ (ረቺና ተረቺ) የሚታይበት መሆኑ፣
- የክርክሩ ጉዳይ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ለሚመለከታቸው ወገኖች ወይም ባለድርሻዎች በአንፃራዊ መልኩ አሳማኝ (persuasive ) መሆን ስለሚገባው፣

❖ ዳኞች ነፃ የሆነውን ሙያዊ የዳኝነት ሥልጣናቸውን (judicial Discretion) ተጠቅመው የሚያከናውኑት ሥራ በመሆኑና በባህሪይው አነስተኛ ቁጥጥር (Control) ያለበት በመሆኑ፣

❖ ሥራው ቴክኒካል ብቻ ሳይሆን ዕውቀትን፣ክህሎትን፣ጥበብን፣ጥንቃቄን፣መልካም ሥነምግባርንና ታማኝነትን የሚጠይቅ መሆኑ፣

❖ በፍትሐብሔርም ሆነ በወንጀል ጉዳዮች የሚሰጡት የዳኝነት ውሳኔዎች የሰዎችን መሠረታዊ መብቶችና ነፃነቶች የሚመለከቱ መሆኑ፣

❖ ፍርድ የፍ/ቤቶች የመጨረሻ የሥራቸው ውጤት ከመሆኑ አንፃር ጥንቃቄን የሚሻ መሆኑ፣

❖ ፍርድ በይግባኝ እስካልተሻረ ድረስ በማንም ላይ የአስገዳጅነትና ተፈጻሚነት ኃይል ያለው በመሆኑ፣

❖ ሰውኛ ባህርይው */Humanistic Nature /* የጉላ በመሆኑና ሰዎች /ኀብረተሰቡ/ ለፍርድ ካላቸው ከፍተኛ ከበሬታና አመኔታ አንፃር ትልቅ ክብደት ሊሰጠው የሚገባ መሆኑ የሚሉት ዋና ዋነዎቹ ሲሆኑ ከተሳታፊዎችም ተመሳሳይ ነጥቦችን ማሰብና መጨመር ይጠበቃል፡፡ የፍርድ አሰጣጥና አፃፃፍ ተግባር በዳኛው ከፍተኛ የመጨረሻውን ጥንቃቄ እንደሚያስፈልገው ለማመልከት የአሜሪካን የሕግ ባለሙያዎች "የዳኝነት ውሳኔ ስትሰጥም ሆነ ሌላውን ሰው ወክለህ ስትከራከር ራስህን በባለ ጉዳዩ/በተከራካሪው/እግር ተክተህ አስብ" የሚሉት ተጠቃሽ ነው በተለይ ደግሞ ዳኛ በውሳኔው በአብዛኛው ከአንድ በላይ የሆነ ተከራካሪ ወገኖችን መብት አስመልክቶ እልባት የሚሰጥ ከመሆኑ አንፃር ሁሉንም ለማሳመንና ፍትሕ ለመስጠት የቱን ያህል ጥረት ማድረግ እንደሚጠበቅበት ማሰብ ይቻላል፡፡ለዚህም ይመስላል ዳኛ የዳኝነት አካል ወይም የፍትሕ ባለሥልጣን/Court or Justice Officer) ለመባል የሚያበቃው ዋናው ምክንያት::

## 7.የፍርድ አሰጣጥና አፃፃፍ ቅድመ ባህርይና ዓላማው

የፍርድ አሰጣጥና አጻጻፍ ሥራ ብዕርን በወረቀት ላይ በማሳረፍ የሚጀምር ክንውን ሳይሆን መሠረታዊ የሆኑ ቅድመ ፍርድ ሂደቶች አሉት፡፡ፍርድ የሚሰጥበትና የሚጻፍበትም ምክንያት እንደየ ጉዳዩ ዓይነት የሚመዝን ዓላማና ግብ ያለው ነው፡፡

### 7.1 ቅድመ ፍርድ ሂደቶች /ክንውኖች /

ከመሠረታዊ ቅድመ ፍርድ ሂደቶች መካከል የሚከተሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

- ዳኛው ፍርዱን ለማን እንደሚሰጥና እንደሚጽፈው ራሱን መጠየቅ አለበት የፍርዱ ተጠቃሚ ( አንባቢ ) ማን እንደሆነ ማሰብና መለየት ይጠበቅበታል፣
- ፍርድ የሚሰጥበትን ጉዳይ ፍሬ ነገርና ማስረጃ ጠንቅቆ ማጥናትና መሠረታዊ ግንዛቤ መያዝ አከራካሪውን ጉዳይ መለየትና በተገቢው መግለጽ መቻል፡፡
- በአከራካሪው ጉዳይ ላይ ተከራካሪ ወገኖች የሚሉትን አቤቱታቸውን ሁሉ የቃል ክርክራቸውን ጭምር መስማት፤ ምክንያቱም የሕግ ሊቃውንቱ እንደሚሉት "ጽሑፍ የቀረበን ቃል ሕይወት ባለው መልኩ ማስረዳት የሚቻለውና የባለ ጉዳዩን ችግሮች በተግባር መረዳት የሚቻለው በቃል ጭምር ሲሰማ ነው"፡፡ ባለጉዳዩም በፍትሕ ሂደቱ ሥርዓት ላይ አመኔታ እንዲኖረው ይረዳል፡፡ ሐኪም ለበሽተኛው መድኃኒት የሚያዝለት የሚሰማውን ስሜት ሁሉ በቃል ሰምቶ መርምሮ እንደመሆኑ ዳኞችም ፍትሕ ቸግሮት /የፍትህ በሽተኛ/ሆኖ የቀረበን ባለጉዳይ ከጽሑፍ አቤቱታው ባሻገር ( ጽሑፉ በሌላ ሰው የተጻፈም ሊሆን መቻሉ ግምት ይወስድበታል) አቤቱታውን በቃል መስማቱና ማከራከሩ ለፍርድ አሰጣጥ ጠቀሜታው ቀላል አይሆንም፡፡
  - የታመኑትንና የተካዱትን ፍሬ ነገሮች መለየትና ጉዳዩን መተንተን አስፈላጊ ነው፣
  - የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎችን ክርክሮች መርምሮ ከዋናው ክርክር ሂደት በፊት ውሳኔ መስጠት የማይታለፍ ተግባር መሆኑ፣
  - ማሰረጃዎችን በተመለከተ የሚሰጡትን ትዕዛዞች /የማረጃ አግባብነትና ተቀባይነትን የተጨማሪ ማስረጃ አስፈላጊነት) በጥንቃቄና በወቅቱ መስጠት፣
  - ለጉዳዩ አግባብነት ያለውን ሕግ መለየትና ማጥናት፣
  - የዳኝነት ውሳኔው የሚያሳምን መሆኑን መመዘንና ወደ ፍርድ ሥራ መሄድ ናቸው፡፡

7.2 የፍርድ መስጠትና መፃፍ ዓላማና ግቦች

የፍርድ መስጠትና የፍርድ መፃፍ የራሱ ዓላማና ግብ አለው ከእነዚህም መካከል የሚተሉት ይገኙበታል፡፡

- ለመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤቶች የፍሬ ነገር የማስረጃና የሕግ ክርክሮችን መርምሮ የፍ/ቤቱን መልስ /የዳኝነት ውሳኔ መፍትሔ/ መግለጫ መገናኛ መንገድ ነው፡፡ለይግባኝ ፍ/ቤቶችም ይግባኝ የቀረበበትን የስህተት ነጥቦች አሰመልክቶ ለማረም የሕግ ትንተና /ምክንያት / የሚቀርብበት መንገድ ነው፣

- ለተከራካሪ ወገኖች አለመግባባት (ክርክር) መፍትሔ መስጫና ውሳኔውንም ለማስፈፀም እንዲችሉ ወይም የይግባኝ መብታቸውን ለመጠቀም እንዲችሉ በምን ምክንያት ረቺና ተረቺ እንደሆኑ ፍ/ቤቱ የሚገልጽበትና የሚያሳምንበት መንገድ ነው፡፡
- የፍ/ቤቱን መደምደሚያ ማሳወቂያ መንገድ ነው፡፡
- ለምርምር፣ለማስተማሪያና የትችት ጽሑፎችን ለማዘጋጀት ሊጠቅም ይችላል፣
- አዳዲስ ሕጐችን ለማውጣትና ነባር ሕጐችን ለማሻሻል የሕጉን አተገባበር ከነባራዊ የኅብረተሰቡ ሕይወት ጋር የሚሄድ መሆኑን ለመገምገምና ለመረዳት ይጠቅማል፡፡
- በፍ/ቤቶች ሕግን ለመተርጐምና በፍትህ ሥርዓቱ የድርሻቸውን ግዴታ ለመወጣት የቅልጥፍናቸውንና የተገማችነታቸው መለኪያ በመሆንም ሊያገለግል ይችላል፡፡
- የሰበር ችሎት ውሳኔ ከሆነ ደግሞ የሕግ አተረጓጐምን ዘዴ ተመሳሳይነት ለማስጠበቅ እንደሕግ ሆኖ ገዥ በመሆን ሊያገለግል ይችላል፡፡
- ለሕግ ሳይንስና ሙያ ዕድገት /Development of Jurisprudence and the Profession/ ፍርዶች አስተዋጽኦ አላቸው
- የሕገ መግሥቱንና የዲሞክራሲያዊ የበላይ መርሕነትንና የሕግ የበላይነትን /

/Supremacy of Constitution and Rule of Law/ ማስጠበቅ የሚቻለውም በዳኝነት ፍርድ አሰጣጥ ነው፡፡ እነዚህ ከላይ የተገለጹት የፍርድ አሰጣጥና መጻፍ ዓላማዎችና ግባች እንደየ ጉዳዩ ዓይነትና ባህርይ የሚንጸባረቁ ሲሆን ፍርድ ቤት ሕግን ለመተርጐም ከተሰጠው ሕገመንግስታዊ ሥልጣንና ኃላፊነት የሚመነጩ ናቸው፡፡ የፍርድ ቤቶች የሥልጣናቸውና ኃላፊነታቸው ማስፈጸሚያ መሳሪያቸውም በዳኝነት ሂደት በዳኞች የሚጻፉት ፍርዶች ወይም ትዕዛዞች መሆናቸው የተሰወረ ወይም ምስጢር አይደለም፡፡

8 **የዳኝነት ውሳኔ አጻጻፍ ዘይቤን የሚወስኑ ጉዳዮች**(Factors Influencing Judicial Writings )

- ፍ/ቤቶች በሀገሪቱ ሕገመንግሥትና በሌሎች ኅጎች በተሰጣቸው ሥልጣን መሠረት ህግን መተርጐም መቻላቸው፡፡
- ዳኞች ስለሚኖራቸው ሚናና ሥልጣናቸው ያላቸው እይታ፣
- ኅብረተሰቡ ስለ ዳኞች ሚና ያለው ግምትና ሚዛን፣የዳኞች የሙያና የትምህርት ደረጃ እንዲሁም ያላቸው የዳኝነት ልምድ፣
- የዳኞች የዳኝነት ውሳኔ አሰጣጥና አጻጻፍ ክህሎትና ጥበብ፣
- የዳኞች ነፃነት ከፖለቲካ ወገንተኝነት፣ ከሙስና፣ ከዘር እና ከመሳሰሉት ወገንተኝነት ነፃ መሆን /Impartiality/

- አንድ ሀገር የምትከተለው የሕግ ሥርዓት /Legal Tradition / ባህርይ፣
- የአገሪቷ የሕግ ትምህርት ሥርዓት በተግባርና ክህሎት ነክ ትምህርቶች ላይ ትኩረት የሰጠ መሆንና አለመሆን፣
- ዳኞች ዳኝነትን በሙሉ ፍላጐትና ፍቅር ቋሚና ዘላቂ ሙያ አድርገው ለመቆየት ያላቸው ዝንባሌ፣ ቁርጠኝነትና መስዋዕትነት፣
- የፍ/ቤቶች ተቋማዊ፣ አስተዳደራዊ የገንዘብና የቁሳቁስ ጥንካሬና ብቃት በተዘዋዋሪ አስተዋጽኦ ይኖራቸዋል፡፡ ተሳታፊዎችም ሌሎች ምክንያቶችን መጨመር ይችላሉ፡፡

## 9. <u>የዳኝነት ውሳኔ አፃፃፍ መመዘኛዎች</u>

### 9.1 <u>የዳኝነት ዓይነቶች</u>፡-

ፍ/ቤቶች በሚመለከቷቸው ጉዳዮች ላይ የተለያዩ ዓይነት ውጤቶችን ይጽፋል፡፡ እነዚህ ውጤቶች ጊዜያዊ /Interlocutory/ እና የመጨረሻ /Final / ተብለው ሊከፋፈሉ ይችላሉ፡፡ ጊዜያዊ ትዕዛዞቹ የመጨረሻ ውሳኔውን /ፍርዱን / ለማመቻቸት የሚያግዙ ናቸው፡፡ <u>ለምሳሌ</u> ንብረት እንዳይሸጥ ማገድ በራሱ ውጤት ያለው ሳይሆን የመጨረሻ ፍርዱን ለማስፈጸም የሚረዳ ነው፡፡ የመጨረሻ ፍርድ ግን የፍርድ ባለዕዳነትንና ባለመብትነትን የሚያስከትል በመሆኑ በፍትሐብሔርም ሆነ በወንጀል ጉዳይ እንደ አግቦብነቱ መፈጸምን ወይም ይግባኝ መጠየቅን ውጤት ያስከትላል፡፡ በኢትዮጵያ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ መሠረት ሦስት ዓይነት የዳኝነት ዓይነቶች አሉ፡፡እነዚህም ውሳኔ /Decree/ ትዕዛዝ /Order/ እና ፍርድ /Judgment/ ተብለው ተቀምጠዋል፡፡ እንዲሁም የሥነ ሥርዓት ሕጉ ትርጓሜ ያልሰጠውና በዝርዝር ድንጋጌዎች አተገባበርም ላይ መቼ አግባብነት እንደሚኖረው ያልተገለጸ 'ብይን' የሚባል የትዕዛዝ ዓይነት እንዳለ ያመለክታል፡፡

በልምድም /Practice/ አንዳንድ ጊዜ 'በትዕዛዝ' ሊወጡ የሚገባቸው ጉዳዮች 'ብይን' በሚል ሲወጡ ይታያሉ፡፡ ስለዚህ ከሕጉና ከልምዱ አንጻር ሲታይ በአሁኑ ጊዜ የኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች ዳኝነት የሚሰጡባቸው መንገዶች ትዕዛዝ፣ብይን፣ውሳኔ እና ፍርድ ናቸው፡፡ ከልምዱ ሲታይ ፍርድና ውሳኔ በተለዋዋጭነት በሥራ ላይ ሲውሉ የሚታይ ሲሆን ውሳኔ ግን ተፈጻሚው የፍርድ የመጨረሻው አካል መሆኑን ለመረዳት ይቻላል፡፡

- ብይንና ትዕዛዝ ጊዜያዊ አገልግሎት ያለው ዳኝነት የሚሰጥባቸው ስያሜዎች /አርዕስት/ ናቸው፡፡
- የትዕዛዝ ውሳኔና ፍርድ ትርጉሞች በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ አንቀጽ 3 የተመለከተ ሲሆን በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕጉ ግን ስለትርጉማቸው

ሆነ ስለአገልግሎታቸው የተገለጸ ነገር የለም፡፡የትዕዛዝና የውሳኔ ልዩነት በግልጽ አልተመለከተም፡፡ይህም በመሆኑ ይመስላል አንዳንድ ጊዜ ፍ/ቤቶች በማቀያየር ሲጠቀሙባቸው የሚታየው፡፡

- በኢትዮጵያ የፍ/ሥ/ሥ/ሕግ መሠረት የሚሰጡት ትዕዛዞች በአምስት ክፍለን ልናያቸው እንችላለን፡፡

ሀ. ክስን የመሰረዝ ባህሪ ያለው በመሆኑ ይግባኝ የሚባልበት ትዕዛዝ፣**ለምሳሌ** ክሱ በይርጋ ወይም የክስ ምክንያት የለውም ተብሎ በትዕዛዝ ቢዘጋ /ቢሠረዝ ወይም ይግባኙ መልስ ሰጭን አያስቀርብም ተበሎ ቢዘጋ፣

ለ. ክሱን የመሰረዝ ውጤት የሌለው ግን ይግባኝ የሚባልበት ትዕዛዝ **ለምሳሌ** ንብረት ከእጅ እንዲወጣ የሚሰጥ ትዕዛዝ ወይም የእሥራት ትዕዛዝ ሲሰጥ /አንቀጽ 320/4)፣

ሐ. ክሱ ተከፍቶ እስኪጠናቀቅ ድረስ በማናቸውም ጊዜ ቢሰጥም ፍርድ ከተሰጠ በኋላ ለይግባኝ ምክንያት ሊሆን የሚችል ትዕዛዝ አንቀጽ 320 (3)፣ ለምሳሌ የይርጋን መቃወሚያ ባለመቀበል በሚሰጥ ትዕዛዝ፣

መ. በከፊል የይግባኝ ምክንያት ሊሆን የሚችል ትዕዛዝ፣ ለምሳሌ በአንቀጽ 324 መሠረት የሚሰጥ ትዕዛዝ፣

ሠ. ፈጽሞ ይግባኝ ሊባልበት ወይም ለይግባኝ ምክንያት ሊሆን የማይችል ትዕዛዝ በአንቀጽ 6/4 መሠረት ዳኝነቱ እንደገና ሊታይ ይገባዋል ወይም አይገባውም ሲል ፍ/ቤቱ በሚሰጠው ውሳኔ ላይ ይግባኝ ለማቅረብ አይችልም፡፡ ለምሳሌ፡- የቀጠሮ መለወጫ ትዕዛዝ መስጠት ይመለከታል፣

9.2 የመጨረሻ ውሣኔዎች ይዘት፡- በመጀመሪያ ደረጃ በሚታዩ ጉዳዮች ላይ የሚሰጥ ውሳኔ (ፍርድ) የሚከተሉትን ነጥቦች ይሸፍናል፡፡

1. የጉዳዩ ባህርይ /Nature of the Action/ ከሳሽ/ተከሳሽ የሚጠይቁት መፍትሔ ዓይነትና

የተከራካሪዎቹ ሚና የጉዳዩ አቀራረብ ታሪክ ወደ ፍ/ቤት እንዴትና በማን እንደረበ የሚናገር ክፍል ነው፡፡

2. ዝርዝር ፍሬ ነገሮች /Facts/ ከሳሽና ተከሳሽ ያቀረቧቸው ዝርዝር ፍሬ ነገርና የማስረጃ

ክርክሮችና ዓይነቶቻቸው ለጭብጡ አመሠራረትና ለጉዳዩ አመራርና አወሳሰን የሚጠቅሙትን አግባብነት የክርክሩ ነጥብ ከፍ/ቤቱ ምላሽ የሚፈልገውን ጉዳይ የሚይዝ ነው፡፡

3. ጭብጥ /Issue/ ከሳሽና ተከሳሽ ያልተግባቡት የክርክሩ ነጥብ ከፍ/ቤቱ ምላሽ የሚፈልገውን ጉዳይ የሚይዝ ነው፡፡

4. ሕግና አስተያየት /Law and Reasoning/ ፍ/ቤቱ ለክርክሩ መደምደሚያ የሚጠቀምበት የሕግ ድጋፍና ምክንያት ነው፡፡

5. ውሳኔ /Disposition or Conclusion/ በጉዳዩ ረቺውና ተረውን ለይቶ ተፈጻሚ የሚሆነውን

የፍ/ቤቱን ድምዳሜ /ማጠቃለያ የሚይዘው ክፍል ነው፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ በይግባኝና በሰበር የሚታዩ ጉዳዮች ላይ የሚሰጥ ፍርድ ብዙም ልዩነት በሌለው ሁኔታ መልኩ የሚከተሉትን ነጥቦች ይሸፍናል፡፡

1. የጉዳዩ ባህሪይ /Nature of the Action/
2. ጭብጦች /General Statement of Issues/
3. ፍሬ ነገሮች /ከመጀመሪያው ደረጃ ፍ/ቤት በጣም ባጠረ መልኩ የሚጻፉ፣
4. ይግባኝ /ሰበር የቀረበባቸው ስህተቶች እና ስለ ስህተቶቹ የተሰጠው አስተያየት /Errors and Determination/
5. ውሳኔ /Disposition/

እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት የሁሉም ደረጃዎች ፍ/ቤቶች የመጨረሻ ውሳኔዎች ይዘት ነጥቦች እንደመሠረታዊ የፍርድ አፃፃፍ ቅደም ተከተል /basic steps/ ደንቦች የሚወስዱበት ሁኔታም ይወሰዳሉ፡፡

9.3 የፍርድ አፃፃፍ መመዘኛዎች

- በሁለቱም የህግ ስርዐቶች ውስጥ የሚከተሉት መመዘኛዎች ጥሩ የዳኝነት አፃፃፍ ሊይዛቸው የሚገቡ ነጥቦች ናቸው፡፡

1. **የይዘት መሟላት**፡- ከላይ በቁጥር 6.2 ክፍል ሥር የተጠቀሱት አምስት የፍርድ ይዘቶች በቅደም ተከተላቸው መሟላት አለባቸው፡፡ እንዲሁም ፍ/ቤቱ ባስቀመጣቸው ጭብጦች ላይ በሙሉ ውሳኔውን ማሳረፍ አለበት፡፡ ሳይመለስ የቀረ ነጥብ /ጭብጥ/ ፍርዱን ጉደሎ ያደርገዋል፡፡
2. **የውሳኔ አስተያየት ቅደም ተከተል፡-** መደምደሚያ ላይ ለመድረስ ፍ/ቤቱ ያነሳቸውን ምክንያቶች /Arguments/ የደረጃ በደረጃ ቅደም ተከተል አካሄድ ሊኖራቸው ይገባል፡፡

3. **የውሳኔ ሀሳብ ምጣኔ** /Scope of the Judgment / ፍ/ቤቱ አስፈላጊ ከሆነው በላይ መወሰን የለበትም የቀረበለትን ክርክር ከመፍታት የዘለለ ሌላ ሐተታ አስተያየት ሊሰጥ አይገባም፡፡ ክርክሩን ከፈታ በጉዳዩ ዙሪያ ያሉ ነገሮችን ከዚያም አልፎ ከጉዳዩ በመውጣት የዳኛን የግል ስሜትና ሃሳብ በመጨመር መተንተንና መፃፍ አያፈልገውም፡፡

4. **የፍሬ ነገርና የሕግ አስተያየት ምጣኔ፡-** የሚጠቀሱት የሕግ ድንጋጌዎች ለጉዳዩ ቀጥተኛ አግባብነት /Direct Relevancy/ ሊኖራቸው ይገባል፡፡ አንድ አንቀጽ ጉዳዩን በቀጥታ የሚሸፍነው ከሆነ ተጨማሪ መጥቀስ አስፈላጊ አይደለም፡፡ እንዲሁም ለውሳኔው የማያገለግሉትን የተከራካሪ ወገኖችን አላስፈላጊ የክርክር ዝርዝር መፃፍ አያስፈልግም፡፡

5. **ወገንተኛ ድምፅን ማስወገድ** /Using Neutral Tone / ዳኛው ራሱን የከሳሽ ወይም የተከሳሽ ድምጽ የሚያስመስለው አገላለጽ መጠቀም የለበትም፡፡ የአንደኛቸው ክርክር ላይ ብቻ ትንተናውን ከሰጠ ሚዛናዊነት ይጉድለዋል፡፡ከእነዚህ መመዘኛዎች በተጨማሪ ከዚህ በታች በፍርድ አፃፃፍ ሁኔታ ሥር (ቁጥር 13) የተዘረዘሩትን ነጥቦች ይመለከቷል፡፡

## 10. የፍርድ አሰጣጥና አፃፃፍ ቅደም ተከተል

የፍርድ አሰጣጥ እና የፍርድ አፃፃፍ አንድነታቸውና ግንኙነታቸው ምንድን ነው? የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ የሚሰጥ ዳኛ በውሳኔ አሰጣጥና አፃፃፍ ሥራው ሦስት ቅደም ተከተል ያላቸውን ሥራዎች ማከናወን ይጠበቅበታል፡፡ እነዚህም (1) ወደ ጽሑፍ ሥራ ከመግባቱ በፊት ክርክሩን ወይም አለመግባባቱን መርምሮ የጉዳዩን መሠረታዊ ግንዛቤ ይዞ አግባብነት ያለውን ሕግ ፈልጐ መደምደሚያ ላይ መድረስ የመጀመሪያው ደረጃ ተግባሩ ነው፡፡

(2) ሁለተኛው ደረጃ ውሳኔውን ለተከራካሪ ወገኖች ወይም ለባለድርሻዎች ማሳወቂያ/ማገናኛ ፎርምን/ መምረጥ ነው፡፡ ይኸውም በቃል ወይስ በጽሑፍ ይነገራል በዳኛው ወይስ በሌላ ወገን በማን ይነገራል የሚለውን ጉዳይ የሚመለከት ነው፡፡ አንዳንድ አገሮች ቀለል ያለ ጉዳዮችን ውሳኔ በቃል የሚወስኑና የሚያሳውቁ ሲሆን የጽሑፍን ውሳኔ ለከባድና ለተወሳሰቡ ጉዳዮች ይጠቀማሉ፡፡በኢትዮጵያ የሕግ ሥርዓት ከ1930ዎቹ ዓመታት ጀምሮ በተለይም ቢያንስ በ1958 የፍ/ብ/ሥ/ሕጉ እና የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕጉ ከወጣበት 1954 ዓ.ም ጀምሮ ፍርድን በጽሑፍ መልክ መንገርና በግልጽ ችሎት መስጠት አስገዳጅና የተከራካሪዎች መብት መሆኑ የታወቀ ጉዳይ ነው፡፡

**በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕጉ አንቀጽ 180-191 እና የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕጉ አንቀጽ 149 ፍርድ በጽሑፍ እንዲነገር ግድ ይላሉ፡፡**

ነገር ግን በአንዳንድ ፍ/ቤቶች ይባስ ብሎ በይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ያውም በወንጀል ይግባኝ ጉዳይ ይግባኝ አቅርበው እሥረኛ በጽሑፍ ያቀረበውን ይግባኝ አቤቱታ ቀርቦ በቃሉ እንዲያስረዳ ሳይጠሩና ሳይሰሙት የዐቃቤ ሕግንም አስተያየት ሳይጠይቁ የጽሑፍ አቤቱታውን ብቻ ፍ/ቤቱ ተመልክቶ ባለመቀበል ከወሰነ በኂላ በስማበለው በማረሚያ ቤት ጉዳይ ተከታታይ በኩል በመልዕክተኛ የሚነገርበት ሁኔታ አለ፡፡ ይህ የዳኝነት አሠራር ከፍርድ አሰጣጥ ዓላማና ተግባር እንዲሁም ከፍ/ቤቶች የፍትሕ መድረክ ከመሆን አንፃር በእጅጉ የሚቃረንና ሊታረም የሚገባው መሆኑን ፀሐፊው በሙያ ተግባሩ ያምናል፡፡

አሠራሩን ተቀባይነት ያለው ለማስመሰል የሚቀርብ እንደ የይግባኝ ጉዳዮች መብዛት፣ ይግባኙ ዋጋ የሌለው መሆን፣የማረሚያ ቤቶች እርቀትና ድካም የመሳሰሉት በምንም መመዘኛ ቢሆን ሚዛን የሚደፉና የመሰማትንና በግልጽ ችሎት ፍርድ የማግኘትን መብት የሚያስቀሩ አይሆኑም፡፡ የዳኝነት ሂደት ሕይወት ባለው መልኩ /Interactive and lively/ መከናወን ያለበት ጭምር በመሆኑ ይመስላል በግልጽ ችሎት መዳኘት /Public Hearing/ እንደ መሠረታዊ መብት እውቅና ማግኘቱ፡፡ስለዚህ ይህ ሁለተኛው የዳኝነት ውሳኔን የመገናኛ የመግለጫ መንገድ/Form of Communicating the Judicial Decision/ ሊዘነጋ የማይገባውና መፈፀም ያለበት ነው፡፡

(3) ሶስተኛው ደረጃ ከሁለተኛው ደረጃ የፎርም ምርጫ የሚከተል ሲሆን ይኸውም ፍርዱን የውሳኔ ይዘትን ቅደም ተከተል ደንቦች ጠብቆ መፃፍን ወይም ወደ ጽሑፍ መለወጥ የሚመለከት ሥራ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር የመጀመሪያው ደረጃ ውሳኔ /ፍርድ /አሰጣጥ ተብሎ ሲጠራ ሶስተኛው ደረጃ ደግሞ የፍርድ አፃፃፍ ሥራ ተብሎ ይታወቃል፡፡ በእርግጥ ሶስቱም ደረጃዎች የተለያዩና የማይገናኙ ሥራዎች ሳይሆኑ የተያያዙና የማይነጣጠሉ ናቸው፡፡

## 11. የይግባኝ እና ሰበር ውሳኔዎች ባህርይ

### ሀ. አጠቃላይ ባህሪይና የውሳኔ ይዘት

- በአብዛኛው በሁለቱም የሕግ ሥርዓቶች ሁለት ዓይነት የይግባኝ ውሳኔ ሰጪ ፍ/ቤቶች ያሉ ሲሆን እነሱም መካከለኛ /Intermediary/ እና የመጨረሻ /Last Resort / ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤቶች በመባል ይታወቃሉ፡፡ ለምሳሌ በኢትዮጵያ የአሁኑ የሕግ ሥርዓት የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤትና በክልል የዞን/ከፍተኛ ፍ/ቤት መካከለኛ ይግባኝ ሰሚዎች ሲሆኑ የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤትና የክልል ጠቅላይ ፍ/ቤቶች የመጨረሻ ይግባኝ ውሳኔ

ሰጪዎች ናቸው። /አዋጅ ቁጥር 25/1988 እና የክልል ፍ/ቤቶችን ማቋቋሚያ አዋጆችን ይመለከታል/።

- የይግባኝ ፍርዶች የበታች ፍ/ቤትን ውሳኔ ስህተት /የፍሬ ነገርና የሕግ ስህተትን የማረም ውጤት ያላቸው ሲሆን ለፍትሕ አሰጣጥ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም በተከራካሪ ወገኖች ባልተነሱ ነጥቦችም ላይ ውሳኔ ሊሰጡ የሚችሉበት አጋጣሚዎች ይኖራል።
- በኢትዮጵያ የሥነ ሥርዓት ሕጎች መሠረት /የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ አንቀጽ 341-348 ይመለከታል/ 5 ዓይነት ውጤት ያላቸው ሲሆን እነዚህም ይግባኝ የተባለበት ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ ሙሉ በሙሉ ማጽደቅ / Affirming /፣የመሻር / Reversal/፣ የማሻሻል /Vary/ ይግባኙን የመሠረዝ /Dismissal/ ወይም ጉዳዩ እንደገና እንዲታይ የመመለስ /Remand/ ናቸው።
- የይግባኝ ውሳኔዎች በአብዛኛው ከአንድ በላይ ዳኞች የሚሰጡ በመሆናቸው የፀሐፊ ዳኛ እና የውሳኔው ሌሎች ተሳታፊ ዳኞች /Collegial Judges/ ግንኙነት የሚታይበት ነው። በመሆኑም ውሳኔዎቹ በአብላጫ ድምጽ (Majority Decision) እና በሃሳብ ልዩነት (Minority Opinion ) ሊሰጡ ይችላሉ።

- የሰበር ውሳኔዎች የሚሰጡት የሕግ ስህተትን አስመልክቶ ከመሆኑ በስተቀር የይግባኝ ውሳኔዎችን ባህሪይ ይጋራሉ። ነገር ግን ውሳኔዎቹ አስገዳጅነት የሚኖራቸው ሊሆን ስለሚችልና በሕግ ስህተት ላይ ትኩረት የሚያደርጉ በመሆናቸው የዳኞች ቁጥር ከይግባኝ ውሳኔ ስጭ ችሎቶች ሲበልጥና የክርክሩም ይዘት ውስብስብነት ሲጨምር ይሰተዋላል።

ለ. የቡድን /የጋራ/ ዳኝነት ሥራ ኃላፊነት /Responsibilities of Collegiality/

ከዚህ በታች የዘረዘሩት ነጥቦች ከአንድ በላይ ቁጥር ባላቸው ዳኞች ውሳኔ በሚሰጡበት ጊዜ ጠቃሚዎች ናቸው። በመሆኑም ትኩረት ሊሰጣቸው ይገባል።

- በሙያዊ ጥረትና ታማኝነት መሥራት፣
- በትህትና በትዕግስትና በሥነ ምግባር መሥራት፣
- በጉዳዮች አመራርና ውሳኔ አሰጣጥ ሁሉ በሙሉ ፍላጎት ማሳተፍ፣
- ከቃል ክርክር /ውይይት/ በፊት ጉዳዩን ማንበብና መረዳት፣
- የአንድ ዳኛ ድምፀት ጽሑፉና ዝንባሌ /በሽታ/ One Judge Syndrome/ ማስወገድ፣
- ለንደኛ ሥራ /ሃሳብ ቦታ መስጠት፣

- ከጉዳዩ ባሻገር የግል አለመግባባት ነገር ቢኖር በታማኝነትና በቅንነት ግልጽ ማድረግ፣ ምክንያቱም የግል አለመግባባት በውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ሊኖረው ስለማችል ነው፣
- ከይሉኝታና ግዴለሽነት በፀዳ ሁኔታ መወያየትና ካስፈለገም አሳድሮ ወይም ቀጠሮ ለውጦ ማጥናትና ከስምምነት ላይ መድረስ፣
- የጥላቻ ወይም የንቀት ቃል ወይም የስድብ ቃል እና የመሳሰሉትን አላስፈላጊ ቀላትን በውይይት ጊዜ አለመጠቀም፣
- መደማመጥና ለሌላው ሃሳብ ክፍት/ቀና አእምሮ መያዝ /Be Open Minded Innocent/ ብዙ ከመናገር ብዙ ማድመጥ እንዲሉ፣
- በተቻለ መጠን የተበታተኑ ሀሳቦችን ወይም ዕርስ በርስ የሚቃረኑ የሚመስሉ ሀሳቦችን በማስወገድ ውሳኔው ወጥነት እንዲኖረው ማድረግ፡፡

## 12. ፍርድ እንዴትና መቼ ይሰጣል?

"Justice delayed is Justice Denied" "የዘገየ ፍትሕ እንደተነፈገ ፍትሕ ይቆጠራል"፡፡

ይህ ጥቅስ በአጭር ቃል የሚነግረን ፍርድ ሳይዘገይ በተፋጠነ ሁኔታና ጊዜ መስጠት እንደሚገባው ስምምነት የተደረሰበትና በጥቅስ መልክ እስከመነገርም የደረሰ ሀሳብ መሆኑን ነው፡፡ ይሁንና በተቃራኒው ደግሞ የተቻኮለ ፍትሕ እንደተሰበረ ፍትሕ ይቆጠራል የሚል አባባልም አለ፡፡

እነዚህ መርሆዎች የሚያስጨብጡት መሠረታዊ ቁም ነገር ፍትሕ ወይም ፍርድ ሳይዘገይ በተፋጠነ ሂደት መስጠት እንደሚገባው ይሁንናም በፍጥነት ሥም ደግሞ የክርክሩን ሂደት ሳይጠናቀቅና ጉዳዩ ለፍርድ ሳይበስል ወይም ብዙ ጉዳዮች ለመዝጋትና ለመወሰን ተብሎ ፍትሕ መስዋዕት ሆኖ በችኮላ መሰጠት እንደሌለበትና የማመጣጠን ዘዴን እንደሚጠይቅ ነው፡፡ የተፋጠነ ፍትሕ መስጠትን በምንመለከትበት ጊዜ ውጤታማነትንና ቅልጥፍናን (Effectiveness and Efficiency) አብሮ ማስኬድ የሚጠይቅ ስራ ነው፡፡የፍርድን አሰጣጥ ሁኔታና ጊዜ ከሚወስኑት ብዙ ነገሮች መካከል የክርክር አቅራቢዎቹ ክርክር አቀራረብና የዳኞች እውቀትና ክህሎት ዋናውን ድርሻ የሚወስዱ ናቸው፡፡ ለማንኛውም የፍርድ ቃል መሠረቱ አንድ አቤቱታ አቅራቢ የሚያቀርበው አቤቱታ ነው የአቤቱታው መቅረብ የክርክሩ መነሻ ሲሆን በቀረበው አቤቱታ ተከራካሪ ወገን ካለ ተጠርቶ ክርክሩን ያቀርባል ፍ/ቤት በሥነ ሥርዓት ሕጉ መሠረት እንደአግባብነቱ አከራክሮ በመጨረሻ ለጉዳዩ እልባት የሚሰጠው ፍርድ በመስጠት ነው፡፡

ፍርድ ዋናው የዳኛ የመጨረሻው ሥራው ሲሆን አንድ ጉዳይ ያለ ፍርድ እየተቀጠረ ጊዜ ካስቆጠረ በዚያ ጉዳይ ላይ ዳኛው ሥራ እንዳልሠራ ተከራካሪ ባለጉዳዮችም የፍ/ቤት ውሏቸው በከንቱ ጊዜ ማጥፋት እንደሆነ ያስቆጥረዋል፡፡ ስለዚህ ፍርድ ጥሩም ይሁን መጥፎ የግድ በወቅቱ /በተፋጠነ ሁኔታ/መስጠት አለበት፡፡ከፍርድ መስጫ ጊዜ ጋር በተያያዘ መልኩ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 180 "የቀረበው ክርክር ከተሰማ በኋላ ፍ/ቤቱ ነገሩን እንዳለቀ ወዲያውኑ ወይም በአጭር ቀን ቀጠሮ በሚወስነው ጊዜ በግልጽ ችሎት ፍርድ መስጠት አለበት" በማለት ተደንግጓል፡፡የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕጉ አንቀጽ 141 እና 149 ድንጋጌዎችም ከፍትሐብሔር ጋር ተመሳሳይ አንድምታ አላቸው፡፡

ይህም የሚያስረዳው ፍርድ በክርክሩ ባህሪይ ምክንያት የክርክሩ መሰማት ሂደት ከዓቅም በላይ ሆኖ ካላዘገየው በስተቀር በተፋጠነ ሁኔታ መሰጠት እንዳለበት ፍርድ የሚሰጠውም በግልጽ ችሎት መሆኑን ነው፡፡ ከፍርድ በፊት ክርክሩን መስማት የፍ/ቤት /የዳኛ/ ግዴታም እንደሆነ ያስረዳል የመጀመሪያ ደረጃም ሆነ የይግባኝ አቤቱታን/ ክርክርን ሳይሰሙ ወደ ውሳኔ መስጠት ተግባር ከተሄደ ግን የውሳኔ አሰጣጥ ቅድመ ሁኔታዎችንና ደንቦችን ያላገናዘበ ይመስላል፡፡ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገመንግስት አንቀጽ 20 እንደተደነገገውም የተከሰሱ ሰዎች ክስ ከቀረበባቸው በኋላ ተገቢ በሆነ አጭር ጊዜ ውስጥ መደበኛ ፍርድ ቤት ለሕዝብ ግልጽ በሆነ ችሎት የመሰማት መብት አላቸው፡፡ክርክሩ በሚታይበት ፍርድ ቤት በተሰጣቸው ትዕዛዝ ወይም ፍርድ ላይም ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ይግባኝ የማቅረብ መብት እንዳላቸውም ተደንግጓል፡፡ በመሆኑም ክርክር ሳይሰማ የተቻኮለ ፍርድ ከተሰጠ ውጤቱ እንደዘገየ ፍርድ ፍትህን መንፈግና የመከራከር መብትንም የሚያጣብብና በሌሎች መብቶቻቸውም ላይ አሉታዊ ተጽእኖ የሚኖረው ይሆናል፡፡ በመሆኑም ፍጥነትና ችኮላ በዳኝነት መድረክ ልዩነት ያላቸው መሆኑን ሊሰመርበት የሚገባ ጉዳይ ነው፡፡

## 13. በፍርድ አሰጣጡ ሁኔታና ጊዜ ላይ ተጽእኖ ያላቸው ነገሮች

1. የአቤቱታ አዘጋጃጀት /አፃፃፍ/ የሥነ ሥርዓት ሕጐችን በጠበቀ መልኩ አለመሆንና አግባብነት ያላቸውና የሌላቸው ነጥቦች ተደባልቀው መቅረባቸው፣
2. ተከራካሪ ወገኖች በሕግ ባለሙያ አለመታገዛቸውና አቤቱታቸውን በባለሙያ አስጽፈው አለመቅረብ እና የኀብረተሰቡ ለባለሙያ ያለው ግምትና ባህል ያደገ አለመሆን፡፡
3. ሥነሥርዓቱን ጠብቆ የሚጽፍ የባለሙያ እና የሕግ አገልግሎት ( Legal Service) አቅርቦት ወይም ተደራሽነት በተለይም ከዋና ከተሞች ውጪ እጅግ አነስተኛ መሆንና አንዳንደ ጊዜ ጭራሽም አለመኖር፣
4. የፍ/ቤት ጉዳዮች ብዛትና የዳኞች ቁጥር ከጉዳዮች ብዛት ጋር አለመጣጣም ሲኖር፣

5. የጭብጥ አመሠራረት ችግር ጭብጡ የክርክሩ መስማት ሲጀመር አለመመሥረት ጭብጥ ሲመሠረትም የተመጠነ አለመሆን፣

6. የዳኞች እውቀት ክህሎትና የሥራ ልምድ እንዲሁም ጥረት ውስንነት፡፡

7. የጉዳዮች ፍሰት አመራር /Case Flow Management) የዳበረ አለመሆንና ጥብቅ የቀጠሮ ፖሊሲ አለመኖር አሁን በBPR ጥናት መሠረት ስራን ለማከናወን ያለው እንቅስቃሴ ጥሩ ቢሆንም፡፡

8. ከፍ/ቤቶች ተቋማዊ ጥንካሬ፣ውጤታማነት፣ቅልጥፍና እና ተገማችነት አለመዳበር ጋር በተያያዘ ሁኔታ ወ.ዘ.ተ የመሳሰሉት በግንባር ቀደምትነት ሊጠቀሱ የሚችሉ ችግሮች ናቸው፡፡

- ተሳታፊዎችም ሌሎች ከላይ ያልተጠቀሱ ምክንያቶችን እንድትገልፁ ይጠበቃል፣

## 14. <u>የፍርድ አፃፃፍ ሁኔታ</u>

በዚህ ርዕስ ሥር የሚጠቀሱት ጉዳዮች /ነጥቦች/ ለጥሩና መጥፎ የዳኝነት ውሳኔ አፃፃፍ መለኪያዎች ተደርገውም ሊወሰዱ የሚችሉ ናቸው፡፡ የፍርድ አፃፃፍ በብዙ ሁኔታ የተለያየ ሊሆን ይችላል፡፡ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሚሰከተለው ፍርድ አፃፃፍና የይግባኝ ሰሚ እና የሰበር ሰሚ የሚሰከተለው የፍርድ አፃፃፍ ዘዴ የተለያየ ነው፡፡ ሆኖም ግን ለሁሉም ዓይነቶች በፍትሐብሔርም ሆነ በወንጀል ጉዳዮች የጋራ የሆነ ጠባይና ዘይቤ አላቸው ማንኛውም ክርክር የሚቋጨው በፍርድ ነውና፡፡ ምንም እንኳ ፍርድ ክርክሩን የያዘው መዝገብ ምትክ ባይሆንም የመዝገቡን ይዘት በአጭሩ ያሳያል ተብሎ ይታመናል፡፡የመዝገቡን ይዘት ለማሳየት ደግሞ የተለያዩ ዳኞች የተለያየ የአፃፃፍ ዘይቤ ( Style ) መጠቀማቸው ተፈጥሮአዊ ( Natural) ቢሆንም ሁሉም ፍርዶች ሲፃፉ የሚከተሉትን እንዲይዙ /እንዲያሟሉ ይጠበቅባቸዋል፡፡

### 14.1) **የቋንቋ አጠቃቀም**

ፍርዱ የሚጻፍበት ቋንቋ የትኛውም ይሁን ለማንም ሰው ( የሕግ ዕውቀት ለሌለው ሰው ሁሉ) በሚገባ ግልፅ እና አሻሚነት በሌለው ቋንቋ መጻፍ ይገባዋል፡፡ የሙያ ቃላት (Technical words) ወይም የሕግ ቃላትን በተቻለ መጠን ማስወገድ አስፈላጊ ነው፡፡ በተቻለ ሁሉ ለእነዚህ ቃላት አቻ ቃላት በመፈለግ መጠቀም እንደአማራጭ ሊወሰድ ይገባዋል፡፡ በአማራጭ አቻ ሆኖ የገባው ቃል የሙያውን ቃል የተካም ይሁን ቀጥታ ትርጉም ያልተገኘለት የሌላ ቋንቋ ለፍርዱ አስፈላጊና ዳኛው ምን ለማለት እንደፈለገ በተለይ ለይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት መገለፅ ያለበት ከሆነ የውጭውን ቋንቋ በቅንፍ ውስጥ በማስገባት ማሳየት ይቻላል፡፡

- **ነገሮችን የሚያራዝም አያያዥ ቃላትን መጠቀም አያስፈልግም፡**

ፓራግራፍም በተቻለ መጠን አጠር አጠር ያለ ቢሆን ይመረጣል በተለይም አረፍተ ነገሮች

ቀላል መሆን አለባቸው ጉዳዩን የሚያስረዝሙ እንደ "ወይም" "እና" " ማለትም" . . . . የመሳሰሉ ሀሳብ አራዛሚ አያያዥ ቃላትን በተቻለ መጠን አለመጠቀም ይመረጣል፡

- የግድ ካልሆነ በስተቀር ከስራ ቋንቋ ውጪ ያለን ሌላ ቋንቋ መጠቀም አያስፈልግም፡፡
  ይህም ማለት የሌላ ቋንቋን /እንግሊዘኛ፣ላቲን . . . ./መጠቀም ጉዳዩን በይበልጥ የሚገልፅ እና ታዳሚን የማያደናግር እስከሆነ ድረስ ብቻ ነው ጥቅም ላይ መዋል ያለበት፡፡
- የሚያግባቡ ቃላት ብቻ መጠቀም
  የሚያግባቡ ወይም የተለመዱ (Common) የሆኑ ቃላት ብቻ መጠቀም ውሳኔውን የሚያነበውም ሆነ የሚሰማው ሰው ሁሉ በቀላሉ ሊገነዘበው ይችላል፡፡ ነገር ግን የማይታወቁና የሠፈር ቃላትን በውሳኔ አፃፃፍ ውስጥ መጠቀም የውሳኔውን ይዘት ተቀባይነት የሚቀንስና አንባቢንም ሆነ የበላይ ፍርድ ቤቱን የሚያደናግር በመሆኑ ጥንቃቄ ሊደረግበት ይገባል፡፡
- የቀልድ፣ የምፀት፣ የስድብ አባባሎችን ማስወገድ የግድ ያስፈልጋል፡፡
  ምሳሌ፡- ተደበደብኩ ባይ" የተከበሩ ከሳሽን" "ተደፈርኩ ባይ የ12 ዐመት ወይዘሪት" . . . . የሚሉት አግቦ እና ምፅት ያዘሉ አፃፃፎች በመሆኑ ሊወገዱ ይገባል፡፡
- በርካታ ጥቅስ መደርደርም አስፈላጊ አይደለም

በተቻለ መጠን በውሳኔ ውስጥ ጥቅስ ባይገባ ተመራጭ ነው ምክንያቱም ተከራካሪ ወገኖችም ሆነ ፅሁፋን የሚያነቡ ሰዎች ወይም ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በቀላሉ ጉዳዩን ከመረዳት ይልቅ ጥቅሱ የተለያዩ ትርጉም ሊኖረው ስለሚችል ትኩረት የሚሠጡበትን ጉዳይ ትተው ጥቅሱ ላይ ስለተሰጠው ማብራሪያ ሊያተኩሩ ስለሚችሉ መጠንቀቅ ያስፈልጋል፡፡ለምሳሌ፡- "ሰው" የሚለውን ቃል ለማስርዳት የበርካታ መዝገበ ቃላት ፍቺን ማስቀመጥ አያስፈልግም፡፡

- አግላይ ቋንቋ መጠቀም አያስፈልግም

የምንጠቀምበት የቋንቋ አጠቃቀም በተቻለ መጠን ለሁሉም የሚስማማ መሆን አለበት አንዱን ከፍ አድርጎ ሌላውን ዝቅ የሚያደርግ መሆን የለበትም፡፡ምሳሌ፡- " አንድ ምክንያታዊ ወንድ ከማለትይልቅ " አንድ ምክንያታዊ ሰው" ማለት ይመረጣል" ይሄ አገላለፅ ለሁሉም የሚስማማ በመሆኑ ተመራጭ ያደርገዋል፡፡

### 14.2 ፍርዱ የተንዛዛ መሆን የለበትም፣

ፍርዱ የተንዛዛ ወይም አላስፈላጊ በሆኑ ቃላት የታጨቀ መሆን የለበትም፡፡ ረጅም ፍርድ ሁልጊዜ ጥሩ ፍርድ አይደለም፡፡ "የተንዛዛ ፍርድ ሲጻፍ ስቃይ ነው ሲነበብም ሥቃይ" "A Prolix Judgment is a Torture to Write, and a Torture to Read" ይባላል፡፡ ሐሳቦችን ወይም አገላለጾችን መደጋገም የለበትም በተለይም ደግሞ የምስክሮች ቃል እየተደጋገመ ሲጻፍ

አይገባውም፡፡የምስክሮችን ቃል እየደገሙ መጻፍ በእኛ አገር የፍርድ አጻጻፍ ልምድ በተለይ በወንጀል ፍርዶች በብዛት የሚታይ ነገር ነው፡፡ በፍርዱ ውስጥ እያንዳንዱ ምስክር የሰጠው ቃል በሙሉ ከተጻፈ በኋላ እንደገና ፍ/ቤቱ ጥፋተኛ ነው፤ ጥፋተኛ አይደለም፤ ወይም ተከላክሏል አልተከላከለም ለማለት ክሱንና የምስክሩን ቃል ሲያገናዝብ የምስክሮች ቃል እንደገና ይደገማል፡፡

ለምሳሌ በአንድ ፍርድ ክሱን ዘረዘረ፣ የምስክሮችን ቃል የመከላከያውን ምስክር ቃል አሰፈረ፡፡ ቀጥሎ በጉዳዩ ከላይ በዝርዝር የተገለፀው ሲሆን ፍ/ቤቱ የወንጀል ሕግን ክስና ማስረጃ ተከሳሹ ካቀረበው መከላከያ ማስረጃ ጋር በማገናዘብ መርምሮታል፡፡ ዐቃቤ ሕግ የመሠረተው ተከሳሹ" . . ሟቹን በጨቤ ወግቶ ገድሎታል በማለት ነው፡፡ ተከሳሹ የእምነት ክሕደት ቃል ተጠይቆ ክዶ ተከራክሯል፡፡ አንደኛው የዐቃቤ ሕግ ምስክር በሰጠው ምስክርነት .. " እያለ በፊት የዘረዘረውን ጉዳይ ይደግማል፡፡ ይህ ዓይነት አጻጻፍ በብዙ የወንጀል ፍርዶች አልፎ አልፎም በፍትሐብሔር ጉዳይ በሚሰጡ ፍርዶች ላይ ይታያል፡፡ ሊወገድ የሚገባው ልምድ ነው፡፡ፍርዱ እጥር ምጥን ያለ ከጉዳዩ ጋር የተገናዘበ መሆን አለበት፡፡

(Judgment must be Precise & Concise)፣

ፍርዱ እጥር ምጥን ብሎ ነገር ግን የተነሱትን ጉዳዮች ሁሉ የሚዳስስ መሆን አለበት፡፡ ፍርዱ ማጠሩ ጥሩ ነው ቢባልም የተነሱ ክርክሮችንና ጭብጦችን የማይመልስ መሆን የለበትም፡፡ ለተነሱት ጭብጦችም ተገቢውን የሕግ ትንታኔ፣ለተነሱት የፍሬ ነገር ክርክሮችም ከቀረቡት ማስረጃወች ጋር እያገናዘበ ማብራራት ይጠበቅበታል፡፡ አለፍ አለፍ እያደረገ ከዚህም ከዚያም አንዳንድ ነጥቦችን እየነካካ አገጣጥሞ ግልብና ግብታዊ በሆነ መልክ የሚደመድም ፍርድ (Sketchy Judgment) መሆን የለበትም፡፡ በመሆኑም ፍርዱ እጥር ምጥን ማለት አለበት ሲባል በግራ ቀኙ የተነሱ ዳኝነት ሊያርፍባቸው የሚገባቸው ነጥቦች ተራቸውን ጠብቆ በሚገባ መተንተን አለበት የሚለውን ይጨምራል፡፡

14.3 .**ማኅፀረ-ቃል**፣/Abrevation/

በፍርድ ውስጥ ማኅፀረ-ቃል መጠቀም በፍፁም መወገድ ይኖርበታል፡፡ ፍርዱ ለፍርድ ቤቱ ብቻ የሚቀር ወይም ለተከራካሪዎች ብቻ አገልግሎት ያለው ሳይሆን ሕዝባዊ ሠነድ (Public Document) ነው፡፡ የታሪክም ሰነድ ነው፡፡ ለወደፊቱ ትውልድ የሚቆይ ነው፡፡ እንደዚህ ዓይነቱ ሠነድ ደግሞ ለሁሉም የሕብረተሰብ ክፍል ለወደፊቱ ትውልድ ግልፅና የማያሻማ ሊሆን ይገባል፡፡ ማኅፀረ-ቃል ቃሉን ባልለመዱ ሰዎች አካባቢ መደናገርን የሚፈጥር ስለሆነ በፍርድ አጻጻፍ ጊዜ ሊወገድ የሚገባው የአጻጻፍ ስልት ነው፡፡

## 14.4 ሚዛናዊነት (Balance)፣

ፍርድ ከሁሉም በላይ በሐሳቦች አቀራረብና በተለያዩ ጭብጦች አቀማመጥ ሚዛናዊ ሊሆን ይገባዋል፡፡ የውስጥ ስሜትንና ፍላጐትን በምንም መልኩ የሚያንፀባርቅ (Display of Sentiments and Emotions) መሆን የለበትም፡፡ ዳኛ ፀጋን የሚያጸድቅ ሀጢያትን የሚኮንን አይደለም፡፡(Neither Rewards Virtue nor Chastises vice ) በአንድ ሰውና በሌላው መካከል ወይም በአንድ ዜጋና በመንግስት መካከል በተነሳ ጉዳይ ገለልተኛ በሆነ ሁኔታ ፍትሕን ማስተዳደር (Administers even-handed Justice) ብቻ ነው ተግባሩ፡፡ ስለዚህ ዳኛው የቀረበለትን ፍሬ ነገርና ማስረጃ መርምሮ ከሕጉ ጋር አገናዝቦ ፍርዱን መጻፍ እንጂ ለተጐዳ ወገን የሐዘን ስሜቱን ወይም የአጥፊውን በደለኛነት በመኮነን ፍርዱን መጻፍ የለበትም፡፡

## 14.5 ያላጋደለ ፍርድ (Lopsidedness)፣

ያጋደለ ፍርድ (Lopsided Judgment)የሚባለው በክርክሩ ውስጥ ከተነሱት ጭብጦች ውሰጥ የተወሰኑትን ወይም አንዱን በማጉላት ሌላውን ቦታ ባለመስጠት ጣል ጣል የሚያደርግ ፍርድ ነው፡፡ ሁሉም ተከራካሪዎች ያነሱዋቸው ጭብጦች ተገቢወ ቦታ ተሰጥቷቸው ሊብራሩ ይገባል፡፡ ዳኛው በክርክሩ አንድ ገጽታ ብቻ ተማርኮ በዚሁ ላይ ብቻ ያተኮረ እንደሆነ ሌሎች ጭብጦች ሊዘነጉ ወይም ተገቢው ትኩረት ሊነፈጋቸው ይችላል፡፡ በዙህም የተነሳ ፍርዱ ያጋደለ ይሆናል፡፡

## 14.6 ሁሉንም የክርክሩን ገጽታዎች ማብራራት፣

ዳኛው ከሚያምንበት ጋር የሚጋጩ ማስረጃዎች በአንዱ ተከራካሪ ወገኖች ወይም በሁለቱ ተከራካሪ ወገኖች የሚቀርቡበት ጊዜ አለ፡፡ እንዲሁም ለዳኛው የማይመስል ክርክር የሚቀርብበት ጊዜ አለ፡፡ ይህ በሆነ ጊዜ ሁሉ ዳኛው ከፍርዱ ውስጥ እነዚህን ነገሮች ወደ ጐን በማድረግ ሊተዋቸው ወይም ሊያልፋቸው አይገባም፡፡ በክርክሩ አቀራረብ ወይም ማስረጃው ምክንያታዊ ካልሆነ ይህንኑ ግልጥልጥ አድርጐ በፍርዱ ውስጥ ሊያሳይ ይገባል፡፡ይህን በተመለከተ በአንዳንድ መዝገቦች እንደሚታየው ከሳሽ የማይገባውን የጠየቀ ሲመስል ወይም ተከሳሹ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባዋል ሲል ከሚያቀርባቸው መከራከሪያዎች አንዳንዶች ከላይ ሲታዩ እንዲሁ ለክርክር ብቻ የቀረቡ ይመስላሉ፡፡

በዚህን ጊዜ ፍ/ቤቱ ዋጋ ባለመስጠት ያልፋቸውና በፍርዱ ውስጥ ተነስተው ምላሽ ሳይሰጣቸው የሚቀሩበት ጊዜ አለ፡፡እንዲህም በሚሆንበት ጊዜ ፍ/ቤቱ ተጠይቆ ያልሰጠው ነገር እንዳልተሰጠ ይቆጠራል የሚለው የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 5(2) የሚጠቀስበት ጊዜ አለ፡፡

ሆኖም ግን ፍርዱ በሚጻፍበት ጊዜ ምንም እንኳን የቀረበው ማስረጃ ዳኛው ከሚያምንበት ተቃራኒ ቢሆንም ወይም ክርክሩ ዋጋ ያለው ባይመስልም በፍርዱ ውስጥ ተገቢው ቦታ ተሰጥቶ ሊተነተንና የማስረጃው ደካማነት ወይም የክርክሩ ዋጋ ቢስነት ሊታይ ይገባዋል፡፡

## 14.7 ሐሳባዊ የሆኑ ጉዳዮች (Hypothetical Cases)፣

ፍርድ ቤቱ ፍርዱን በሚጽፍበት ጊዜ ጉዳዩን ለማብራራት ሲል የፈጠራ ጉዳዮችን እየፈጠረ በምሳሌነት  ለመግለፅ የሚሞክርበት ጊዜ አለ፡፡ ይህ ግን ለብዙ ትርጉም በር የሚከፍት ሊሆን ስለሚችል በተቻለ መጠን ሊወገድ ይገባዋል፡፡በምሳሌያዊ አነጋገር ሐሳብን ለመደገፍ የሚደረገው የአጻጻፍ ዘዴም ብዙ ጊዜ ተመራጭ አይደለም፡፡ በመጀመሪያ የተገለፀው ሐሳብ ምንነቱ በውል አልታወቀም፡፡ ይህ ደግሞ በተለያየ ቦታ የተለያየ ትርጉም ባለው ምሳሌያዊ አነጋገር ከታጀበ የበለጠ አደናጋሪ ሊሆን ስለሚችል ምሳሌያዊ አነጋገር በፍርድ አጻጻፍ ውስጥ መግባት የለበትም፡፡

## 14.8 በማስረጃ የተደገፈ ፍርድ፣

ዳኛው ፍርዱን መስጠት ያለበት በቀረበው ማስረጃ ብቻ መሆን አለበት፡፡ በመዝገብ ውስጥ ከተያዘው ማስረጃ ውጭ የፈለገውን ያህል ለጉዳዩ አግባብነት ያለው ማስረጃ ቢሆን ለፍርዱ መሠረት ሊሆን አይገባውም፡፡ ዳኛው በግል የሚያውቀው ጉዳይም የማስረጃነት ዋጋ ኖሮት ለፍርዱ መሠረት መሆን አይገባውም፡፡ ስለዚህ ፍርድ ባልቀረበ የጽሑፍ ወይም የምስክር ማስረጃ ላይ ተመስርቶ ሊጻፍ አይገባውም፡፡

## 15.9 የተከራካሪዎች ወይም የምስክር ሥም አጻጸፍ፣

በፍርዱ ውስጥ መጠቀስ ያለባቸው ተከራካሪዎች ወይም ምስክሮች በተለያየ መግለጫ የሚታወቁበት ሁኔታ ይኖራል፡፡ ለምሳሌ ተከሳሹ ሻለቃ በላይ ወረደ ቢሆን በፍርዱ ውስጥ አንዴ ተከሳሹ፣ አንዴ ሻለቃ አንዴ በላይ ወረደ፣አንዴ ሻለቃ በላይ ወረደ እየተባለ በማፈራረቅ ሰውየውን መጥቀስ ትክክል አይደለም፡፡ በፍርዱ መጀመሪያ ላይ ተከሳሹ ማን እንደሆነ ስለታወቀ ተከሳሹ በማለት መጥቀስ ወይም ስሙን ከመጀመሪያ መጥቀስ ይገባል፡፡ በማፈራረቅ የመጻፉ ስልት የፍርዱን ግልፅነት የሚያጠፋ (አደናጋሪ) ከማድረግም አልፎ ተጠቃሹን ግለሰብ ፍርድ ቤቱ የሚሳለቅበት ስለሚመስል የሚያበሳጭ ሊሆን ይችላል፡፡

## 14.10 የፊደላት ተስተካክሎ መጻፍ፣

ፍርዱ ውስጥ የሚጻፉ የሰዎችና የቦታ ስሞች በተቻለ መጠን ተስተካክለው መጻፍ ይገባቸዋል፡፡

ፍርዱ ውስጥ የሚጻፈው ስም ስሕተት የስሙን ባለቤት ስሜት የሚጐዳ ሲሆን የቦታ ስሞች ስሕተትም አንባቢው በፍርድ ቤቱ ላይ ጥሩ ስሜት አይኖራቸውም፡፡ (ፍርድ ቤቱን ግዴለሽ፣ አካባቢውን የሚንቅ ወዘተ . . . በማስመሰል ጥሩ ያልሆኑ ስሜቶችን እንዲያድርበት ያደርጋል፡፡

**14.11 የሠነዶች አጠቃቀስ፣**

ለፍርድ ቤት የቀረቡ በፍርዱ ውስጥ የሚጠቀሱ የመሥሪያ ቤት ሠነዶች የተጻፉበት ቀንና ቁጥራቸው ተስተካክሎ የአውጭው መ/ቤት ሥም ጭምር ሊጠቀሱ ይገባል፡፡ ቀንና ቁጥሩ ያልተገለፀ ደብዳቤ ወይም መመሪያ አደናጋሪ ነው፡፡

**14.12 አግባብነት ያለውን ሕግ መጥቀስ፣**

ተከራካሪ ወገኖች በክርክራቸው ውስጥ የሚያነሷቸውን ሕጐች በየበኩላቸው ይጠቅሙናል ያሏቸውን ነው፡፡ እያንዳንዱ ተከራካሪ ለጉዳዩ አግባብነት ያለውን ሕግ መጥቀሱ ፍ/ቤቱ በዚያ እንዲወሰን የሚያደርገው አይሆንም፡፡ ስለዚህ ፍርድ ቤቱ ፍርድን በሚሰጥበት ጊዜ በተከራካሪ ወገኖች ተጠቀሰም አልተጠቀሰም ለጉዳዩ አግባብነት አለው የሚለውን ሕግና ቁጥር በትክክል ሊጠቅስ ይገባል፡፡ ለጭብጡ ተገቢውን ሕግ መፈለግ የፍ/ቤቱ ተግባር ነውና፡፡

**14.13 የተገራና ለሰስ ያለ ቋንቋ (Language to be Sober and Temperate)፣**

ፍርድ የሚጻፍበት ቋንቋ የሚያጋንን፣ ልቅ እና አንዱን ዝቅ አንዱን ከፍ የሚያደርግ መሆን የለበትም፡፡ ዳኞች ሐሳባቸውን በሚገልፁበት ጊዜ በተገራና በለሰለሰ ቋንቋ መሆን ይገባዋል፡፡ በፍርዱ ውስጥ ያለው አገላለፅ ዳኛው መጀመሪያውኑ አቋም ይዟል የሚያሰኝ መሆን የለበትም፡፡ አገላለፁ በሙሉ ዳኛው አንዱን ወገን የሚደግፍ መሆኑን የሚያመለክት ሳይሆን ገለለተኛ ሆኖ ጉዳዩን ከሕጉ አንፃር ብቻ የተመለከተው መሆኑን ማሳየት አለበት፡፡

**14.14 መግለጫዎች ማስረጃን የተደገፉ መሆን ስለሚገባው (Remarks to be Based on Evidence)፣ፍ/ቤቱ ስለከሳሽ** ተከሳሽ ወይም ምስክሮች ወይም ተደረገ ስለተባለው ጉዳይ የሚሰጠው የመግለጫ ቃል በቀረበው ማስረጃ መሠረት የታወቀውን (የተረጋገጠውን) መሆን አለበት፡፡ **ለምሳሌ፡-** በቸልተኝነት ሰውን የገደለውን ተከሳሽ ነፍስ ገዳዩ ብሎ መግለፅ ተገቢ አይደለም፡፡ከዚህም በላይ አንድ የመንግሥትም ሆነ የግል ድርጅት በክሱ ውስጥ ተሳታፊ ሆኖ ጥፋተኛ ነው በመባሉ ጠቅላላ ድርጅቱን ሁልጊዜ ጥፋት እንደሚሠራ አድርጐ በፍርዱ ውስጥ የአጥፊነት ስያሜ መስጠት በፍፁም ሊወገድ የሚገባው ነው ስለፖለቲካ ፓርቲዎች ወይም ስለመንግሥት ወይም ስለመንግሥት ባለሥልጣን ዳኛው ያለውን የግል አመለካከት በፍርዱ ውስጥ ከማስፈር መቆጠብ ይኖርበታል፡፡

**14.15 ፍርዱ የመዘገቡ ምትክ ስላለመሆኑ (Not a Substitute of the File)፣**

ፍርዱ በውስጡ መያዝ ያለበት የክርክሩን ሂደት ዋና ዋና ፍሬ ነገሮችን በአጭሩ መሆን ይኖርበታል፡፡ ከዚህ በኋላ የተነሱትን ጭብጦች በመዘርዘር ከሕጉ ጋር በማገናዘብ የሚሰጠው ትንታኔ በተቻለ ሁሉ ሰፊውን ክፍል መያዝ ይኖርበታል፡፡ ብዙ ጊዜ ግን ከመዝገቦች ለማየት እንደሚቻለው ፍ/ቤቱ በሚሰጣቸው ፍርዶች አብዛኛውን ክፍል ይዞ የሚገኘው ተከራካሪ ወገኖች ያቀረቡት ክርክር ነው፡፡ አሥር ገፅ ባለው ፍርድ 9 የክስና መልስ ማስረጃ ሪፖርት ሆኖ ለጉዳዩ አግባብነት አለው የሚባለው ሕግ የሚጠቀስበት ብዙ ጊዜ ምንም ዓይነት ትንተኔ በማይኖርበት ሁኔታ በአብዛኛው ሩብ ገጽ ያህል ብቻ ነው፡፡ ይህንን ከብዙ መዝገቦች ማየት ይቻላል፡፡ ይህ የፍርድ አፃፃፍ ተከራካሪዎች ያነሱዋቸውን ፍሬ ነገሮች በስፋት የሚቀርብ ሪፖርት እንጅ  የፍ/ቤቱን አቋምና የህጉን አተረጓጐም የሚያሳይ ፍርድ ነው ለማለት አይቻልም፡፡

14.16 የፍርድ ውሳኔ አፃፃፍ ለአፈፃፀም የማያስቸግር ተፈፃሚነት ያለው መሆን አለበት፡፡ ማንኛውም ፍርድ የውሳኔ አፃፃፍን ይዘትና ቅደም ተከተል ያሟላ ከጉዳዩ ባህሪይ እስከ መደምደሚያ የያዘ መሆን አለበት፡፡

- **<u>ጥሩ ፍርድ የሚባለው ምን ዓይነት ፍርድ ሲሆን ነው?</u>**

ጥሩ ፍርድ ከሁሉ በፊት በሚገባና በግልፅ ቋንቋ ይጻፋል፡፡ ቴክኒካል ወይም የሕግ ቋንቋን በተቻለ መጠን አይጠቀምም፡፡ የሕግ ቋንቋ መጠቀም የሚያስፈልግ ከሆነ አቻውን ተራ ቋንቋ ያስገባል፡፡ ፍርዱ ሲጻፍም፣

- ሲያነቡት የሚያጓጓ ለመረዳት ቀላል፣ አንድን ጉዳይ ሳይጨርስ ወደ ሌላው የማይዘል አላስፈላጊ ነገሮችን ያላዘለ ግን ዋና ዋና ነጥቦችን ያካተተ እጥር ምጥን ያለ ነው፡፡
- አጫጭር ዐረፍተ ነገሮችን መጠቀም ለፍርዱ ግልፅነት ጥሩ ዘዴ ነው፡፡
- የቀልድና የአግቦ አነጋገሮችን ያስወገደና ሁሉንም ሰው የማያስከፋ ፍርድ መሆን አለበት፣
- በፍርዱ ውስጥ "የተባለው ወገን" ይመስላል" "ቀደም ብሎ የተጠቀሰው"የሚሉ ቃላት በተቻለ መጠን ሊወገዱ ይገባል፡፡
- ክሱን ወይም መልሱን በሙሉ መድገም አያስፈልግም  በተቻለ መጠን ለክርክሩ ዋና ዋና የተባሉትን በማመልከት ፍሬ ነገሮችን ብቻ ሊጠቀሙ ይገባል፡፡
- የተከራካሪው መጠሪያ በፍርዱ ውስጥ አንድ ወጥ ሆኖ መጻፍ አለበት፡፡ (ተከሳሹ ወይም ስሙ) ፣
- በፍርዱ ውስጥ ለተወሰነ ሐሳብ አጽንኦት ለመስጠት ኢታሊክስ ወይም የግርጌ መስመር ማስመር ወይም ትምዕርተ ጥቅስ መጠቀምን ያስወገደ መሆን አለበት፡፡

**ጉዳይ (case)  <u>የከሣሽ ክስ ፍሬ ነገሮች</u>**

- አቶ በላይ ታርጋ ቁጥር አ.ማ 00507 የሆነ ባጃጅ ተሽከርካሪ ባለቤት ናቸው፡፡
- ይህቺን ባጃጅ የግብርና ኮሌጅ በቀን 100/ አንድ መቶ ብር ሂሣብ ተከራይቷታል፡፡
- ጥቅምት 30 ቀን 2000 ዓ.ም የጉን ቁጥሩ 00037 አማ የሆነ የጭነት አይሱዙ መኪና ባጃጅን በመግጨት አደጋ አድርሶበታል፡፡
- በዚሁ አደጋ ምክንያት ባጃጅ ያለ ሥራ 10 ቀን ለጥገና በመቆየቱ ለጋራጅ 1500 ብር ፣ለሠራተኛ ደመወዝ 200.00 ብር (ለ10 ቀን በቀን 10 ብር)
- ባጃጁ ቢሠራ ኖሮ በቀን 100×10 ቀን = ብር 1000.00 / አንድ ሺህ ብር / በአጠቃላይ 27000 የጉዳት ካሣ ከበቂ ኪሣራና ወጭ እንዲሁም ወለድ ታስቦ ይከፈለኝ በማለት ክስ አቅርቧል፡፡

**በማስረጃነትም**

1. የባጃጁ ሊብሬ፣
2. ከኮሌጅ ጋር ስምምነት የወሰደበት ውል /ዋናውና ኮፒው/ ተያይዟል፣
3. አደጋው የደረሰው በአቶ ከበደ በአይሱዙ መኪና ምክንያት መሆኑን የሚያሣይ የቴክኒክ ማስረጃ ተያይዟል፡፡
4. አደጋው ሲፈጸም የተመለከቱ ሶስት ምስክሮች ቀርበው መስክረዋል፡፡
5. የተለያዩ ገንዘብ የተከፈለባቸው ደረሰኞች ተያይዘዋል፡፡

የተከሣሽ መልስ / አቶ ከበደ /

- አደጋው መድረሱን አምኗል፡፡ ሆኖም በመከራከሪያነት ያቀረባቸው ነጥቦችም፡-
    1. ለማስጠገኛ ወጣ የተባለው ወጭ የተጋነነ ነው፣
    2. በከሣሽ የቀረበው የውል ሠነድ ህጋዊነትን የጠበቀ አይደለም፣
    3. አደጋው ከመድረሱ ከአንድ ሣምንት በፊት መኪናዬ ባልታወቀ ሰው ተሰርቆ ስለነበር ለደረሰው ጉዳት ጥፋትና ኃላፊነት የለብኝም ብሏል፡፡

<u>**በማስረጃነት**</u>

1. ተከሣሹ ለፎገራ ወረዳ ፖሊስ መኪናው ካቆመበት የጠፋ ስለመሆኑ ያመለከተበት ማስረጃ በቁጥር -------------------- በቀን -----------------------የተፃፈ ተያይዟል፡፡
2. የመኪናው ሊብሬ / ባለቤትነት ደብተር / ኮፒው ቀርቧል፡፡

<u>**መወያያ ጥያቄ**</u>

1. ከላይ የቀረበውን ክስና መልስ እንዲሁም ማስረጃዎችን በመመርመር አንድ ፍርድ መያዝ ያለበትን ቅርጽና ይዘት ግምት ውስጥ በማስገባት ፍርድ / ውሣኔ ሰጡ፡፡

## 15.<u>የውሣኔ አፃፃፍ በፍርድ ቤቶች ደረጃ</u>

አስቀድመን ለመመልከት እንደሞከርነው የውሣኔ አፃፃፍ ይዘት በጥቅሉ የተመሣሰለ ቢሆንም ከጉዳይ ጉዳይ ግን ይለያያል፡፡ በወንጀል ጉዳይ የሚፃፈው ውሣኔ በይዘቱ እና በቅርፁ በፍትሐብሄር ጉዳይ ከሚፃፈው ይለያል፡፡ በፍታብሔር ጉዳይም በተፋጠነ ሥነ ሥርዓት የሚቀርበው በመደበኛው ሥርዓት ከሚቀርበው እንዲሁም በመደኛ ከሚቀርበው ውስጥ አከራካሪ ጉዳይ ያለው እና ጭብጥ የሌለው ልዩነት አላቸው፡፡ ጭብጥ በሌላቸው ውስጥም ቢሆን የውሣኔ አፃፃፍ በተለይ በውሣኔ ሰጭ ጥራት እና ትጋት ሊለያይ ይቻላል፡፡ ልዩነቱ ማቆሚያ አይኖረውም፡፡በዚህ ርዕስ ላይ የምንመለከተው በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እና በይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች መሐከል ሊኖር የሚችለውን የውሣኔ አፃፃፍ ቅርጽ እና ይዘት ነው፡፡ በዚህ መልኩ ውይይት የሚደረግበት የውሣኔ ጽሑፍ ልዩነት ሣይደረግበት ለሁሉም ጉዳዩች ነው፡፡

### 15.1 <u>የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ውሣኔ አፃፃፍ</u>

የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤቶች በተለይ የማስረጃ እና የፍሬ ነገር ክርክር በስፋት የሚካሄድባቸው እና የሚመዘገብባቸው ናቸው፡፡ በዚህ ደረጃ በሚሰጡ ውሣኔዎች የፍርድ ቤቱ ውሣኔ አልፎ አልፎ መንደርደሪያ ላይ ሰፍሮ ይገኛል፡፡ ከሣሽ በክሱ ላይ “ ክሱ የቀረበው........ ያህል ገንዘብ ለማስከፈል ነው” በማለት ጥያቄውን በግልጽ በመንደርደሪያው ላይ እንደሚገልጸው ሁሉ በመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም በዚሁ አገላለጽ የተከሣሽን ክስ መሰረዙን ወይም በተከሣሽ ላይ የኃላፊነት ውሣኔ መሰጠቱን ገልፆ  ሊጀምር ይችላል፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ ለሚፃፉ ውሣኔዎች በይዘታቸው እንደቅደም ተከተሉ፣

1. የጉዳዩ ዓይነት፣
2. ፍሬ ነገሮችን፣
3. ጭብጥ / ጭብጦችን /፣
4. ሕግ፣ ብያኔ እና መደምደሚያ፣
5. ማጠቃለያ/ ፍርድ /፣ሊይዙ ይገባል፡፡፡ በዝርዝር ስንመልከታቸውም፣

#### 1. የጉዳዩ ዓይነት

ይህ የውሣኔ ክፍል “ ፍርድ” እየተባለ ርዕስ ተሰጥቶት ከሚፃፈው ሥር በመጀመሪያ የሚሰፍረው ነው፡፡ ጉዳዩ የምን እንደሆነ፣ ያለፈበት አስፈላጊ ታሪክ፣ በጉዳዩ ላይ ፍ/ቤት ያለው ሥልጣንና በፍ/ቤቱ ሊወሰን የሚገባው ጉዳይ የሚጠየቅበትን የሚይዝ ነው፡፡ ለምሣሌ( ጉዳዩ የመሬት ክርክርን የሚመለከት መሆኑ፣በጉዳዩ ላይ የመሬት አስታራቂ/ አስማሚ/ ሽማግሌዎች ያደረጉት የማስታረቅ፣ የማስማማት/ ጥረት ውጤት አለማስገኘትን ጉዳዩ በሕግ መሠረት በፍርድ ማለቅ የሚገባው ስለሆነ ከሣሽ መሬቱን ለመረከብ ጥያቄ ማቅረቡ ….. ይገለጽበታል፡፡) እንደ ርዕስ ሊጠቀስ የሚባውም ነው፡፡

## 2. ፍሬ ነገር

ፍሬ ነገር ስንል በተከራካሪ ወገን ማስረጃ ሊረጋገጡ ወይም ሊፈርሱ የሚችሉ ሕግ ነክ ያልሆኑ ክርክሮች ማለታችን ነው፡፡ በሲቪል ሎው ሕግ ፊት ውሣኔ አሰጣጥ በአንድ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ውሣኔ ውስጥ ፍሬ ነገሮች ምን ጊዜም መካተት ይገባቸዋል፡፡ / በጉዳዩ አስፈላጊ የሆኑት ብቻ በትረካ መልክ ሊካተቱ ይገባል፡፡ ዳኛው ተገቢ የሆኑትን የፍሬ ነገር ክርክሮች ብቻ መርጦ መመዝገብ ይኖርበታል፡፡ ውሣኔውን ለመረዳት የሚያነብ ሰው ወሣኝ የሚለውና ውሣኔውን ለመረዳት የሚያግዙት ፍሬ ነገሮች ብቻ ይካተታሉ፡፡ ተከራካሪ ወገን እና አንባቢ በውሣኔው ተስቦ በቀላሉ እንዲያነበው እና እንዲረዳው ፍሬ ነገሮችን በተቻለ መጠን ይገለፃል፡፡ ጊዜን መጥቀስ አስፈላጊ ቢሆንም ፍሬ ነገሮች እንደቀደም ተከተላቸው ቢገለፁ ይመረጣል፡፡

የውሣኔው ፀሐፊ ተከራካሪ ወገን እና / ወይም ሌላው አንባቢ ከፍሬ ነገሩ በይበልጥ የሚፈለገውን በሚያካትት መልኩ መፃፍ ይኖርበታል፡፡ ለምሣሌ በመሬት ጉዳይ ከፍ/ቤት ክርክር አስቀድሞ በእርቅ ጉዳዩ መፈታት አለመቻሉ ቢገለፁ በቂ ሲሆን በውል ክርክር ጊዜ ውሉ የተፈፀመበት፣ የፈረሰበት ጊዜ ወዘተ እንደ ቅደም ተከተል እየጉላ መጠቀስ ያስፈልገዋል፡፡ የጊዜ ቅደም ተከተል ያለባቸው ጉዳዮች በሐተታ መልክ ወይም በመዘርዘር ሊገለጽ ይችላሉ፡፡ለምሣሌ…ኅዳር 21/2000 የተፈረመውን ውል ባለማክበር በውሉ ላይ የተመለከተውን እንቁላል ጥር አጋማሽ 2000 አላስረክበኝም…ብሎ መፃፍ እንደሚቻለው ሁሉ፣

1. ኅዳር 21/2000 ውል ተፈፀመ፣
2. በጥር አጋማሽ 2000 ውሉ ፈረሰ፣ተብሎ ሊቀመጥ ይቻላል፡፡

ዳኞች ፍሬ ነገርን በውሣኔያቸው ውስጥ በሚያሰፍሩበት ጊዜ የይዘት ለውጥ እንዳይኖረው ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡ በተቻለ መጠን በክርክሩ ቋንቋ መቀመጥ ይገባዋል፡፡ ዳኞች ፍሬ ነገርን የመተርጐም ሥልጣን የላቸውም፡፡ ሕግን ለመተርጐም የተሰጣቸው ሥልጣን ለፍሬ ነገር “

መመዝገብ” ብቻ ተደርጐ መታየት ይኖርበታል፡፡ ከሣሽ ጥር አጋማሽ ውሉ ፈረሰ ቢል ውሣኔ ሲፃፍ ጥር 15/2000 ተብሎ መጠቀስ አይኖርበትም፡፡ ፍሬ ነገርን መተርጐም አንባቢን የማሣመን ኃይልን መቀነስ ከመሆኑም በላይ ፍሬ ነገርን የመመርመር ስልጣናቸው / ኃላፊነታቸው/ እየቀነሱ የሚመጡ የበላይ ፍ/ቤቶችም በጉዳዩ ላይ የተዛባ ውሣኔ እንዲያሣርፍ በር የሚከፍት ስለሆነ በጥንቃቄ መፃፍ ይኖርበታል፡፡ ፍሬ ነገር በጥንቃቄ መፃፍ አለበት ሲባል የተከራካሪ ወገን የፍሬ ነገር ክርክር እንዳለ መስፈር አለበት ማለት አይደለም፡፡

**ለምሣሌ**፡- የልጅነት ይረጋገጥልኝ የሚል አቤቱታ ከቀረበ መስፈር ያለበት አባትነትን ሊያረጋግጡ የሚችሉ ፍሬ ነገሮች እንጅ አባት የተባለው ሰው የዘር ግንድ ተዘርዝሮ መስፈር አለበት ማለት አይደለም፡፡ አግባብ ያለውን ፍሬ ነገር መምረጥ ከፍተኛ ጥበብን፣እውቀትንና ልምድን ይጠይቃል፡፡ ፍሬ ነገርን መርጦ ድምዳሜ ላይ መድረስም በተመሣሣይ መልኩ ጥንቃቄን የሚጠይቁ በሀገራችን የዳኛ ብቻ የሆነ ሥራ ነው፡፡ እዚህ ድምዳሜ ላይ ለመድረስም መነሻው ማስረጃ ብቻ ነው፡፡ **ለምሣሌ** አባትነትን ለማስረዳት ከቀረበው ማስረጃ ውስጥ ፍ/ቤቱ “ ተከሣሽ/ አባት የተባለው ፣ ከወ/ሮ……/እናት / ጋር ጋብቻውን ከ14/1/1970 መፈጸሙ ተረጋግጧል፡፡” የሚል የፍሬ ነገር መደምደሚያ ላይ ይደረሣል፡፡ ይህ የፍሬ ነገር መደምደሚያ በራሱ ትርጉም የሌለው በመሆኑ ወደ ሕግ መደምደሚያ መቀየር ይኖርበታል፡፡

በዚህም መሠረት ፍሬ ነገር በጉዳዩ ላይ ለተያዘው ጭብጥ እልባት የሚያሰጥ ይሆናል፡፡ ስለሆነም በተያዘው ጉዳይ ላይ ጭብጥ ከሌለ ፍሬ ነገርና መደምደሚያ ላይኖር ይችላል ማለት ነው፡፡ በርካታ ፍሬ ነገሮች ይኖራሉ፡፡ ይህ ማለት ግን በፍሬ ነገር እና መደምደሚያ መኖር ሁል ጊዜ ጭብጥ ያስፈልጋል ማለት አለመሆኑን ማስታወስም ይገባል፡፡ፍሬ ነገሮች መረጃ የሚሰጡ፣ የታመኑ ወይም በማስረጃ ላይ የተመለከቱ፣ ጭብጥ ሊሆን የሚችል/ ክስ ላይ የተመለከተ/፣ወዘተ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ክስ የተመሠረተበት ቀን፣ የከሣሽ ቀበሌ፣ የከሣሽ ችሎታ ፣ በእነዚህ ዝርዝር ውስጥ የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ እነዚህ ፍሬ ነገሮች ውሣኔ እስከተደመደመ ድረስ ሊጠቀሱ የሚችሉ ሲሆን አስፈላጊ ካልሆኑና አግባብነት ከሌላቸው ፍሬ ነገሮች መለየት ያለባቸው ናቸው፡፡በአጠቃላይ ከጭብጥ በፊት እንዲሁም ከጭብጥ በኋላ ከጭብጡ ጋር የተያያዙ ፍሬ ነገሮች ሊገለፁ ይችላሉ፡፡ የሚፃፉ ፍሬ ነገሮች በማስረጃ / ክርክሩ / ቃል የተቀመጡ፣ የተመረጡ፣ አስፈላጊ ብቻ የሆኑት፣ በቅደም ተከተላቸው የተቀመጡ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

3. ጭ ብ ጥ

ጭብጥ ከዚህ በፊት እንደተገለጸው ተከራካሪ ወገኖች ያልተስማሙበት የፍርድ ቤቱን ውሣኔ የሚጠይቅ ነጥብ ነው፡፡ የፍሬ ነገር ወይም የሕግ አለዚያም የሁለቱም ጥያቄ ሆኖ የሕግ ምላሽ

የሚጠይቅ ነው። እንደ ሌሎች ጽሑፎች ሁሉ ጭብጥም በግልጽ ቋንቋ መቀመጥ ይኖርበታል። ጭብጥ በፍርድ ቤቱ አገላለጽ የሚቀመጥ ሆኖ በጥያቄ መልክ ወይም.... ስለመሆን/ አለመሆኑን/..... ስለመኖር/ አለመኖሩ ወዘተ...በሚል አረፍተ ነገር ሊቀመጥ ይችላል።ለምሣሌ፡- በፍ/ቤቱ ሊመረመር የሚገባው ጭብጥ /ነጥብ/ አከራካሪ ጉዳይ፣

- የከሣሽ ክርክር በይርጋ ቀሪ ሊሆን ይገባል? ወይም
- የከሣሽ ክርክር በይርጋ ቀሪ ስለመሆን አለመሆኑ ነው።ተብሎ ሊመዘገብ ይችላል። በዚህ ጊዜ ምላሽ የሚያስፈልገው ጭብጥ የሕግ እና የፍሬ ነገር ሆኖ መቋጫው የሕግ ጥያቄ የጊዜ ውጤትን የተመለከተው ይሆናል። ጭብጥ በርካታ ሊሆን ይችላል። የሕግ እና የፍሬ ነገር የተቀላቀለበት እንዲሁም በአንድ ጭብጥ ውስጥ ንዑስ ጭብጦች የተካተቱበት ይሆናል። ለምሣሌ የሚከተለውን መመልከት ያቻላል፣

1. ከሣሽ እና ተከሣሽ የፀና የጋብቻ ውል አላቸው? ካላቸው ጋብቻው የተፈጸመበትን ቀን ያረጋግጣል?
2. ጋብቻው ሊፈርስ አይገባውም በማለት ተከሣሽ ያቀረበው ክርክር የሕግ መሠረት አለው?
3. ጋብቻው በፍርድ የሚፈርስ ከሆነ፡-
   - 3.1. የተርጋ ቁጥር------- የሆነው መኪና የተከሣሽ የግል ነው?
   - 3.2. የቤት ቁጥር ....... የሆነው የከሣሽ እና ተከሣሽ የጋራ ንብረት ነው?

እየተባለ ሊቀመጥ ይችላል። (እያንዳንዱ ጭብጥ ዋና እና ንዑስ ጭብጦችን የያዘ ነው።) እንደሁኔታው ሁሉም ምላሽ ላያስፈልጋቸው ይችላል። ከሣሽ እና ተከሣሽ የፀና ጋብቻ የላቸውም የሚል መደምደሚያ ላይ ፍ/ቤቱ ከደረሰ ቀሪ ጭብጦችን በመተቸት በውሣኔ ላይ መፃፍ አያስፈልግም። የጭብጥ አቀማመጡም ቅደም ተከተል ይህንና ጊዜን መሠረት ማድረግ ይኖርበታል። የሕግ ጭብጦች በመጀመር ምላሽ ቢያገኙም ይመረጣል።

## 4. ሕግ እና ምክንያት

በውሣኔ ላይ ጭብጥ ከተገለጸ በኋላ የሚከተለው ለጭብጡ ምላሽ ለመስጠት አግባብ ያለው ሕግ እና ሕጉ ከጭብጡ ጋር ያለው ግንኙነት ነው። ሕጉን እንዳለ መገልበጥ ሁልጊዜ አያስፈልግም ለምሣሌ፣ የኢትዩጵያ ሕግ " ክርክሩ በ2 / ሁለት/ ዓመት ጊዜ ውስጥ ካልቀረበ ቀሪ ይሆናል" በማለት ይደነግጋል ተብሎ ሊገለጽ ይችላል። የሚጠቀሰው ሕግ የተሻረ ካልሆነ በስተቀር ሕግ ምንጊዜም በአሁን ጊዜ / መገለጽ አለበት። ሕጉ ግልጽ በሆነ ጊዜ ይኸው ሕግ ግልጽ ለሆነው ፍሬ ነገር ተፈጻሚ ይደረጋል። ሕጉም ሆነ ፍሬ ነገሩ ሁለቱም ግልጽ ባልሆኑ ጊዜ በውሣኔው ላይ

በፍሬ ነገሩ የተሰጠው ክብደት ተመዝኖ ከተቀመጠ በኋላ ሕጉ በምን መልኩ ተፈጻሚ ሊሆን እንደሚገባው ይፃፋል፡፡ ፍሬ ነገሩ ብቻ ግልጽ ካልሆነ ይህንኑ በምዘና ወስኖ ግልጹን ሕግ ተፈጻሚ ማድረግ ነው፡፡ ሁልጊዜ ግልጽ ላልሆነው ነገር ምላሽ መስጠትን ማስቀደም እና መቋጫውን ግልጽ ከሆነው ነገር ጋር ማገናኘት አፃፃፉን ይበልጥ ተነባቢ ያደርጋዋል፡፡

ከፍ ሲል ለመግለጽ እንደተሞረው በሕግ ጥያቄ የሚደረስበት መደምደሚያ የፍሬ ነገርን መደምደሚያ መሠረት ያደረገ ነው፡፡ በፍሬ ነገር ላይ የሚደረስበት ድምዳሜ በዳኝነት ነፃነት ላይ የተመሠረተ ሣይሆን የቀረበን ማስረጃ መሠረት ያደረገ ነው፡፡ ይህ በራሱ የመጨረሻ የሚሆን ሣይሆን ለሕግ ጥያቄ ምላሽ ለመስጠት መነሻ ነው፡፡ የሕግ ጥያቄ ምላሽ በሚሰጥበት ጊዜ የተባለውን ሕግ ሙሉ ቁጥር / አንቀጽ / መገልበጥ ላያስፈልግ ይችላል፡፡ ልዩ ሁኔታዎች እንደተጠበቁ ሆነው በዚህ መልኩ ሕጉ ባይገለበጥ ይመረጣል፡፡ ፍሬ ነገር ጥያቄ ትርጉም ያለው የሕግ ውጤት የሚኖረው በዚህ ጊዜ ነው፡፡ የተከራካሪ መገኖች መብት ውሣኔ የሚያገኝበት በመሆኑ ከፍሬ ነገር ጋር ትስስሩ በግልጽ ተመልክቶ ነገር ግን በአንድ ዓርፍተ ነገር ከፍሬ ነገር በነፃ መልኩ መቀመጥ ይኖርበታል፡፡

ለምሣሌ፡-

ፍሬ ነገር መደምደም ← ተከሣሽ የውሉን እንቁላል በጥር አጋማሽ/2000

አላስረከበም፣ →

የህግ መደምደሚያ ← ጥር አጋማሽ /2000 ባለማስረከቡ ውል አፍርሷል፣

ፍ/ቤቱ የሕግ መደምደሚያ ላይ ሲደርስ ፍሬ ነገሩን መሠረት በማድረግ አይገባም ያለውን ሕግ የመፈለግ፣ ለጉዳዩ በጥቅሉ እና ለያዘው ጉዳይ በተለይ የሚፈጸም መሆኑን መርምሮ ነው፡፡ ይህም በፍ/ቤቱ የተለየውን ጭብጥ አገላለፁ እና የማስረዳት ሸክሙን መወጣት ያለበት ወገንን ማስረጃ በተከተለ ሁኔታ ይገለፃል/ ይፃፋል/፡፡የሕግ እና ምክንያት ትንተና ከተቋጨ በኋላ የፍርድ ቤቱ ውሣኔ ይገለፃል፡፡ ይህን " ውሣኔ" በተቻለ መጠን አጭር እና ለአፈጻጸም የሚመች መሆን አለበት፡፡ ግልጽ፣ አጭር ምጥን ቃል መሆንና ሁሉም ወገኖች የሚገባቸውን/ የማይገባቸውን በቀጥታ የሚናገር መሆን አለበት፡፡ <u>ለምሣሌ</u>፡- ከፍ ሲል በተገለጸው መሠረት " ከሣሽ ክሱን ያቀረበው ውሉ ከፈረሰ ከሁለት ዓመት በኋላ በመሆኑ ክስ የማቅረብ መብት የለውም" ተብሎ ሊፃፍ ይችላል፡፡ የበለጠ የሚገለፀውም ከሆነ "----- ክሱ በይርጋ ቀሪ ይሆናል" ሊባል ይችላል፡፡ ከውሣኔው ጋርም ተያይዞ ተፈፃሚ መሆን የሚገባቸው ጉዳዮች ሊካተቱ ይችላሉ፡፡ ለምሣሌ ከሣሽ አላግባብ ክስ በማቅረቡ ተከሣሽን ለወጭ እና ለኪሣራ ለዳረገበት ካሣ …… ይከፈል፣ በዚህ ውሣኔ ቅር የተሰኘ የይግባኝ መብቱ የተጠበቀ / በሕግ / ነው፣ መዝገቡ የተዘጋ በመሆኑ በቋሚነት

ስለሚቀመጥበት ቦታ ... ሊወሰን ይችላል፡፡ ይህ ውሣኔ ብዙውን ጊዜ ትዕዛዝ በሚል ርዕስ ስር ሲቀመጥ እንመለከታለን፡

**<u>የወንጀል ጉዳይ የውሳኔ አሰጣጥ</u>**

ህጉ በየቀጠሮው የሚሠጥ ውሳኔ፣ ትዕዛዝ፣ፍርድ ይዘት ምን መምሰል እንዳለበት በዝርዝር በግልፅ አያስቀምጥም፡፡ ይሁን እንጅ የወ.መ.ስ.ስ.ህግ ከአንቀጽ 136-149 የማስረጃ ስርዐትና የፍርድ አሰጣጥ ሁኔታ ይደነግጋል፡፡

- የመዝገብ ቁጥር፣
- ጉዳዩ የታየበት ቀን /እና ሠዓት፣
- የዐ/ህግ፣ የተከሳሽ /ጠበቃ/ስም፣
- የዳኞች ስም፣
- የጉዳዩ መሰማት የተቆረጠበትን እና የተቀጠረበትን ቀን /ቁ 98
  በፅሑፍ መያዝ አለበት፡፡
  - በተቃውሞ ላይ የሚሠጥ ውሳኔ ያለ ቀጠሮ “ወዲያውኑ” መሠጠት ያለበት ሲሆን ሌሎች ክርክር የተደረገባቸው የህግ ጉዳዮችም ያሉ እንደሆኑ ክርክሩ በተነሳበት ቀን መፃፍ አለባቸው፡፡
  - ውሳኔዎች እና ትዕዛዞች በተለይ የሚፈፀሙ በመሆናቸው ግልፅ ሆነው መፃፍ አለባቸው ከምንል በቀር በህጉ ላይ እያንዳንዱ ውሳኔ ትዕዛዝ ሲፃፍ ሊከተለው ስለሚገባው /ሊይዘው ስለሚገባ/ቅርፅ የተገለፀ ነገር የለም፡፡

ይሁን እንጅ በወ/መ/ህ/ስ/ስ/ቁጥር 149 መሠረት የሚሠጥ ፍርድ በቅርፅ ደረጃ ሲታይ የሚከለውን ይመስላል፡፡

ፍርድ

↓

ውሳኔ/የቅጣት

↓

ትዕዛዝ/አፈፃፀም/ሊይዝ የሚችል መሆኑን ስንመለከት በይዘቱም

- ፍርድ የተሰጠበት ቀን፣
- የዳኛ ፊርማ፣
- የማስረጃ አጭር መግለጫ፣
- ማስረጃ ተቀባይነት ያገኘበት ምክንያት፣

- ማስረጃው ተቀባይነት ያላገኘበት ምክንያት፣
- ፍርዱ መሠረት ያደረገው የህግ ቁጥር፣
- ጥፋተኛ ያሰኘው ህግ፣
- ቅጣትን ለማክበድ እና ለማቅለል የተሰጡ አስተያየቶች፣
- ይህን ለማስረዳት የቀረበ ማስረጃ / ስለ ጠባዩ/፣
- የይግባኝ መብት ያለ መሆኑን ስለ መናገር መፃፍ እንዳለበት የወ.መ.ስ.ስ ህግ ቁጥር 149 መረዳት ይቻላል። በወንጀል ጉዳይ የሚሠጥ ፍርድ ላይ መገለፅ እንዳለበት በህጉ ላይ የተመለከተ ሲሆን፣

- የፍ/ቤቱ ስም፣
- ፍርድ ቤቱ ያስቻለበት ቦታ፣
- የተከሳሽ ማንነት /አድራሻ/፣
- ወንጀሉ የተፈፀመበት ቦታና ጊዜ፣
- የተላለፈው የህግ አንቀጽ፣
- ተከሳሹ /አምኖ/ መከራከሩን /ጭብጥ፣
- ተከሳሽ ያቀረበው የክስ ተቃውሞ ካለ ውሳኔው መኖሩ በአጭሩ የተገለፅ፣
- ለክሱ የቀረቡ ማስረጃዎች አይነት እና ዝርዝር፣
- መከላከያ ማስረጃ ቀርቦ ከሆነ በተመሳሳይ መልኩ አይነቱን፣ብዛቱን፣ የሚያስረዳውን፣ጭብጥ ተቀባይነት ያገኘበትን /ያጣበትን ምክንያት፣

ክርክር የተደረገባቸው ሌሎች ጉዳዮች /ምሳሌ፡- ዕድሜ ጤና../ካሉ ክርክራቸውና ውሳኔው፣ በጥቅሉ በአግባቡ መገለጽ ይኖርበታል።ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ጉዳዮች በህግ እና በልምድ ተቀባይነት ያላቸው አሰራሮች ናቸው። አንዳንዶቹ ነጥቦች በውሳኔው ላይ በግልፅ መቀመጥ ያለባቸው ለይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ለተከራካሪ ወገንና ለህብረተሰቡ መገለፅ ስላለባቸው ነው።ክርክሩ ሁሉ ተገቢውን ሚዛንና ክብደት የተሰጠው መሆኑን ለማስረዳትና የወንጀል ፍርድ የማስተማር አላማ ያለው በመሆኑ ለአስተማሪነቱም ጭምር ነው።

## 15.2 ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት

በፍ/ቤቶች አወቃቀር የበላይ የሆኑ ፍ/ቤቶች ዋነኛ ተግባራቸው በሥር ፍ/ቤት የታዩ ጉዳዮችን በይግባኝ መመልከት ነው። የሀገራችን ፍ/ቤቶች አወቃቀር ከዚህ እምብዛም የተለየ አይደለም።
በወረዳ ፍ/ቤቶች የቀጥታ ክስ ክርክሮች የሚበዙ ሲሆን በበላይ / በከፍተኛ እና ጠቅላይ ፍ/ቤቶች / በይግባኝ የሚታዩት ጉዳዩች እየበዙ ይመጣሉ። ይህ ማለት ግን በወረዳ ፍ/ቤት ይግባኝ አይታይም

በጠቅላይ ፍ/ቤቶች ደግሞ ቀጥታ ክስ አይኖርም ማለት አይደለም፡፡ መጠኑ እና የሚጠበቀው ውጤት፣ ይለያያል እንጅ በሁሉም ፍ/ቤቶች ይግባኝ ይታያል፡፡ ስለሆነም የሚከተለው ውይይትም እንደአግባቡ ለፍ/ቤቶች ሁሉ ያገለግላል፡፡ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት አንድን ጉዳይ በይግባኝ በሚመለከቱበት ጊዜ በዋነኛነት የክለሣ ተግባር ያከናውናል፡፡

የሥር ፍ/ቤት የሥነ ሥርዓት ሕጉን በአግባቡ ለመፈጸሙ፣ መሠረታዊ ሕጐች አለመጣሣቸው፣ ማስረጃ በአግባቡ መመዘኑን፣ እና የመሣሠሉ ተግባራት በፍትህዊነት መፈጸማቸውን ያረጋገጣል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የመጨረሻው በሆነ ጊዜ የሕግ ስህተት አለመፈጸሙን ያረጋግጣሉ፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የመጨረሻው በሆነ ጊዜ አትኩረቱ በሕግ ጥያቄዎች ላይ ሆኖ ሕገ መንግስታዊ ድንጋጌዎች አለመጣሣቸውን ፖሊሲዎች እና ሌሎች ሕጐችም በመሠረታዊነት አለመጣሣቸውን በማረጋገጥ በክልሉ ወይም በሀገሪቱ ተመሣሣይ እና ተገማች የሆነ የሕግ ሥርዓት መኖሩን የሚረጋገጥ ተጨማሪ ከባድ ኃላፊነት አለባቸው፡፡

የይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ከመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በተለይ የሚለየው ጉዳይን በይግባኝ/ በክለሣ/ መመልከቱ ብቻ አይደለም፡፡ ይህንን ለመፈጸም በአብዛኛው የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትን የመዝገብ ግልባጭ ይመረምራል፡፡ ከታች የመጡትን የመዝገብ ግጭባጭ ከመረመረ በኂላ የሥር ፍ/ቤትን ውሣኔ የማጽናት፣ የመሻር፣ የማሻሻል፣ ጉዳዩ እንደገና እንዲወሰን ወይም ተጣርቶ እንዲመለስለት የመወሰን ሥልጣን አለው፡፡ የበላይ ፍ/ቤት ይህንን ሥልጣን ከሥር በተለየ መልኩ በኀብረት በሚሠራ የዳኝነት ተግባር ያከናውናል፡፡ ዳኝነት በቡድን / በኀብረት/ የሚሠራ በመሆኑ የውይይት ተግባር በስፋት የሚከናወንበትና አብዛኛው የተስማማበት የፍ/ቤቱ ውሣኔ የሚሆንበት ነው፡፡ በአብዛኛው ሃሣብ ያልተስማማ የራሱን ሃሣብ ያስፍራል፡፡ በአንድ ጉዳይ አነስተኛ ድምጽ ያለው በሌላው በአብዛኛው ድምጽ ውስጥ ሊካተት ይችላል፡፡ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት የዳኝነት ተግባሩን በአብዛኛው በኀብረት የሚከናወን ይሁን እንጅ በሀገራችን የውሣኔ አፃፃፍ ሥርዓት የፍ/ቤት ውሣኔ የምንለው በአንድ ዳኛ ተጽፎ በሁሉም የሚፈረምበት ነው፡፡ ውሣኔውን የሚጽፈው ዳኛ የራሱን ብቻ ሣይሆን የሥራ ባልደረቦቹ ሊያደርጉ የሚፈልጉትን ጥንቃቄ መረዳት ይኖርበታል፡፡ ጽሑፍ የአንድ ዳኛ ውሣኔ ሣይሆን ከፍሬ ነገርም ይሁን ከሕግ የተጨመቀ የጋራ የአእምሮ ውጤት መሆኑን ማሣየት ይገባዋል፡፡

በኀብረት በሚከናወን ተግባር ውስጥ ልዩነትን ሙሉ በሙሉ ማስቀረት አይችልም፡፡ በሌላ በኩልም በውሣኔው የሚስማማ ነገር ግን የተለየ ምክንያት መቀመጥ ይገባዋል የሚል ሃሣብ ሊኖረው ይችላል፡፡ የእነዚህ ልዩነቶች መፃፍ በዳኝነት ሥርዓቱ አቋም መጠናከር አስፈላጊ ሲሆን ቢፃፍ ይመረጣል፡፡ ሲፃፍም አብዛኛውን ዳኛ በግል የሚመለከቱ ሁነው ሣይሆን የችሎት ውሣኔ

የተባለውን ብቻ በሚመለከት ይሆናሉ። ትችት እና ወቀሣ ያዘሉም መሆን የማይገባቸው ሆኖ በክርክሩ ላይ የተስማማውን ጭብጥ ብቻ ማዕከል ያደረጉ ይሆናሉ። በተቻለ መጠን ልዩነት የሚያሰፍር ዳኛ ቢቻል ምጥን ባለ አገላለጽ ከሌሎች ባልደረቦቹ ጋር የማይስማማባቸው ነጥቦች እንዳሉ እና ነጥቦቹም ዘርዘር ብለው ቢገለጹ ይመረጣል።

## የአጻጻፍ አድማስ

ተደጋግሞ እንደተገለፀው የአንድ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ዋና ተግባር በሥር ፍ/ቤት የውሣኔ አሰጣጥ እና አካሄድ ላይ የተከሰቱ ስህተቶች በመከላከል ማረም ነው። በዚህ ረገድ በሥር ፍ/ቤቶች በርካታ ስህተቶች ተፈጽመው ሊገኙ ይችላሉ። የተወሰኑት ተከራካሪ ወገን ላይ ጉዳት የማያደርሱ ሊሆኑ ይችላሉ። ለምሣሌ ከሣሽ 10×10=100 ብር ይገኛል በማለት የጠየቀውን ፍ/ቤቱ 5×20=100 ብር ይገባዋል ብሎ ቢወስን እንደማለት ነው። የዚህ ዓይነት ስህተቶች በተለይ ከሀገራችን የሙግት መብዛት ጋር ተያይዞ ፍትህን የሚያዛቡ ሊሆኑ ስለማይችሉ በይግባኝ ላይታረሙ ይችላሉ። ስህተት ግልጽ እና አንድ ፍ/ቤት በመሠረቱ ሊከተለው የሚገባውን አቅጣጫ የሣተ ሆኖ ሲገኝ መታረም ግድ ይለዋል። ስህተት አልተፈጸመም፣ ስህተት ቢፈጸምም ጉጅ አይደለም እንዲሁም ስህተቱ መታረም አለበት በማለት የይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት የሚይዘው አቋም የሚገለጽበት ጽሑፍም ይለያያል። የውሣኔው ይዘት ከፀሐፊ ፀሐፊ ሊለያይ ቢችልም በጥቅሉ የሚከተለውን ይመስላል።

1. የጉዳዩ ዓይነት፣
2. ጭብጥ፣
3. ፍሬ ነገር፣
4. የተገኘው ስህተት / ሕግ፣ ትንታኔ፣ምክንያት/፣
5. ማጠቃለያ፣

አንድ ውሣኔ ማጠቃለያ ይኖረዋል። ከተራ ቁጥር 4 ድረስ የተመለከቱት ነጥቦች በመሠረቱ ከዚህ ቀደም በነበረው ክፍል የተመለከትናቸው ሲሆኑ ልዩ ሁኔታዎች በውይይት የሚታዩ ሆነው በዚህ ክፍል ውይይት በተራ ቁጥር 5 ሥር የተመለከተውን ብቻ እናያለን።የፍ/ሥ/ሥ/ሕግ በቁጥር 348/1/ ላይ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በይግባኝ የቀረበለትን ውሣኔ ለማጽናት፣ ለማሻሻል፣ ለመለወጥ፣ ወይም ለመሻር" ይችላል በማለት ይደነግጋል። በቁጥር 341 እና 343 መሠረትም ጭብጥ አስተካክሎ ወይም ክርክር ተደርጐ ውሣኔ እንዲሰጥ ጉዳዩን ለበታች ፍ/ቤት መመለስ ይችላል። በተመሣሣይ መልኩ የወንጀል ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁጥር 195 መሠረት ይግባኙን የማጽናት፣ጉዳዩን ሌላ ፍርድ ቤት እንዲምለከተው ማዘዝ፣ ውሣኔውን ሙሉ

በሙሉ የመሻር፣ ቅጣትን የመጨመር፣የማጽናት፣የመቀነስ፣ ሥልጣን አለው፡፡ ይህ ሥልጣን በተራ ቁጥር 5 ሥር የተቀመጠው የይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ይግባኙን ከመረመረ በኋላ አቋሙን የሚገልጽበት ማጠቃለያው ነው፡፡

1. ማጽናት

ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት የሥር ፍ/ቤትን የመዝገብ ግልባጭ/ መዝገብ/ ከመረመረ በኋላ በክሱ ውስጥ የሚያስገባው ስህተት አለመፈጸሙን ከተረዳ ይህንኑ በመግለጽ ብቻ ብዙ ሣያስፈልገው ውሣኔውን በጹሑፍ ማስፈር ይችላል፡፡ የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) እና የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁጥር 195 ይህንኑ ያስምሩበታል፡፡ በዚህ መሠረት የይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት" ይግባኝ ባይ ያቀረበው ቅሬታ ተቀባይነት ስለሌለው የሥር ፍ/ቤት ውሣኔ ፀንቷል" በማለት ውሣኔን መፃፍ ይቻላል ማለት ነው፡፡

በሀገራችን የውሣኔ አፃፃፍ ሥርዓት ውስጥ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤቶች የሥር ፍ/ቤት ውሣኔ ሲያፀኑ" የይግባኝ ባይን ቅሬታ ከሥር ፍ/ቤት የመዝገብ ግጭባጭ ጋር አገናዝበን እንደመረመርነው በሥር ፍ/ቤት የተፈጸመ የሕግም ሆነ የፍሬ ነገር ስህተት ያላገኘን በመሆኑ ይግባኙን በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 /በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁጥር /95/1/ መሠረት ሠርዘናል፣ መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ " የሚል አጭር ትዕዛዝ መስጠታቸው በጣም የተለመደ ነው፡፡ ይህንን አፃፃፍ በተመለከተ አንዳንድ ፀሐፊዎች የይግባኝ ባይ ቅሬታ ለምን ተቀባይነት እንዳላገኘ የማይገልፁ በመሆኑ ትክክለኛ አፃፃፍ አይደለም  በማለት ሲተቹ ይሰማሉ፡፡

**የመወያያ ጥያቄ**

1. በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ እና ሌሎች ሥልጠናዎች ውስጥ ከተመለከትካቸው ውሣኔዎች ውስጥ፣

- የሰበር መ/ቁጥር 34694 በ11/6/2000 የተሰጠውን ትዕዛዝ፣
- በመ/ቁጥር 03234 በ3/3/2000 የተሰጠውን ትዕዛዝ፣

ተመልክተህ በውሣኔ አፃፃፋቸው ላይ ያለህን አስተያየት አስቀምጥ/ጭ/፡፡ ሁሉንም ትዕዛዞች አግባብ ነው ባልከው /ሽው/ አፃፃፍ አስፍር፡፡

16. ውሣኔ አፃፃፍ እና ሥነ ምግባር

ውድ ሰልጣኞች ከዚህ ቀደም የሥነ ምግባር ኮርሶችን ወስዳችኋል ተብሎ ይገመታል፡፡ ውሣኔ ሰጭዎች ሥነ ምግባራቸውን ሊጠብቁ የሚገባው ለፍ/ቤት/መ/ቤታቸው / እና ከፍርድ ቤት ውጭ በንግግራቸው፡ በአኳኋናቸው፣ እና በጹሑፋቸው ነው፡፡ በሁሉም ረገድ ምን ዓይነት ሥነ ምግባር

ሊከተል እንደሚገባ ከዚህ ቀደም የተመለከትነው ስለሆነ ተመልሰን በድጋሜ አንመለከተውም።( ይልቁንም ውሣኔ ሰጭዎች በጹሑፋቸው ምን ዓይነት ሥነ ምግባር ሊከተሉ እንደሚገባቸው ለይተን ብቻ በጥቅሉ እንመለከታለን።በሀገራችን የፍትህ ሥርዓት ክርክሮች እና አለመግባባቶች በፍ/ቤት ሲቋጩ በጹሑፍ መሆን እንዳለባቸው ህጎቻችን በአስገዳጅነት ደንግገዋል። የዳኞች የመጨረሻ ተግባር አለመግባባትን በውሣኔ መቋጨት ነው። ውሣኔው የተለያየ ስያሜ እየያዘ በጹሑፍ ይሰፍራል።

ከውሣኔ በፊት ዳኞች ያላቸው የፍ/ቤት አመራር ችሎታ እና በሕብረተሰቡ በተለይ በተከራካሪ ወገኖች ብቻ ምስክርነት የሚያገኝ ነው። በፍ/ቤት ያለ አብዛኛው ታዳሚ ለራሱ ጉዳይ ብቻ የተለየ ትኩረት የሚሰጥ ነው። ዳኛው ለሁሉም አግባብ ከባለጉዳይ ጋር የሚገናኘውም በዚሁ በራሱ ጉዳይ ነው። የፍ/ቤት ውሣኔ በጹሑፍ መስፈር ግን የግንኙነት አድማሱ ከሁሉም የሕብረተሰብ ክፍሎች ጋር የሚሆንበት ዕድል ይሰፋል። በሁሉም ግንኙነቶች የዳኞች ውሣኔ / አስተያየት/ ባለጉዳይ እንዲሁም ሕብረተሰቡ ላይ ተፅዕኖ የሚያሣድረው ለተደረሰበት መደምደሚያ ብቻ ሣይሆን ውሣኔዎች እንዴት እንደተፃፉም ጭምር ነው።

ከፍ/ቤት ውጭ ታዳሚ ዳኞችን " የሚዳኘው" በውሣኔያቸው ላይ በሚያሰፍሩት በዚሁ ፀሑፍ ነው። ሕብረተሰቡ በፍ/ቤት ላይ እምነት የሚጥለውም በተለይ በዚሁ ውሣኔ ነው። ጹሑፍ ችሎታ ይለካበታል፣ ይግባኝ ላይ ወሣኝ ሚና ይኖረዋል፣ የሕብረተሰቡን ማኅበራዊ ግንኙነት የሚኖረውን ይዘት ይወስናል፣ ተጠያቂነትን ያስከትላሉ፣ ለሕግ ትምህርት እና ምርምር መሠረት ይሆናሉ፣ የታሪክ ሰነድ ነውና። ስለሆነም የሚፃፍ ውሣኔ ሊታመን የሚችል ገለልተኛ፣ ቶን ያለው፣ ክብሩን የጠበቀ፣ጉዳዮ ከሚፈጥረው ስሜት የራቀ፣ መሆኑን ማረጋገጥ ይገባል።በእርግጥ በሥነ ምግባር መርሆዎች ውስጥ ምን ማድረግ እንዳለባቸው ከመግለጽ/ ከመዘርዘር/ ይልቅ ምን መደረግ የለባቸውም የሚባሉትን መዘርዘሩ ቀላል ነው። በውሣኔ አፃፃፍ ውስጥም ስድብ መግባት የለበትም፣ የተገለበጠ/ የተዘበራረቀ መሆን የለበትም፣ ከፍሬ ነገር የወጣ መሆን የለበትም ወዘተ..... የሚሉትን መዘርዘሩ ምን መካተት አለበት የሚለውን ከመዘርዘር ይቀላል።ጥሩ የውሣኔ ጹሑፍ የሚባለው የተከለከሉትንም የተፈቀዱትና በአግባቡ ግንዛቤ ውስጥ ያስገባ ነው። በጥሩ ሥነ ምግባር የታነፀ ዳኛ ጥሩ ውሣኔ ሊጽፍ ይችላል። ይህ ማለት ግን ጥሩ ስነ ምግባር ያለው ዳኛ ሁልጊዜ ጥሩ ውሣኔ ይጽፋል ማለት አይደለም። ጥሩ ውሣኔ ለመፃፍ ከሚያስፈልጉ ቁምነገሮች ውስጥ አንዱ የሥነ ምግባር ደንቦች በውሣኔ በጹሑፍ ውስጥ በአግባቡ መጠበቃቸውን ማረጋገጥ ነው።

17. <u>የዳኝነት የውሳኔ ፅሁፋ ታዳሚ መለየት</u>

ዳኞች ውሣኔ ሲጽፍ ውሣኔውን በማንበብ የሚታደሙ በርካታ እና የተለያየ የሕብረተሰብ ክፍል እንደሆነ ልብ ማለት ይገባቸዋል፡፡ የአንድ ውሣኔ ታዳሚ ሊሆኑ ከሚችሉት ውስጥ፣

- ውሣኔውን የሚጽፈው ዳኛ ራሱ፣
- የሥራ ባልደረባ ዳኛ /ዳኞች /፣
- የውሣኔው ፈራሚ ዳኞች፣
- የሙያ / የሕግ / ማኅበር፣
- የሕግ ትምህርት ቤቶች፣ ሥልጠና ማዕከላት ፣
- በጉዳዩ ላይ ያገባናል የሚሉ ወገኖች፣ /ለምሣሌ ሴቶች ማኅበር /፣
- ሕብረተሰቡ በአጠቃላይ ፣
- ሕግ አውጭውና የመንግስት አካላት ፣
- ዓለም አቀፍ / አገር አቀፍ / ድርጅቶች ፣
- ሚዲያ ፣
- ኢምባሲዎች ፣
- የመላው ዓለም /በኢንተርኒት/ ፣ ዌብ ሣይት ወዘተ የሚገኝበት መሆኑን ማስተዋል ተገቢ

ነው፡፡ውሣኔው ሲፃፍም በተለይ የሚመለከተው ታዳሚ እና የውሣኔው ግብ መለየት አለበት፡፡ ተከራካሪ ወገኖች /በተለይ / በሕግ አሣማኝ የሆነ አስገዳጅ ውሣኔ የማግኘት መብት እንዳላቸውና ይህን መብት የማክበር ግዴታ ደግሞ የውሣኔ ሰጭው አካል ይሆናል፡፡ ውሣኔ ሰጭዎች ሕግን የመተርጐም/ ሕግን የመፈጸም/ ተግባራቸውን ገለልተኛ፣ ፍትሐዊ እና ግልጽ በሆነ መንገድ መውጣታቸውን በሕግ አውጭው እና በሕብርተሰቡ ያለባቸውን ተጠያቂነት ከሚወጡበት መንገድ አንዱ በአሣማኝ ምክንያት ላይ የተደገፈ ውሣኔ በመፃፍ ነው፡፡ ውሣኔ በሚፃፍበት ጊዜም ከላይ ከተመለከቱት እና መሰል ታዳሚዎች መሐከል፣

- ❖ ውሣኔውን ማን ሊያነበው እንደሚችል፣
- ❖ አንባቢው ምን ማድረግ እንዳለበት፣
- ❖ ውሣኔው የሚገለጽበት አግባብ እና ቃል፣

ከአንባቢው ጋር ያለው ግንኙነት ምን ሊሆን እንደሚችል አስቀድሞ በአእምሮ ማሰብ ይኖርበታል፡፡ ውሣኔ በሚፃፍበት ጊዜ በውሣኔው ሊስማማ የማይችል አካል ሊኖር ይችላል፡፡ በክርክሩ የተሸነፈ ጠበቃ፣ የጠበቃ ማኅበር፣ተከራካሪ ወገን፣ ሌላ ዳኛ፣ የበታች ወይም የበላይ ፍ/ቤት ወዘተ በተሰጠው ውሣኔ ላይ ላይስማሙ ይችላሉ፡፡ ክርክሩን በሽንፈት ያጣ ተከራካሪ ወገን በተለይ

በውሣኔው እንዲስማማ ለማድረግ  አግባብ ያለው የፍሬ ነገር ክርክር ሣይዛባ በታማኝነት ማስፈር የሚያስፈልግ ሲሆን፣ ቢቻል ከፍሬ ነገሮች ውስጥ ፍርድ ቤቱ የተስማማባቸው ነጥቦች የተወኑትን በዚሁ ቃላት መገለጹ ጥሩ ይሆናል፡፡

ይህም ፍ/ቤቱ ውሣኔ ሲሰጥ ለተከራከሪ ወገኖች ክርክር እኩል ክብደት የሰጠ ታማኝ መሆኑን ለማሣየት ይጠቅማል፡፡ ለተከራካሪ ወገኖች ክርክር ታማኝ መሆን ማለት ግን ተከራካሪ ያቀረበውን ክርክር ሙሉ በሙሉ በውሣኔ ላይ ገልብጦ ማስፈር ማለት አይደለም፡፡በአጠቃላይ ውሣኔ በሚፃፍበት ጊዜ ከሙያው የሚጠበቀው ሥነ ምግባር በአጠቃላይ መጠበቁን ማረጋገጥ ይገባል፡፡ ለአብነት ገለልተኝነት ማሣየት፣ ዲዩ ኘሮሰስ መጠበቁን፣  ውሣኔ የመስጠት ብቃት ያለ መሆኑን ፣ የታዳሚ ክብርና  ሙገሣ ሊቸረው የሚገባ የፍ/ቤትን ክብር የጠበቀ መሆኑን እና የሙሣሠሉትን የሥነ ምግባር መርሆዎች ያከበረ መሆኑን ማረጋገጥ ይገባል፡፡

## የመወያያ ጥያቄ፣

1. ሥነ ምግባር እና የውሣኔ አፃፃፍ ያላቸውን ግንኙነት አብራራ/ ሪ /፣
2. ከዚህ በታች ያሉትን ጉዳዮች ተመልክተህ(ሽ) የውሣኔውን ግብ እና ታዳሚ ላይ፣
   - 2.1. አቶ “ ሀ ” ለልጅ ልጁ ሞግዚት እንዲሆን ጥያቄ አቅርቧል፡፡ በሌላ በኩል“ሀ”  ልጅ ለራሷ ልጅ ሞግዚት መሆን ይገባኛል በማለት ተቃውማለች፡፡ አቶ “ሀ ” ሞግዚት ሊሆን ይገባል በማለት ትዕዛዝ ሰጥተሃል፡፡
   - 2.2. አቶ  “ ለ ” ጠበቃ ለያዘው ክርክር የጠየቀው ክፍያ የተጋነነ ስለሆነ ሊቀነስ ይገባል በማለት ወ/ሮ “ መ ” ጠይቀዋል፡፡ ክፍያው የተጋነነ በመሆኑ የሙያ ሥነ ምግባሩን ባለመጠበቁ ሊቀነስ ይገባዋል በማለት ትዕዛዝ ሰጥተሃል፡፡
   - 2.3. አቶ “ ረ ”  ስሜ ይቀየርልኝና ውሣኔው ለውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ይላክልኝ በማለት ጠይቋል፡፡ ስሙ እንዲቀየርለት ትዕዛዝ ሰጥተሃል፡፡
   - 2.4. በ------ከተማ የሚሠራ የግንድ ባንክ ሠራተኛ ከባንኩ ደንብ ውጭ ለ2 ዓመት በቦታው እየሠራሁ ስለሆነ የ2 ዓመት ውሎ አበል ይከፈለኝ በማለት ጠይቋል፡፡ የ2 ዓመት አበል እንዲከፈለው ውሣኔ ሰጥተሃል፡፡
   - 2.5. የኢትዮጵያ አየር መንገድ አቶ “ መ ” የተባለው ሠራተኛ  ያለው ባህሪ በዓለም አቀፍ ውድድር ውስጥ የማያስቀጥለው በመሆኑ ከሥራ አሰናብቶታል፡፡ አቶ መ ወደ ሥራ እንዲመለስ ጠይቋል፡፡ በአማራጭ በቂ ካሣ ተከፍሎት እንዲሰናበት የቀረበውን ጥያቄ ተቀብለህ አቶ “ መ ” ወደ ሥራ እንዳይመለስ ወስነሃል፡፡

2.6. “ሮሃ” የተባለ ድርጅት ለመንገድ ሥራ ያከማቸው ድማሚት በአቶ “ በድሉ ” ይዞታ ላይ ሁከት የፈጠረ በመሆኑ በአስኳይ የተባለው ድማሚት በባለሙያ እንዲነሣ ወስነሃል፡፡ ጊዜ ቢጠይቅም ይህ ጊዜ መግዣ ብቻ ነው በማለት በአስቸኳይ እንዲነሣ ወስነሃል፡፡

## 18. አጠቃላይ የፍርድ አሰጣጥና አፃፃፍ ዘዴ ጉድለት ውጤት

ፍርድ የፍ/ቤቶች ዋናውና የመጨረሻው የሥራቸው ውጤት መስኪያ በመሆኑ ገድለቱ ዘርፈ ብዙ አሉታዊ ውጤት የሚያስከትል ስለሆነ በተቻለ መጠን በጥንቃቄ መታየት ይኖርበታል፡፡በመሆኑም ዋና ዋናዎቹን በምሳሌነት ለማየት ያህል በሚከተለው መልኩ ቀርቧል፡፡

1. የፍትህ መዘግየትንና መንፈግን ያስከትላል፡፡
2. በፍ/ቤቱም ሆነ በተከራካሪ ወገኖች ላይ አላስፈላጊ የገንዘብ፣ የቁሳቁስ የሰው ሃይልና የጊዜ ብክነትን ያስከትላል፡፡
3. አላስፈላጊ ይግባኝ እና ሰበር አቤቱታና ክርክር እንዲበዛ ያደርጋል፣
4. ባለጉዳዮች እንዲሁም ኅብረተሰቡ በፍ/ቤቶችና በፍትሕ ሥርዓቱ ላይ አመኔታ እንዲያጣ ያደርገዋል፡፡ በመሆኑም በማኅበራዊ/በኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ባህላዊ ሥርዓቱ ላይ አሉታዊ ውጤት ይኖረዋል፡፡ ተሳታፊዎች እስቲ ራሳችሁን በምሳሌነት ውሰዱና ለአፍታ (ሁለት ደቂቃዎች ወስዳችሁ) እንደባለጉዳይ ወይም እንደከሳሽ/ተከሳሽ ወይም ይግባኝ ባይና መልስ ሰጪ አስቡና ከመደምደሚያ ድረሱ ለመሆኑ በፍ/ቤቶቻችን አሠራር ፍርድ አሰጣጥና በፍትሕ ሥርዓቱ ላይ የአመኔታችሁ መጠን ስንት ፐርሰንት ይሆናል? በፌደራሉም ሆነ በክልል በከባድ ወንጀል ተጠርጥሮ ብከሰስ በሰንት ጊዜ/ወራት ወይም ዓመት /ፍርድ ይሰጠኛል ብላችሁ አስቡ?
5. የፍ/ቤቶችን ውጤታማነት ቅልጥፍና እና ታማኝነት ይቀንሰዋል፡፡
6. የፍ/ቤቶች ውሳኔ አሰጣጥና አፃፃፍ ተመሳሳይነት (Uniformity) እንዳይኖረው ያደርጋል፣
7. በሕግ አውጪው የወጣው ሕግ በአግባቡ ተተርጉሞ ዓላማውን እንዳያሳካና ግቡን እንዳይመታ ያደርገዋል፡፡
8. የፍርድ ቤቶችን ተደራሽነት (accessibility ) ይቀንሳል፡፡
9. የፍርድ ቤቶች ፍርዶች ለማስተማሪያነት ለምርምር /በሕግ ሳይንስ ዕድገት፣. . . . . የሚኖራቸውን ሚና ይቀንሰዋል፡፡
10. የፍ/ቤቶችን /የዳኞችን፣ ክብርና ዝናም የሚቀንስ ይሆናል፡፡

## ዋቢ መፃሕፍት


1. ፊሊጶስ ዓይናለም፣የውሣኔ /ፍርድ/ አሰጣጥና አፃፃፍ ዘዴ በኢትዮጵያ፣የአብክመ ጠቅላይ ፍ/ቤት ዝክረ ሕግ መጽሔት ቁጥር 1 ቅጽ 1 1999፣
2. ውብሸት ሽፈራው የውሣኔ አፃፃፍና ህገ- መንግስት /ያልታተመ /፣
3. ማርክነህ እና ሚካዔሌ የወንጀል ጉዳይ ትኩረት የሚሰጣቸው አንዳንድ ነጥቦች /ያልታተመ/፣
4. የኢፊዲሪ ሕገ መንግስት፣
5. የፍትሐብሄር ሥነ ሥርዓት ሕግ፣
6. የወንጀል ሥነ ሥርዓት ሕግ፣
7. የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የወንጀል ህግ፣
8. አዋጅ ቁጥር 120/98 የአማራ ክልል አስፈጻሚ አካላትን ማቋቋሚያ አዋጅ፣
9. ልዩ ልዩ የፍ/ቤት ውሣኔዎች፣